# ዲሞክራሲያዊ የለውጥ እርምጃዎች እንድምታዎች እና አማራጮቻቸው በኢትዮጵያ

## ቅጽ ሁለት፣ የኢኮኖሚ ጉዳዮች

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ
Forum for Social Studies

# ዲሞክራሲያዊ የለውጥ እርምጃዎች
# እንድምታዎች እና አማራጮቻቸው በኢትዮጵያ

ቅጽ ሁለት

## የኢኮኖሚ ጉዳዮች


**አርታኢዎች**

**አበበ አሠፋ**

**ክቡር እንግዳወርቅ**



ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ

FORUM FOR SOCIAL STUDIES (FSS)

© 2012 ዓ.ም ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ

አዲስ አበባ

ማንኛውም የአሳታሚው መብቶች በሕግ የተጠበቁ ናቸው

ISBN: 978-99944-50-72-4

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ

ፖ.ሳ.ቁ. 25864 ኮድ 1000

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ኢሜይል፡ fss@ethionet.et

ድረ-ገጽ፡ www.fssethiopia.org.et

ይህ መጽሐፍ የታተመው በናሽናል ኢንዶውመንት ፎር ዲሞክራሲ (National Endowment for Democracy) የገንዘብ ድጋፍ ነው በዚህ ህትመት ውስጥ የተገለጹት አስተያየቶች የፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ የሥራ አመራር ቦርዱን፣ የድርጅቱን አጋሮችና የገንዘብ ድጋፍ የሠጠውን ናሽናል ኢንዶውመንት ፎር ዲሞክራሲ አቋምና አመለካከት ላያንጸባርቅ ይችላል።

# ማውጫ

መቅድም. ........................................................................................................III

መግቢያ. .......................................................................................................V

የኢትዮጵያ ዐብይ-ኢኮኖሚ (ማክሮ-ኢኮኖሚ) ሁኔታና መንግስት ወደፊት በኢኮኖሚው ውስጥ ሊኖረው የሚገባ ሚና ............................................................................ 1

*ዓለማየሁ ገዳ*

የኢትዮጵያ የማክሮ ኢኮኖሚ ሚዛን መዛባት እና ቀጣይ አቅጣጫዎች ...................21

*ቴዎድሮስ መኮንን*

የመንግስት የልማት ድርጅቶች ማሻሻያ...................................................................37

*ብሩክ ታዬ*

ፕራይቬታይዜሽን በኢትዮጵያ፡- ኢትዮ-ቴሌኮም ለምን ይሸጣል?............................53

*ክቡር ገና*

## መቅድም

**ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ** (Forum for Social Studies-FSS) በፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ልማታዊ የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ጠለቅ ያለ ጥናትና ምርምር የሚያካሂድ፤ በአገራዊ ጉዳዮች ላይ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በመረጃ ላይ የተመሠረተ ውይይት እንዲያደርጉ መድረኮችን የሚያዘጋጅ መንግስታዊ ያልሆነና ለትርፍ ያልተቋቋመ ሀገር በቀል የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅት ነው። የድርጅቱ እንቅስቃሴ በመንግስት ፖሊሲ አውጪዎች፣ አስፈጻሚ የመንግስት አካላት፣ ምሁራንና ተመራማሪዎች፣ የሲቪል ማኅበራትና በአጠቃላይ በህብረተሰቡ መካከል በአገራዊ ጉዳዮች ላይ በትክክለኛ መረጃ ላይ የተመሠረተ፣ ግልጽና ቀና ውይይት ማድረግ ጤናማ የውይይት ባህልን ከማዳበርና ግልጽና አሳታፊ የፖሊሲ ቀረፃና ትግበራ ስርዓትን ለማስፈን ከማስቻሉ ባሻገር ለአገር ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ዕድገት፣ ለዴሞክራሲ መዳበርና ለዜጎች ዕኩልነት መስፈን ከፍተኛ ድርሻ ይኖረዋል በሚል ዕምነትና መርህ ላይ የተመሠረተ ነው።

ድርጅቱ ከሚያካሂዳቸው የጥናትና ምርምር ስራዎች በተጨማሪ ተከታታይ ሕዝባዊ የውይይት መድረኮችን የሚያዘጋጅ ሲሆን፤ በመድረኮቹም የመንግስት ፖሊሲ አውጪዎችና አስፈጻሚዎች፣ የሲቪል ማኅበረሠብ አካላትና ተመራማሪዎችን ጨምሮ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት በወቅታዊ አገራዊ የልማት ጉዳዮች ላይ በመረጃ ላይ የተመሰረተ ግልጽ፣ ገንቢና አሳታፊ ውይይቶች ያደርጋሉ።

ድርጅቱ ባለፉት ሁለት አስርተ ዓመታት ብዛት ያላቸው ተከታታይ ሕዝባዊ የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀት ሕብረተሰቡን ሲያሳትፍ የቆየ ሲሆን፤ የነዚህን የውይይት ወጤቶችን በተለያዩ ህትመቶችና የብዙሀን መገናኛ ዘዴዎች አማካኝነት ለህዝብ ተደራሽ ሲያደረግ ቆይቷል። ይሁን እንጂ በ2001 የወጣው የኢትዮጵያ በጎ አድራጎትና ማኅበራት አዋጅ በጣለው ገደብ ሳቢያ ድርጅቱ በአገራችን የፖለቲካና ፖለቲካ ነክ ጉዳዮች ላይ የሚያደርገው የጥናት፣ ምርምርና ሕዝባዊ የውይይት መድረክ ስራዎች ተቀዛቅዘቀው መቆየታቸው ይታወሳል።

ባለፉት ሁለት ዓመታት በአገሪቱ በመካሄድ ላይ የሚገኘው የፖለቲካ ሪፎርምና በመንግስት የተወሰዱ እርምጃዎች ይህንን ተቀዛቅዞ የነበረ ስራ ዳግም በመመለስ ረገድ በሁለት በኩል አስተዋፅዖ እንዳደረገ ይታመናል ። የመጀመሪያው እርምጃ በሲቪል ማኅበራት እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ገደብ አስቀምጦ የነበረው አዋጅ መሻሻል ሲሆን፣ አሁን ተሸሻሎ በወጣው የሲቪል ማኅበራት አዋጅ (ቁጥር 113/2011) ቀደም ሲል የነበሩት ስራ መስኮች ገደብ ተነስቶ ማንኛውም የሲቪል ድርጅት በየትኛውም ሕጋዊ ሥራ ላይ የመሠማራት ሙሉ መብት ሰጥቷል። በዚህ ምክንያት በፖለቲካና ፖለቲካ ነክ ጉዳዮች

የምናደርገውን የጥናት፣ ምርምርና ሕዝባዊ የውይይት መድረክ እንቅስቃሴዎች ለመቀጠል ችለናል። በሌላ በኩል ኢትዮጵያ ከ2010 ጀምሮ ዘርፈ-ብዙ በሆነ የፖለቲካ ሪፎርም ሂደት ውስጥ ያለች ከመሆኗ አንፃር ሪፎርሙ ቀደም ሲል ያልተነሱ ውይይትና ክርክርና የሚያስፈልጋቸው ወቅታዊ ሁኔታዎችን ይዞ መምጣቱ የፖለቲካና ፖለቲካ ነክ ጉዳዮች ላይ የሚደረገውን ሕዝባዊ የውይይት መድረክ ዳግም ለማንሰራራት ጥሩ አጋጣሚ ፈጥሯል።

በመሆኑም ***ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ*** ወቅታዊውን የአገራችን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ሁኔታን በሚመለከት ***ዲሞክራሲያዊ የለውጥ ጉዞ በኢትዮጵያ፡- የለውጥ ዕርምጃዎች፣ አንድምታዎቻቸውና አማራጮች*** በተሠኘ ርዕስ ሕዝባዊ የውይይት መድረኮችን ቀርጾ አካሂዷል። የውይይት መድረኮቹ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ተገኝተው በተመረጡ ወቅታዊ ርዕሶች ላይ የሚነጋገሩበት፣ ሀሳብ የሚለዋወጡበትና አማራጮችን የሚፈልጉበት መድረክ ለመፍጠር አስችሏል። በእያንዳንዱ የውይይት መድረክ ላይም ለውይይቶቹ በመነሻነት የሚያገለግሉ ጥናታዊ ጽሑፎች በየመስኩ በተሰማሩ ባለሙያዎች የቀረቡ ሲሆን፤ በነዚሁ ጥናታዊ ወረቀቶቹ ላይ ተመርኩዘው ተሳታፊዎች ሰፊ ውይይቶችን አካሂደዋል። የተካሄዱት ውይይቶችም በተለያዩ የሬድዮ ጣቢያዎችና ማሕበራዊ ሚዲያ አማካይነት ለሕዝብ እንዲደርሱ ተደርጓል።

ከዚህ በተጨማሪ ጥናታዊ ጽሑፎቹን በሕትመት ለህዝብ ለማድረስ ባለን ዕቅድ መሠረት ከተካሄዱት የውይይት መድረኮች መካከል የጀመሪያዎቹ ሁለቱ በቅፅ አንድ ታትመው የወጡ ሲሆን በክፍል ሦስት እና አራት የቀረቡት በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላይ ያተኮሩት ውይይቶች ደግሞ በዚህ ቅፅ ታትመው ቀርበዋል ። በመጨረሻዎቹ ሁለት መድረኮች የቀረቡት ውይይቶችም በቀጣዩ እና በሶስተኛው ቅፅ ታትመው የሚቀርቡ ሲሆን፣ በእነዚህ መድረኮች ላይ ጥናታዊ ጽሑፎችን በማቅረብ፣ በአወያይነትና በተሳታፊነት የተሳተፉትን ባለድርሻ አካላትን በሙሉ ለማመስገን እወዳለሁ። በተለይ ይህን ሕዝባዊ የውይይት መድረክ እና ህትመት ለማዘጋጀት ያስቻለንን ናሽናል ኢንዶውመንት ፎር ዲሞክራሲን (National Endowment for Democracy-NED) የተሰኘውን መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ከልብ አመሠግናለሁ።

የራስወርቅ አድማሴ (ዶ/ር)
ስራ አስፈፃሚ ዳይሬክተር
ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ

## መግቢያ

በኢትዮጵያ በየወቅቱ በተከሰቱት ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ሳቢያና የችግሮቹን መንስዔዎች ናቸው ተብለው የሚታሰቡትን ምክንያቶች ለማስወገድ የታለሙ ፖለቲካዊ ለውጦች ተካሂደዋል። ባለፈው ግማሽ ምዕተ-ዓመት ውስጥ እንኳን ዓብይ ሊባሉ የሚችሉ ሦስት ፖለቲካዊ ለውጦች ተካሂደዋል። የዘውዳዊውን አገዛዝ ገርስሶ ስር-ነቀል ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጥ ያስከተለው የ1966ቱ አብዮት የመጀመሪያውና ዋናው ሲሆን፤ በመቀጠልም ለአስራ ሰባት ዓመታት የዘለቀውን ይህንን የደርግ አገዛዝ በመቃወም በ1983 የተከተለው ለውጥ ሌላው ዐቢይ ፖለቲካዊ ዕውነታ ነው። ይህን ለውጥ ተከትሎ በኢትዮጵያ በእርግጥም የተሻለ የኢኮኖሚና የመሠረተ-ልማት ውጤቶችን አሳክታለች። በኢኮኖሚ ረገድ አገሪቱ ባለፉት ሁለት ዓስርተ-ዓመታት ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ከማዝመግቧ በላይ ከ1998 እስከ 2008 ባሉት አስር ዓመታት የአገሪቱ ኢኮኖሚ የ10.3 ዕድገት ማሳየቱን የተለያዩ መረጃዎች ያመለክታሉ።

ይሁን እንጂ ይህ እጅግ አመርቂ የኢኮኖሚ ዕድገት፣ እንዲሁም ሠፊ የመሠረተ- ልማትና የማኅበራዊ አገልግሎቶች መስፋፋት ኢትዮጵያን በዓለም እጅግ ደሀ ከሚባሉት አገራት ተርታ አላወጧትም። የአገሪቱ ኢኮኖሚ በኋላ-ቀር የአመራረት ዘዴ፣ በአየር ንብረት መዛባት እና በተለያዩ መዋቅራዊ ችግሮች በተተበተበው የግብርናው ክፍለ-ኢኮኖሚ ላይ የተንጠለጠለ ሲሆን፤ ክፍለ-ኢኮኖሚው ከግማሽ በላይ የሚሆነውን የአገር ውስጥ ምርት (Gross Domestic Product-GDP)፣ 83% የወጪ ምርትና 80% የስራ ዕድል ይሸፍናል። በአሁኑ ጊዜ የገጠር መሬት እጥረትና መሬት አልባነት በሁሉም የአገሪቱ ክልሎች በከፍተኛ ደረጃ ይስተዋላል።

በተመሳሳይ ሁኔታ በአገር ውስጥ ካፒታልና የውጭ መዋለ-ንዋይን በመሳብ የኢንዱስትሪውን ክፍለ-ኢኮኖሚ ለማሳደግ የተደረገው ጥረት በከፍተኛ ፍጥነት በማደግ የስራ ገበያውን ለሚቀላቀለው ስራ ፈላጊ የህብረተሰብ ክፍል በቂ ስራ ለመስጠት የሚችልበት ደረጃ ላይ ገና አልደረሰም። በዚህ ሳቢያ ስራ አጥነት በከተማም ሆነ በገጠር በከፍተኛ ደረጃ ይስተዋላል። ከዚህ በተጨማሪ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ አንዳንድ ለልማት ተብለው የተወሰዱ ዕርምጃዎች በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች የቅሬታ ምንጭ በመሆን ተቃውሞ አስነስተዋል። ለምሳሌ በከተሞች መስፋፋት፣ በኢንቨስትመንትና በልማት ሰበብ የእርሻ መሬቶቻቸውን የተወሰደባቸው ገበሬዎች የኑሯቸው መሠረት በነበረው መሬት መወሰድና የተሰጣቸው ካሣ አነስተኛ መሆን ለተነሳው የህዝብ ተቃውሞ አንዱ ዋና ምክንያት እንደነበር መጥቀስ ይቻላል።

በፖለቲካው ረገድም አገሪቱን ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ ሲያስተዳድር የቆየው ኢህአዴግ የተለያዩ ገዳቢ ሕጎችን በማውጣት፣ ለተቃዋሚ/ተፎካካሪ ድርጅቶች ማነቆ በመፍጠርና

የፖለቲካ ፉክክር መድረኩን በማጥበብ ሲወነጀል መስማት የተለመደ ነበር። እነዚህ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮች ከፍተኛ ሕዝባዊ ተቃውሞ በማስነሳት በአገሪቱ ከፍተኛ ቀውስ እንዲፈጠር ምክንያት ሆነዋል። የቀውሱ አሳሳቢነት በአስራ ስምንት ወራት ውስጥ ሁለት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እዲታወጅም ምክንያት ሆኗል። ችግሩ ስር ነቀል ዕርምጃ የሚፈልግና በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ብቻ የሚፈታ ባለመሆኑ ገዢው ፓርቲ የተለያዩ ስር ነቀል የፖሊሲ ዕርምጃዎችን ለመውሰድ ተገድዷል። በሒደቱም የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ ስልጣናቸውን ለቅቀው ዶ/ር ዐቢይ አህመድ በቦታቸው ተተክተዋል። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይም ወደስልጣን ከመጡ ጀምሮ የተለያዩ እርምጃዎችን የወሰዱ ሲሆን ቀደም ሲል የተለያዩ የፖለቲካ አመለካከቶች ያሏቸው የፖለቲካ ድርጅቶች ወደአገር ውስጥ ገብተው እንዲንቀሳቀሱ እርምጃ መወሰዱ፣ ከኤርትራ ጋር የሠላም ስምምነት ሒደት መደረጉ፣ እንደ ምርጫ ቦርድና ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመሳሰሉት ተቋሞች ላይ ተቋማዊ ማሻሻያዎች መጀመሩ እና የተለያዩ መብት ገዳቢ የነበሩ ሕጎች ላይ ማሻሻያ መደረጋቸው የለውጡ ዓቢይ ዕርምጃዎች ተደርገው ይጠቀሳሉ።

በአጠቃላይ ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ ምናልባትም ከዚህ ቀደም ባልተለመደ ሁኔታና መጠን በፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ የለውጥ ሒደት ውስጥ ትገኛለች። አገሪቱ ባለፉት ሁለት አስርተ-ዓመታት ያስመዘገበችው ኢኮኖሚያዊ ዕመርታ እንደተጠበቀ ሆኖ በተቃራኒው የመልካም አስተዳደር ዕጦት፣ እየተስፋፋ የመጣው የከተማና የገጠር ስራ አጥነት፣ ፍትኃዊ የሀብት ክፍፍል አለመኖርና የፖለቲካ ምኅዳር መጥበብ የለውጥ ሒደቱ እንዲመጣ ካስገደዱት ምክንያቶች መካከል በዋናነት ይጠቀሳሉ። ይሁን እንጂ ለውጡ ወዴት አቅጣጫና በምን ፍጥነት መጓዝ ይኖርበታል? ምን ምን ጉዳዮችን ማካተት ይገባዋል? እንዲሁም የአገሪቱ የወደፊት ሁኔታስ ምን መምሰል ይኖርበታል? በሚሉ ኃሳቦች ላይ ገና ሙሉ በሙሉ አገራዊ መስማማቶች ላይ ተደርሷል ተብሎ አይገመትም። በመሆኑም የተጀመረው አገራዊ ለውጥ የበለጠ ፍሬያማ እንዲሆን የሁሉም ባለድርሻ አካላት ኃሳቦች የሚንጸባረቁባቸው የጋራ መድረኮች የማዘጋጀትና ውይይት የማካሄድ አስፈላጊነት አያጠያይቅም።

በመሆኑም **ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ** የተለያዩ ባለድርሻ አካላት በወቅታዊ አገራዊ ጉዳዮች ላይ ተገኛኝተው የሚወያዩባቸው፣ የሚመክሩባቸውና አማራጮችን ላይ የሚከራከሩባቸው ሕዝባዊ የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀትና በማካሄድ ለአገራዊ የፖለቲካ ሪፎርሙ መሳካት የበኩሉን ለመወጣት ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል። የውይይት መድረኮቹ ከግንቦት ወር 2011 ጀምሮ እስከ ሕዳር ወር 2012 ዓ.ም ድረስ ባሉት ስድስት ወራት የዘለቁ ሲሆን ውይይቶቹም በሦስት አቢይ ክፍሎች የተከፈሉ ነበሩ። እነዚህም 1) ፖለቲካ፣ ሕገ መንግስትና ሕገ-መንግስታዊ ተቋማት ግንባታ፣ 2) አገራዊ ኢኮኖሚ ፖሊሲ እና 3) የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ነበሩ። በእያንዳንዱ ዓቢይ ርዕስ ስር ሁለት ሁለት የውይይት መድረኮች ተካሂደዋል። በእያንዳንዱ መድረክም በመስኩ የጠለቀ ዕውቀትና የስራ ልምድ ያላቸው ሁለት ሁለት ምሁራን የውይይት መነሻ ጽሑፎች እንዲያቀርቡ ተድርጓል።

አቅም በፈቀደ መጠን የሚቀርቡት ጽሑፎች የሁሉንም ባለድርሻ አካላት አቋሞች የሚያንጸባርቁ እንዲሆኑ ጥረት ተደርጓል፡፡

በመድረኮቹ የቀረቡት ጽሑፎችም ከመወያያ አዳራሽ ባሻገር በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች ለሕብረተሰቡ እንዲደርሱ ጥረት ተደርጓል፡፡ በተለያዩ የኤሌክትሮኒክና ህትመት ሚዲያዎች እና ማኅበራዊ ሚዲያዎች በተከታታይ ከሚቀርበው በተጨማሪ ጥናታዊ ጽሑፎቹ አርትዖት ተደርጎባቸው በሕትመት በየዐቢይ ርዕሶቹ ዘርፍ በሦስት ተከፍለው እንዲቀርቡ ታቅዶ የመጀመሪያው ዐቢይ ርዕስ በሆነው **ፖለቲካ፣ ሕገ መንግስትና ሕገ-መንግስታዊ ተቋማት** ግንባታ ስር የቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፎች በቅፅ አንድ ታትመው ለሕዝብ መቅረባቸው ይታወሳል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ በዚህ ቅፅ ሁለት **አገራዊ ኢኮኖሚ ፖሊሲ** በሚል ዓብይ ርዕስ ስር ሁለት የውይይት መድረኮች ተካሂደዋል፡፡ ‹‹**የማክሮ-ኢኮኖሚ ፖሊሲ እና በኢኮኖሚ ውስጥ የመንግስት ሚና**›› በሚል ርዕስ ነሐሴ 2 ቀን 2011 በተካሄደው መድረክ በፕሮፌሰር ዓለማየሁ ገዳና በዶ/ር ቴዎድሮስ መኮንን የቀረቡት ጥናታዊ ፅሑፎች በዚህ ቅፅ ውስጥ ተካትተዋል፡፡ ፕሮፌሰር ዓለማየሁ ‹‹**የኢትዮጵያ ዐብይ-ኢኮኖሚ (ማክሮ-ኢኮኖሚ) ሁኔታና መንግስት ወደፊት በኢኮኖሚው ውስጥ ሊኖረው የሚገባ ሚና**›› በሚለው ጽሁፋቸው መንግስት ባለፉት ሁለት አስርተ-ዓመታት በልማታዊ መንግስት ቅኝት ጥሩ የሚባል የኢኮኖሚ ዕድገት ማስመዝገቡን ጠቅሰው፤ ይሁን እንጂ ይህ ዕድገትና ዕድገቱ የመጣበት ሒደት አሁን ለታየው የዐብይ ኢኮኖሚ (Macro economy) መናጋት ዋና ሚና መጫወቱን ይተነትናሉ፡፡ መንግስት በመሠረተ-ልማት እና በከፍተኛ ፕሮጀክቶች (Mega Projects) ላይ ከፍተኛ መዋዕለ-ንዋይ ያፈሰሰ ሲሆን ይህን መዋዕለ-ንዋይ ያሰባሰበበት፣ ጥቅም ላይ ያዋለበትና ጉድለቱን ለመሸፈን የተጠቀመባቸው መንገዶች አገሪቱን ዛሬ ለምናየው ከፍተኛ የዐብይ ኢኮኖሚ መናጋት፤ ለዋጋ ንረት፣ ለውጭ ምንዛሬ ዕጥረትና ለዕዳ ጫና እንደዳረጋት ያመለክታሉ፡፡ መንግስት በጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የሄደውን የአገሪቱን የመዋዕለ-ንዋይ ፍላጎት ክፍተት ለሟሟት የውጭ ብድርን እና ገንዘብ ማተምን እንደ አይነተኛ መፍትሔ መውሰዱን በመጥቀስ፤ በዚህ ሁኔታ ሀብት በማሰባሰብ የተተገበሩት ፕሮጀክቶችም በዕቅድና በሙያዊ አመራር ዕጦት፣ በፖለቲካዊ ወገንተኝነት እና በሌብነት የታሰበላቸው ደረጃ ላይ ሳይደርሱ ብድር የመክፈያ ጊዜያቸው መድረሱን ያብራራሉ፡፡ መንግስት እከተላለሁ ይለው የነበረው የልማታዊ መንግስት ፍልስፍና በጠራ ንድፈ-ኃሳባዊ መሠረት ላይ ያልተመሰረተ፣ የሰለጠነ የሰው ሀይልና ብቁ ቢሮክራዊ የሌሉበት፣ በፖለቲካ ወገንተኝነት ላይ ተመስርቶ ግለሰቦች በኃላፊነት የሚቀመጡበት ስለነበር ከውድቀት ማምለጥ አለመቻሉን አስምረውበታል፡፡ በመጨረሻም አሁን የሚታየውን እጅግ አስፈሪ የዐቢይ ኢኮኖሚ መናጋት ለማስተካከል እና የኑሮ ውድነትንና የገንዘብ ግሽበትን ለማቃለል መንግስት ሊወስዳቸው ይገባሉ ያሏቸውን እርምጃዎች በምክረ-ኃሳብነት አቅርበዋል፡፡ ምዕራባውያንና የአለም የገንዘብ ተቋም ‹‹እጃችሁን ከኢኮኖሚ ውስጥ አውጡ›› በማለት ከሚሰጡት ምክር በተቃራኒ መንግስት

በዕውቀት ላይ በተመሰረተና ተጠያቂነት በሰፈነበት ሁኔታ በኢኮኖሚ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ እንዳለበት በምክረ-ኃሳባቸው ያሳስባሉ፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ ዶ/ር ቴዎድሮስ መኮንን ‹‹**የኢትዮጵያ የማክሮ ኢኮኖሚ ሚዛን መዛባት እና ቀጣይ አቅጣጫዎች**›› በሚለው ፅሁፋቸው መንግስት ከ1983 ጀምሮ ይከተለው የነበረውን የኢኮኖሚ መርሆዎች ከተነተኑ በኋላ ከ1997 በኋላ ግን የመንግስት የዕድገት መርህ ተቀይሮ ለኢትዮጵያ ፈጣን ዕድገት የሚያዋጣው የልማታዊ መንግስት መርህ መሆኑን አቋም በማውጣት ‹‹የልማታዊ መንግስት ፅንሰ-ሀሳብን›› በይፋ መከተል መጀመሩን ያብራራሉ፡፡ ባለፉት 15 ዓመታት አገሪቱ ከፍተኛና ፈጣን ዕድገት ለማስመዝገብ መቻልዋን ጠቅሰው፤ ይሁን እንጂ የዚህ ዕድገት ዓይነተኛ መንስዔ በፍላጎት መጨመር ላይ የተመሰረተና በተለይም በመንግስት ኢንቨስትመንት የሚመራ እንደነበር ያትታሉ፡፡ ለዚህ ኢንቨስትመንት የዋለው መዋዕለ-ንዋይም ከቁጠባ፣ የታፈነ የፋይናንስ ስርዓትን በመዘርጋት ፈሰስ ከተደረገ ብድር፣ ከብሔራዊ ባንክ የበጀት ድጎማ እና ከውጭ ብድር የተገኘ እንደነበር በመዘርዘር ይሁን እንጂ መንግስት እነዚህን ምንጮች አላግባብ በመጠቀሙ ዛሬ የተከሰተውን የማክሮ-ኢኮኖሚ መዛባት ማስከተሉን ያሰምሩበታል፡፡ በመሆኑም ይህንን መዛባት ለማስተካከል የገንዘብ መዋቅሮች ላይ ማሻሻያ ማድረግንና ልቅ የገንዘብ ልቀት ላይ እርምት መውሰድን ጨምሮ መንግስት በአስቸኳይ ሊወስዳቸው ይገባቸዋል ያሏቸውን እርምጃዎች በምክረ-ኃሳብ አቅርበዋል፡፡

የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ወደግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ማዛወርና የኢኮኖሚ መዋቅር ማሻሻያ ላይ ትኩረቱን ያደረገው መስከረም 08 ቀን 2012 በተካሄደው ሁለተኛው የውይይት መድረክ ላይ ‹‹**የመንግስት የልማት ድርጅቶች ማሻሻያ**›› በሚል ርዕስ ጥናታዊ ጽሑፋቸውን ያቀረቡት ዶ/ር ብሩክ ታዬ መንግስት ‹‹የልማታዊ መንግስት›› ሞዴልን በመከተል ዕድገት ለማምጣት ጥረት ሲያደርግ መቆየቱን አስታውሰው ይሁን እንጂ በዚህ ሞዴል ትግበራ ውስጥ የተለያየዩ ተግዳሮቶች በመኖራቸው በ2010 የመጣው አዲሱ አስተዳደር የሞዴሉን የትኩረት አቅጣጫዎች በመፈተሽ የተለያዩ ማሻሻያዎች (reforms) ማድረግ መጀመሩን ያስረዳሉ፡፡ ከነዚህ መካከል መንግስት የሚያስተዳድራቸውና በተለያዩ ችግሮች የተተበተቡትን የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ወደ ግል የማዘዋወር የመዋቅር ማሻሻያ ፕሮግራም አንዱ መሆኑን ይጠቅሳሉ፡፡ አብዛኞቹ የልማት ድርጅቶች ከፍተኛ የዕዳ ጫና ያለባቸው፣ በበቂ ሁኔታ አትራፊ ያልሆኑና በመንግስት ድጎማ የሚንቀሳቀሱ፤ በአገልግሎት አሰጣጥ ጥራትና የተደራሽነት ችግር ያለባቸው በመሆኑ እንዲሁም በካፒታል እጥረት ምክንያት የመሠረተ-ልማት ዝርጋታና ማስፋፊያ ስራዎች ወጪን ለመሸፈን በጀት ስለሚያንሳቸው አሁን ባሉበት ሁኔታ መቀጠል አለመቻላቸውን ያመለክታሉ፡፡

ኢትዮ ቴሌኮም፣ የስኳር ኮርፖሬሽን፣ የኤሌክትሪክ ሀይል፣ ሎጂስቲክስ፣ ኢንዱስትሪ ፓርክና የኢትዮጵያ ምድር ባቡር ኮርፖሬሽን በማሳያነት በመጥቀስ እነዚህ ድርጅቶች

በማሻሻያ ፕሮግራሙ ውስጥ አሁን ያሉበትን ሁኔታና ደረጃ በመተንተን የፕሮግራሙን ተቋማዊ አደረጃጀትና አተገባበር በዝርዝር ያብራራሉ። በፕሮግራሙ የመንግስት ድርጅቶችን ወደ ግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ ማዛወር ከሽግግሩ የሚገኘው ገንዘብ የፋይናንስ ፍሰቱን በማጠናከር የልማቱን ቀጣይነት ለማረጋገጥ ከማስቻሉና ቀጥተኛ የውጭ ኢንቨስትመንት እንዲጨምር ከማድረጉ በተጨማሪ የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ በአገሪቱ አጠቃላይ ኢኮኖሚ ውስጥ የሚኖረውን ተሳትፎና ድርሻ በማሳደግ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንደሚያስገኝ ያብራራሉ።

በተቃራኒው አቶ ክቡር ገና **‹‹ፕራይቬታይዜሽን በኢትዮጵያ፡- ኢትዮ-ቴሌኮም ለምን ይሸጣል?››** በሚለው ጥናታዊ ጽሑፋቸው የመንግስት የልማት ድርጅቶች ወደ ግል መዛወራቸው ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግበት ይገባል በማለት ይሞግታሉ። የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ወደ ግል የማዛወር ሒደት በ1986 መጀመሩን በማስታወስ በነዚህ ዓመታት ውስጥ 381 የመንግስት የልማት ድርጅቶች ወደ ግል መዞራቸውን ያመለክታሉ። የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ወደ ግል ማዛወርን በመርሕ ደረጃ እንደማይቃወሙና ወደ ግል ቢዞሩ የበለጠ ውጤታማ የሚሆኑ ድርጅቶች እንዳሉ ሁሉ፤ የሕዝብና የመንግስት ስትራቴጂካዊ ሀብቶች የሆኑ ወደ ግል መዞር የሌለባቸው ድርጅቶች እንዳሉ በምሳሌነት ኢትዮ ቴሌኮምን፣ ኢትዮጵያ አየር መንገድንና ኢትዮጵያ መብራት ሀይልን በመጥቀስ ይተነትናሉ።

እነዚህ መሰል ድርጅቶችን ወደ ግል ማዞር እንደተባለው የአግልግሎት ጥራትንና ተደራሽነትን፣ የገበያ ተወዳዳሪነትና ለማስፋፊያ የሚሆን ፋይናንስ አቅርቦትን በራሱ አያረጋግጥም። ይልቁንም እነዚህ መሰል ድርጅቶች በችኮላ ወደ ግል ከማዞር ይልቅ የአስተዳደርና አመራር ነፃነት በመስጠት፣ ከፖለቲካዊ ጣልቃ ግቦነት በማጽዳት፣ ግልፅ ዓላማና ግቦች በመቅረጽ እና የእነዚህን ዓላማዎችና ግቦች ማስፈፀሚያ የሚሆኑ ድርጅታዊ አወቃቀሮችና ባህሎችን በማስፈን ውጤታማ ማድረግ ይቻላል በማለት ይሞግታሉ።

በሚቀጥለው ሦስተኛውና የመጨረሻው ቅፅ **የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ** በሚለው ዐቢይ ርዕስ ስር በተካሄዱት ህዝባዊ የውይይት መድረኮች ላይ የቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፎች ታትመው የሚቀርቡ መሆናቸውን መግለጽ እንወዳለን።

አርታኢዎቹ

# ‹‹የማክሮ-ኢኮኖሚ›› ፖሊሲ እና በኢኮኖሚ ውስጥ የመንግስት ሚና

# የኢትዮጵያ ዐብይ-ኢኮኖሚ (ማክሮ-ኢኮኖሚ) ሁኔታና መንግስት ወደፊት በኢኮኖሚው ውስጥ ሊኖረው የሚገባ ሚና

*ዓለማየሁ ገዳ*

## 1 መግቢያ

ባለፉት ሁለት አስርተ ዓመታት የኢህአዲግ መንግስት በጣም ጥሩ የሚባል የኢኮኖሚ ዕድገት አምጥቷል። ለምሳሌም በመንግስት በኦፊሴል የተሰጠው መረጃ እንደሚያሳየው ከ1992/1993 ዓ.ም እስከ 2009/2010 ዓ.ም አማካይ የኢኮኖሚ ዕድገቱ 8.9 በመቶ ነበር። እስከ 1995/1996 የነበረው ዓመታዊ ዕድገት በጣም አነስተኛና በብርቱ የሚዋዥቅ ስለነበረ፣ እሱን ትተን ከ1996/1997 እስከ 2009/2010 ዓ.ም ድረስ ያለውን ጊዜ ብንመለከት፣ ከአስር ዓመት በላይ ዓመታዊ አማካይ ዕድገቱ 10.4 በመቶ ይሆናል። የሂሳብ ቀመር ተጠቅሜ ስመረምረው ግን፣ ይህንን ዕድገት የተጋነነ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። በኔ ግምት አማካይ ዓመታዊው ዕድገቱ ከ6 በመቶ አይበልጥም። ይህም ቢሆን ከአፍሪካ አማካይ ዕድገት በላይ የሆነና በጣም ጥሩ የሚባል ነው። ሌላው ዕድገቱ ከ6 በመቶ አይበልጥም ነበር ለሚለው ሀሳቤ ደጋፊ ማስረጃም በዚህ ፅሁፍ ወረድ ብዩ የምጠቅሰው አስፈሪ የድህነትና የስራ-አጥነት መጠን ነው። መንግስት ይህንን ከፍ ያለ ዕድገት ያስመዘገበው ከፍተኛ መዋዕለ-ንዋይ በኢኮኖሚው ላይ በማፍሰስ ነው። ይህ አካሄዱና የልማት ወጪ አሸፋፈኑ ግን ለዐብይ-ኢኮኖሚው መናጋት ዳርጎታል። ስለሆነም አካሄዱ ልክ ነበር ወይ? የሚጠበቀውንስ ውጤት በሚጠበቀው መጠንና ጥራት አምጥቷል ወይ? የመንግስት ሚናስ በዚህ ሂደት ላይ ምን ነበር? ወደፊትስ ምን መሆን አለበት? የሚሉት ጥያቄዎች ቀጥዬ በአጭሩ የማብራራቸውና የዚህ ጽሁፍ ዋንኛ ዓላማዎች ናቸው።

## 2 የዐብይ ኢኮኖሚው መናጋት

### 2.1 የልማት ወጪ አሸፋፈንና የዐቢይ ኢኮኖሚው መናጋት

የኢትዮጵያ መንግስት ባለፉት አስርተ-ዓመታት ውስጥ በልማታዊ መንግስት ቅኝት በጣም ከፍ ያለ መዋዕለ-ንዋይ በተለይ በመሠረተ ልማት ላይ አውሏል። በዚህም ምክንያት ከላይ ከተጠቀሰው የኢኮኖሚ ዕድገት በተጨማሪ ሌሎችም ጥሩ ውጤቶችን አምጥቷል። ለምሳሌ ያህልም ከባቡርና የመብራት መሠረተ-ልማቶች መስፋፋት በተጨማሪ የዛሬ 10 ዓመት 32 ሺ ኪ.ሜ ብቻ የነበረው የመንገድ ርዝመት ዛሬ 120 ሺ ኪ.ሜ. ደርሷል።

ጥራቱ ደካማ ቢሆንም ትምህርትና የጤና አገልግሎትም በእጅጉ ተስፋፍቷል። በአንድ ሁለት ጥናቶቼ እንዳሳየሁት የመንግስት የገንዘብ አጠፋፍ ከፍተኛ መሠረታዊ ችግሮች ያሉበትና ማምጣት የነበረበትን ከፍ ያለ ውጤት በጥራት ባያመጣም፣ ባለፉት አስር ዓመታት መንግስት እስከ 65 በመቶ የሚደርሰውን ዓመታዊ በጀት ለድሀ-ተኮር ክፍላተ-ኢኮኖሚዎች በጅቷል። የኢህአዴግ መንግስትም ይህ አጠቃላይ አካሄዱን በፍጥነት ከአደጉት የእስያ አገሮች እንደቀዳው እና፣ ስለዚህም እንደነሱ ልማታዊ መንግስት እንደሆነ ይናገራል። ሆኖም ግን የመንግስት አካሄድ ጠለቅ ያለ የልማታዊ መንግስት ኢኮኖሚ ግንባታ ንድፈ-ሀሳባዊ አረዳድ፣ በዚህም ምክንያት ጤናማ የልማት ወጪ አሸፋፈንና መዋቅራዊ ለውጥ የማምጣት አቅም አልነበረውም። ይህም አሁን ለተከሰተው የዐብይ-ኢኮኖሚ መናጋት በተለይ ደግሞ ለዋጋ ንረት፣ የውጪ ምንዛሬ ዕጥረት፣ የዕዳ ጫና፣ ለገንዘብ ፍልሰትና በሌብነት የታጀበ ኢ-ፍትሀዊ የገቢ ክፍፍልና ድህነት አገሪቷን ዳርጓታል። ይህም ከስርዓቱ አፋኝነት ጋር ተደምሮ በመጨረሻ ለታየው አመፅና ጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይን ወደ ስልጣን ላመጣው የአመራር ለውጥና ለለውጡ ምክንያት ሆኗል። እነዚህን ጉዳዮች በዚህ ንዑስ ክፍል ውስጥ ባጭሩ አብራራለሁ።

የዐብይ ኢኮኖሚው መናጋትን በአጭሩ በአሀዝ ለማሳየት፣ ባለፉት አምስት ዓመታት የአገሪቱ መዋዕለ-ንዋይ ከጠቅላላው የአገሪቱ ምርት አንፃር በዓመት በአማካይ ወደ 40 በመቶ መድረሱና፣ ቁጠባው ግን በእኔ ስሌት 10 በመቶ ብቻ መሆኑ (መንግስት ግን እስከ 22 በመቶ ነው ይላል፤ ቢሆንም ዕንኳን እኔ ቀጥዬ የምሰጠውን ድምዳሜዬን አያፋልሰውም) ዋነኛው ጉዳይ ነው። ይህ ማለት ከ20 እስከ 30 በመቶ የቁጠባ ክፍተት (መዋዕለ-ንዋይ ሲቀነስ ቁጠባ) አለ ማለት ነው። ይህን ክፍተት ለመሙላት መንግስት የውጪ ብድርና እና ገንዘብ ማተምን ተጠቅሟል። በዚህም ምክንያት በ2010 ዓ.ም አገሪቱ ያለባት የውጪ ብድር $29 ቢሊዮን ዶላር ሲገመት ከዚህ ውስጥ የቻይና ድርሻ ከ$17 እስከ $19 ቢሊዮን ዶላር እንደሚደርስ ይገመታል። ያገር ውስጡም ብድር የውጪውን ያህል ከፍተኛ ሆኗል። ገንዘብ ማተምን በተመለከተ ባለፉት አስር ዓመታት ብቻ የአገሪቱ የገንዘብ አቅርቦት በ1999 ዓ.ም ከነበረበት 68.2 ቢሊዮን ብር በሚያስፈራ መልኩ በዓመት በ30 በመቶ በማደግ በ2010 ዓ.ም 740.6 ቢሊዮን ብር ደርሷል። ይህ ዓመታዊ የገንዘብ ዕድገት ጤነኛ ከሚባል ዓመታዊ ዕድገት በየዓመቱ ከ4 እስከ 5 እጥፍ የሚሆን ነበር። ይህ ደግሞ በሰዎች እጅ በገፍ እንዲገባ ሲደረግ አብዛኛው ተቀጣሪ ህዝብ በድህነት ምክንያት በብዛት ገቢውን ምግብ-ነክና መሠረታዊ ሸቀጥ ላይ ስለሚያጠፋ፣ አገሪቱ ላይ ያለውን የምግብና የሌሎች መሠረታዊ ሸቀጦች ፍላጎት ደካማ ከሆነው ከአቅርቦቱ በላይ በማሳደግ አገሩን ለዋጋ ንረት ዳርጎታል። በተጨማሪም ብድሩ በአገዛዙ ልሂቃንና በደጋፊ ልሂቃን እጅ መግባቱም ኢ-እኩልነት በማምጣት (በተለይም በአገሪቱ ልሂቃን መካከል)፣ ካፒታል በማፍለስና በተመሳሳይ ድርጊቶች ለሌሎች ሸቀጦች ዋጋ መናርና ለአጠቃላይ ግሽበቱ የበኩሉን አስተዋጽዎ አድርጓል።

በተመሳሳይም የመዋዕለ-ንዋዩን ፍሰት ተከትሎ የአገሪቱ የገቢ-ንግድ (import) ከአገሪቱ የወጪ-ንግድ (export) ከስድስት እጥፍ በላይ ሆኗል (ለማሳያም በ2010 ዓ.ም የገቢ-ንግድ ወደ $18 ቢሊዮን ዶላር ሲሆን የወጪ ንግድ ገቢያችን ግን $3 ቢሊዮን ዶላር ብቻ ነበር)። የአገሪቱ ጠቅላላ ብሔራዊ ብድርም ከአጠቃላይ የአገሪቱ ዓመታዊ ብሔራዊ ምርት ከ60 በመቶ በላይ ደርሷል። በእኔ የምርምር ስራና ግምት፣ የብዙ ዓመታት የአገሪቱ ዓመታዊ አጠቃላይ ዕድገትና በዚህም ምክንያት አጠቃላይ አገራዊ ምርቱ ከላይ እንደገለፅኩት የተጋነነ ስለሚመስለኝ፣ እውነተኛው የዕዳው ጫና ምጣኔ 60 በመቶ ብቻ ሳይሆን፣ አነሰ ቢባል እስከ 70 በመቶ ሊደርስ ይችላል።

በብድር የተካሄዱት ፕሮጀክቶች በዕቅድና ሙያዊ አመራር ማጣት ምክንያት ገና ፍሬ ሳያፈሩ የብድሩ ፍሬና ወለድ መክፈያ ጊዜ መድረሱ ደግሞ ይህን የውጪ ንግድና የክፍያ ሚዛን (Balance of Payment) መዛባትን አባብሶታል። ለማሳያም ያህል በ2010 ዓ.ም የዚህ አይነቱ የዕዳ ክፍያ በዓመት ወደ $1.4 ቢሊዮን ዶላር ደርሶ፣ ከጠቅላላ የዓመቱ የወጪ ንግድ ገቢያችን ግማሽ ሊደርስ ምንም ያህል አልቀረውም። በ2011 ዓ.ም የዕዳ ክፍያው ችግር ተባብሶ በትልቅነቱ ከመንግስት በጀት ውስጥ፣ ከመንገድና ከትምህርት ወጪ በመቀጠል፣ ሶስተኛው ትልቁ አገራዊ ወጪ ሆኗል። ይህ ደግሞ አሁን ለተከሰተው የውጪ ምንዛሬ ችግር፣ የውጪ ምንዛሬ እጥረቱ ላመጣው ግሽበት፣ የዕዳ ጫናና የኢኮኖሚ መቀዛቀዝ ዳርጎናል። በመሆኑም አገሪቱ ዛሬ የብድሩን ፍሬና ወለዱን መክፈል ተስኗት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይን ዕዳውና የአከፋፈሉ ሁኔታ ቀለል እንዲልላቸው፣ በዚያውም ከተገኘ ተጨማሪም ለመጠየቅ፣ አበዳሪዎቻችንን እየዞሩ እንዲለምኑ አድርጓቸዋል። ቻይና ከአበዳሪዎቻችን አንዷና ዋናዋ መሆኗ ይታወቃል። ከቻይና መበደር በራሱ ችግር አልነበረም፤ ነገር ግን እኔ ካካሄድኳቸው ብዙ የቻይናና አፍሪካ ጥናቶች ተነስቼ የተረዳሁት ጉዳይ ቢኖር፣ የቻይናን የአፍሪካ ስትራቴጂን በሚገባ ተረድተንና ኢትዮጵያ በዚያ ላይ ያላትን ሚና ተገንዝበን በዕውቀት ብንጠቀምበት ኖሮ፣ ቻይና ባለፉት አስርተ ዓመታት የሰጠችን የልማት ዕድል በትውልድ አንዴ የሚገኝ ዕድል ነበር። በግብዝነታችን ግን አልተጠቀምንበትም። አሁንም ከተረዳን ዕድሉ ጨርሶ የሞተ አይደለም።

ስለ ዐብይ-ኢኮኖሚው መናጋት ስንተነትንና ስንወያይ ከላይ ከዘረዘርናቸው አመላካቾች ውስጥ ለዋጋ ንረት ወይም ለገንዘብ ግሽበት ("ግሽበት") የምንሰጠው ትኩረት እጅግ በጣም ከፍተኛ መሆን አለበት። ይህም የሚሆነበት ምክንያት ግሽበት ድሀውን በበለጠና በጣም ስለሚጎዳ ብቻ አይደለም። ከዚህ ባልተናነሰ፣ ግሽበት አጠቃላዩን የዐብይ ኢኮኖሚ አናግቶ መዋዕለ-ንዋይን በማኮሰስ ዕድገትና ልማትን ያሰናክላል፣ ብርን አርክሶ ህገ-ወጥ የውጪ ምንዛሬ ገበያን ያስፋፋል፣ ተወዳዳሪነትን ይቀንሳል፣ ከግሽበቱ ለማትረፍ የሚደረጉ ቋሚ ንብረት፣ የተለያዩ ሸቀጦችንና የውጪ ገንዘብ በመያዝ/በማከማቸት እንደ ቁማር አይነት የትንበያ-ቁማር ስራ (speculative business) ያስፋፋል። ከዚህ በተጨማሪ ግሽበት የካፒታል ፍልሰትን ያባብሳል፣ ኢ-ፍትሀዊ የገቢ ክፍፍል ያመጣል አሁን ያለውንም

ያባብሳል፣ ለተወሰነ በብር ለተያዘ የፕሮጀክት ወጪ ተብሎ ከውጪ የሚገባን የካፒታል መጠን (ከግሽበቱ በፊት ከነበረው ጋር ሲነፃፀር) ይቀንሳል፣ የገቢ ሸቀጦችን በማስወደድና የመንግስት በጀትን ከዕቅድ ውጪ በማስጨመር ለሌላ ዙር የግሽበት አዙሪት አገሩን ይዳርጋል፤ በዚህም ግሽበትን የቋሚነት መልክ በመስጠት ልማቱን ራሱን ያጠፋል። ይህ ደግሞ የማህበራዊና ፖለቲካዊ ቀውስ ያመጣል። ስለዚህ ግሽበት አንድ የዐብይ ኢኮኖሚው መናጋት አመላካች ብቻ ሳይሆን ሁሉንም የዚህ አይነት አመላካቾችን በውስጡ አምቆ የያዘ የዐብይ ኢኮኖሚው ሰይጣኖቹ ሁሉ አለቃ ጭምርም ነው። ለዚህም ነው በአገራችን ላለ የግሽበት ችግር ከፍተኛ ትኩረት መሰጠት ያለበት።

## 2.2 የውጭ ንግድና የክፍያ ሚዛን ክፍተትና የወጪ አሸፋፈኑ

ከላይ የጠቀስኩትን ከፍተኛ የሆነና በዓመት እስከ 14 ቢሊዮን ዶላር የደረሰ የንግድ ሚዛን ክፍተት ዋንኛው ምክንያት የተጣራ አገራዊ ቁጠባችን 10 በመቶ ሆኖ የመዋዕለ-ንዋይ ፍሰታችን ግን 40 በመቶ መሆኑና ከዚህ ከፍተኛ የመዋዕለ-ንዋይ ፍሰት ጋር በሚያያዙ ሌሎችም ምክንያቶች ናቸው። ይህንን የንግድ ሚዛን ክፍተት ወጪ የሚሸፈነው ከውጪ በሚመጣ ካፒታል ነው። በንድፈ-ሀሳብ ደረጃ ማንኛውም አይነት የውጪ ካፒታልን (ነፃ ዕርዳታን፣ የእህል ዕርዳታን፣ የውጪ ቀጥተኛ መዋዕለ-ንዋይን፣ብድርንና የውጪ ሀዋላን) የልማት ጠቀሜታ ለመተንተን ጥልቁ መመዘኛ "ዕርዳታ፣ ብድርም ሆነ የውጪ መዋዕለ-ንዋይ ሊመዘን የሚገባው አገሪቱ በወጠነችው የልማት ዐውድ ውስጥ መሆን አለበት" በሚለው ሀሳብ መሠረት ነው። የውጪ ካፒታሉም የመጨረሻ ውጤቱ የሚለካው "በረዥም ጊዜ ሲታይ፣ አንደኛ የዚህ አይነት የውጪ ካፒታል ፍላጎትን በማጥፋቱና፣ ሁለተኛ የውጪው ክፍለ-ኢኮኖሚ ለዕድገት ማነቆ የመሆኑን ነገር በማስቀረቱ ነው"። የዚህ አይነት ትንተናና ምዘና ግን አጠቃላይ ዕቅድ መንደፍን እንደ ቅድመ-ሁኔታ ይጠይቃል።

ይህንን ሀሳብ ከኢትዮጵያ ሁኔታ አንፃር ለማየት የመጀመርያው ነጥብ አገሪቱ በምን ያህል መጠን በእንደዚህ አይነቱ ካፒታል ላይ ጥገኛ መሆኗን መገንዘብ ነው። በአማካይ በዓመት ወደ ውጪ $3 ቢሊዮን ዶላር ብቻ ሸቀጥ ሸጦ በዚያው ዓመት በ$18 ቢሊዮን ዶላር ከውጪ ሸቀጥ የሚገዛ አገር (የሚገዙት ሸቀጦች ደግሞ እስከ 70 በመቶ የሚሆኑት በዓመት ከ$2 ቢሊዮን ዶላር በላይ እንደሚወስደው እንደ ነዳጅ አይነት መሠረታዊና የልማት ማካሄጃ ስትራቴጂካዊ ሸቀጦች መሆናቸው ሲታወቅ)፣ የ$15 ቢሊዮን ዶላር የውጪ ንግድ ክፍተቱን ለመዝጋት እርዳታ፣ ብድርና የውጪ ሀዋላ ባይኖር፣ ኢኮኖሚው ተንኮታኩቶ አገሩ ማህበራዊ ቀውስ ውስጥ እንደሚገባ ማወቅ ነቢይነትን አይጠይቅም። ኢትዮጵያም ባለፉት 10 ዓመታትና ዛሬም ያለችበት የውጪ ክፍለ-ኢኮኖሚ ሁኔታ ይህ ነው።

ይህንን ክፍተት በየዓመቱ የምንሸፍነው በአማካይ $3 ቢሊዮን ዶላር የሚሆነውን ዕርዳታ በሚባለው፣ ነገር ግን ትንሽ ስጦታ በተቀላቀለበት ብድር ነው፤ ባለፉት ሦስት ዓመታት

ደግሞ በአማካይ በዓመት እስከ $3 ቢሊዮን የሚደርስ ዶላር በውጪ መዋዕለ-ንዋይ መልክ ስለሚገባና በአማካይ በየዓመቱ ወደ $4 ቢሊዮን ዶላር የሚደርሰ ገንዘብ ደግሞ ትውልደ-ኢትዮጵያውያን ዘመዶቻችን ከውጪ ሀገራት ስለሚልኩልን፣ እነዚህ የውጪ ምንዛሬ ምንጮችም ሌሎች ይህንን ክፍተት ለመሙላት የምንጠቀምባቸው ገንዘቦች ናቸው። ከዚህ የቀረውን ክፍተት ደግሞ በሌላ ብድር ነው የምንሸፍነው። ይህ የተዛባ የንግድና የክፍያ ሚዛን ለብዙ ዓመታት መቀጠሉና መዋቅራዊ መልክ መያዙ (የአካላችን ክፍል መምሰሉ) ለሁለት መሠረታዊ ችግሮች አገሪቱን ዳርጓታል።

አንደኛ፣ ደሞዙ በወር 3,000 ብር ለሆነ ሰው በተደጋጋሚና ለብዙ ዓመታት በየወሩ 18,000 ብር በልመናም ይሁን በብድር ማጥፋት ጤነኛና ዘላቂ እንዳልሆነ ሁሉ፣ ተመሳሳይ የሆነው የኛም አገር ሁኔታ ጤነኛና ዘላቂ አይደለምና የግድ ቆም ተብሎ "ከዚህ ነገር እንዴትና መቼ ልውጣ?" ተብሎ መታሰብ ያለበት ጉዳይ ነው። መንግስት ግን ቢያንስ ላለፉት 10 ዓመታት ይህን አላደረገውም - አንድ ሁለቴ በዓለም-ባንክ ምክር የሞከራቸው መፍትሔ ናቸው የተባሉ ገንዘብ-ነክ ፖሊሲዎች (ብርን ማርከስ/devaluation) ውጤት እንዳላመጡ መንግስት ራሱ በ2011 ዓ.ም ለፓርላም ባቀረበው ሪፖርቱ ላይ አምኗል። (ይህ ገንዘብ-ነክ ፖሊሲ ግሽበት እንጂ የወጪ ንግድ ዕድገት አያመጣም፣ የንግድና የክፍያ ሚዛን መዛባቱንም አይፈውስም ብዬ በተደጋጋሚ ብፅፍም፣ በመገናኛ ብዙኃን ብናገርም የሚሰማ መንግስት አልነበረም፣ ወይም ደግሞ ቢሰማም ተቃራኒውን ይመክር የነበረው የአበዳሪው የዓለም-ባንክና የምዕራብ አገሮች ተፅዕኖና ጉልበት ከባድ ነበር ማለት ነው)። ለዚህ መፍትሔ ተብሎ የተሞከረው የገንዘብ-ነክ ፖሊሲው ውድቀት ምክንያት ደግሞ የውጪ ንግድና የክፍያ ሚዛን መዛባቱ ችግር መዋቅራዊ እንጂ ገንዘብ-ነክ አለመሆኑና፣ ለመዋቅራዊ ችግር ደግሞ መፍትሔው መዋቅራዊ ፖሊሲ እንጂ ገንዘብ-ነክ ፖሊሲ ባለመሆኑ ነው።[1]

ሁለተኛ፣ ይህንን ያህል በዕርዳታና በብድር ላይ ጥገኛ የሆነ አገር በአበዳሪና ለጋሽ አገራት የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና የርዕዮተ-ዓለም ጥቅም መታገቱ የማይቀር ነው። ለዚህም

[1] ከኢትዮጵያ የውጪ ንግድ አንፃር የመዋቅራዊና ገንዘብ-ነክ ፖሊሲዎች ልዩነታቸው ምንድነው የሚለውን ጥያቄ በምሳሌ ላስረዳ፡፡ የብር ምንዛሬ ከረከሰ ወደ ውጪ ሸቀጥ ላኪዎች በብር ለአንድ ዶላር የሚያገኙት ምንዛሪና በዚያውም ገቢያቸው ትልቅ ስለሚሆን፣ ይህ አበረታትቷቸው ወደ ውጪ የሚልኩትን ምርት በመጨመር የውጪ ምንዛሬ ችግሩ ይፈታል የሚለው የዓለም ባንክና የምዕራብ አገሮች ምክር የገንዘብ-ነክ ፖሊሲ ነው፡፡ምክንያቱም የገንዘብ ምንዛሬውን መለወጥ እንጂ ሌላ የሚደረግ ነገር የለም፡፡ በአንፃሩም ለምሳሌ እኔ ባደረግኩት ጥናት ከመቶ በላይ ወደ ውጪ ሸቀጥ ላኪዎችን "በስራችሁ ላይ የሚያጋጥሟችሁ ዋና ዋና ችግሮች ምን ምን ናቸው?" ብዬ ስጠይቅ የሰጡኝ ዋንኛ መልስ፡ መሬት ማጣት፣ ብድር ማጣት፤ የጉምሩክ ውጣ ውረድ፣ የመሠረተ-ልማት በተለይም የመብራት የወደብና ትራንስፖርት ችግርና ጉቦ ናቸው፡፡ እነዚህ ከማምረትና ከአቅረቦት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች መዋቅራዊ ችግሮች (የስራ ማነቆዎች) የምንላቸው ናቸው፡፡ አንድም ሰው ዶላር በብር ሲመነዘር ብር አለመርከሱ የሚል ምላሽ አልሰጠኝም፡፡ እነዚህን እኔ ያገኘኋቸው ችግሮች ብርን በማርከስ አይፈቱም፤ ችግሩን ለመፍታት የሚደረጉ ፖለሲዎችም ገንዘብ-ነክ ፖሊሲ ሳይሆኑ መዋቅራዊ ፖሊሲ ወይም መዋቅራዊ ችግሮችን ለመፍታት የታለሙ ፖሊሲዎች ይባላሉ፡፡

ይመስላል የአዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ መንግስት ትላልቅና ስትራቴጂካዊ የሆኑትን የመንግስት ድርጅቶችን በጥድፊያ የመሸጥ ፖሊሲ ያወጀው፤ ለዚህም ነው ስለ አገሪቱ ኢኮኖሚና የልማት ታሪክ የጠለቀ ዕውቀት በሌላቸው የምዕራብ አገሮች ተወካይ በሆኑት በዓለም-አቀፍ የገንዘብ ድርጅቶች አማካሪዎችና በእነርሱም ወጪ በተቀጠሩና የእነርሱን ርዕዮትና ጥቅም አድናቂ ኢትዮጵያውያን ሠራተኞችና አማካሪዎች የተከበበው (እነዚህን ኢትዮጵያውያን ዓለም-አቀፍ የገንዘብ ድርጅቶቹና ደጋፊ ጋዜጦቻቸው "በማዳነቅ" "ቴክኖክራቶች" ማለት ጀምረዋቸዋል)። በሌላው ጽንፍም ዋነኛ አበዳሪያችንና የምዕራብ አገሮች የቀጠናውን ዓለም-አቀፍ ተገዳዳሪዋ ቻይና ወደፊት የምትወስደውን ፖሊሲ ማወቅ ባይቻልም፣ የመንግስትን አካሄድ አይታ ምን ልታደርግ እንደምትችል መገመት ግን ይቻላል። ዋናው ቁም ነገር ግን ጉዳዩ አሁን ካሉትም ሆነ ወደፊት ከሚመጡት ጠቅላይ ሚኒስትሮች ሰብዕና፣ ችሎታና ርዕዮተ-ዓለም ጋር ብቻ አለመያያዙ ነው። ይህም ማለት አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትርም እንኳ ሄደው ሌላ ቢመጣ የውጪ ኢኮኖሚው ሁኔታና አወቃቀር በዚህ መልክ እስከ ቀጠለና መንግስትም ተገዳዳሪ ለጋሾችን በጥበብ በመያዝ ለብሔራዊ ጥቅም ወይም ለጋራ ጥቅም እስካልተጠቀመባቸው ድረስ፣ መንግስትና መሪው እንደ ፖለቲካ ቁመናቸው ሁኔታ በለጋሾችና አበዳሪዎች ጥቅም መታገታቸውና የፖሊሲ ሉዐላዊነታቸውን ማጣታቸው ሁሌም አይቀሬ ነው።

## 2.3 የጠራ የንድፈ-ሀሳብ መሠረት የሌለው "ልማታዊ መንግስት"

ከልማት ወጪ አሸፋፈን ችግሩ በተጓዳኝ ያለፈው የኢህአዲግ መንግስት ለስኬታማ ልማታዊ መንግስትነት ከሚያስፈልጉ ቁልፍ ነገሮች (ለምሳሌም በዕውቀት ላይ የተመሰረተ የሰው-ሀይል፣ ዝርዝሩን ዝቅ ብሎ ተመልክቷል) በተጨማሪ የጠራ የልማታዊ መንግስት ንድፈ-ሀሳብና ከእርሱም ተፈልቅቀው የወጡ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን ቢከተል ኖሮ አሁን የገባንበት የኢኮኖሚና የፖለቲካ ችግር ውስጥ በዚህ መጠን ባልገባን ነበር። በታዳጊ አገሮች ፈጣን የኢንዱስትሪ ልማት በማምጣት ለሥራ-አጥነት (ለግልጹም ሆነ ለሽፍንፍኑ፣ open or disguised unemployment) ዘላቂ መፍትሔ መስጠትና ድህነትን መቀነስ ዋነኛ ተግባር ቢሆንም፤ ይህንን ለማድረግ ከኢንዱስትሪ ልማት በተጓዳኝ አብዮታዊ የሚባል የእርሻ ምርት ዕድገት ማምጣት ዋነኛ ጉዳይ ነው። የኢንዱስትሪ ልማቱ ተሳክቶ የስራ-አጥነቱ ችግር ያለ ዋጋ ንረት ("ግሽበት") እና የዐብይ-ኢኮኖሚው መናጋት በመሠረታዊነት የሚቀረፈው፣ የእርሻ ምርታማነትን በመጨመር ነው። እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ታዳጊ አገሮች ትልቅ መዋዕለ-ንዋይ ሳይፈስ በአጭር ጊዜ ጠቀም ያለ የእርሻ ምርት በሔክታር ሊጨምር የሚችለው ደግሞ ትንንሽ የመስኖ ሥራዎችን በማስፋፋትና የእርሻ ክፍለ-ኢኮኖሚውን በአጠቃላይ፣ የአነስተኛ ማሳ ባለቤት አርሶ አደሮችን እርሻ በተለይ፣ በማዘመን ነው። ስለሆነም ለኢህአዲግ መንግስት ከልማት ወጪ አሸፋፈኑ ጋር የተሳሰረው የልማቱ ዋነኛ ተግዳሮት የእርሻው ክፍለ-ኢኮኖሚ ድክመትና ይህም ከዋጋ ንረትና ከልማት ወጪ አሸፋፈን ችግሮች ጋር መያያዙ ነው።

የኢትየጵያ የመሬት-ስሪትና ተያያዥ ተቋማዊ ችግር፣ ደካማ የሆነው የእርሻ ምርታማነት ሁኔታና፣ በኢንዱስትሪው፣ በአገልግሎቱና በእርሻው ክፍለ-ኢኮኖሚ መካከል በአጠቃላይ፣ ከምግብ ምርት አቅርቦቱ ጋር በተለይ መኖር የነበረበት የዕድገት ጥምርታ ውስንነትና ይህን ተከትሎ የመጣው ግሽበትና የዐብይ-ኢኮኖሚው የመናጋት ሁኔታ፣ የኢህአዲግ መንግስት ዋነኛ ድክመቶች ነበሩ:: አሁንም ቢሆን እነዚህን ክፍላተ-ኢኮኖሚዎች ከሚያይዘው የንድፈ-ሀሳብ እይታና ምርምር የሚገኘው አንዱና ጠቃሚው የፖሊሲ አቅጣጫ፣ እኔም ስለ ኢትዮጵያ የዋጋ ንረትና የኢኮኖሚ ዕድገት በሰራሁት ምርምር የተረዳሁት ነገር፣ የአገሪቱ የመዋዕለ-ንዋይ ዕቅድ ከአገሪቱ የምግብ አቅርቦትና የውጪ ምንዛሬ አቅርቦት ዕቅድ ጋር ተቀናጅቶ፣ ካልስኪ የተባለው የጉዳዩ ምሁር "ተገቢ የሆነ የኢኮኖሚ ዕድገት ምጣኔ" (the warranted rate of economic growth) ያለውን መሻትና መከወን ነው:: "ተገቢ የኢኮኖሚ ዕድገት ምጣኔ" ማለት በዕቅድ ከተያዘውና ድህውን ከማይጎዳው የግሽበት መጠንና የውጪ ምንዛሬ የማፍራት አቅም ጋር የሚሄድ የኢኮኖሚ ዕድገት ምጣኔ ማለት ነው (ይህንንም የምናሰላበት ቀመርና ምስለ-ኢኮኖሚ በልማት ሀቲት በሰፊው የሚታወቅ ጉዳይ ነው)::

በኛም ሀገር የዚህ አይነት ንድፈ-ሀሳባዊ አረዳድና ተያያዥ ፖሊሲ የማጣት ሁኔታ ግብርናውና የዐብይ ኢኮኖሚው መናጋት የተያያዙ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል:: እኔም ከግሽበት ጋር በተያያዘ ለአገራችን የዋጋ ንረት መንስዔ ከሆኑትና በጥናት ካገኘኋቸው ምክንያቶች ውስጥ ዋነኞቹ ከላይ የተጠቀሰው ኢኮኖሚው ሊሸከመው ከሚችለው በላይ ብር ከማተም በተጨማሪ የእርሻው ክፍለ-ኢኮኖሚ (በተለይ የምግብ አቅርቦት) አጠቃላዩ የአገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት በሚጠይቀው መጠን ያለማደጉ ነው:: በዚህ ረገድ መንግስት የዚህ አይነቱን ሀቲት ያለመከተሉ (ወይም ያለማወቁ) ሌላው አመልካች ደግሞ ስንዴና ዘይት በሀገር ውስጥ ለማምረት የፖሊሲ ትኩረትና ማትጊያ ባለመስጠቱ፣ ከውጪ በማስገባት ግሽበቱን ለመቋቋም የሚያጠፋው ከፍ ያለ የውጪ ምንዛሬና የውጪ ንግድ ክፍተቱን የሚየባብሰው ድርጊቱ ነው:: ለምሳሌም ለስንዴና የምግብ ዘይት ለመሳሰሉት ብቻ ባለፉት ሦስት ዓመታት በአማካይ በዓመት ከ$1.2 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ (ከጠቅላላው የወጪ-ንግዳችን ሲሶውን) አውጥቷል:: በተጨማሪም የእኛ አገር ነጋዴዎች ያልተገባ የጠቅላይነት አቅምና (degree of monopoly) ተያይዞ የሚመጣው ዋጋን እንደፈለጉ የመወሰን (price making) ጉልበት እንዲሁም ህዝቡ "ዋጋ ይጨምር ይሆናል" ብሎ የሚያደርገው ግምታዊ-ትንበያ (expectation) በጥናቴ የተገኙ ሌሎች የግሽበት መንስዔዎች ናቸው:: በደምሳሳው ይህ የሚያሳየው ለዓመታት መንግስት በእርሻና እርሻ ባልሆነው ክፍለ-ኢኮኖሚ መካከል አስፈላጊ የሆነውን ሀቲታዊ መስተጋብር መጠበቅና የዐብይ-ኢኮኖሚውን በዕቅድ መምራት አለመቻሉን ነው::

ጠቅለል ብሎ ሲገለፅ፣ በንድፈ-ሀሳብ ደረጃ ልማትን ለማምጣት መዋዕለ-ንዋይ ቁልፍ ሲሆን፣ ይህንን የመዋዕለ-ንዋይ ወጪ ለመሸፈን ቁጠባ (ከአገር ውስጥም ሆነ ከውጪ) አስፈላጊ ቢሆንም ዋናውና ብቸኛው ጉዳይ ግን አይደለም:: ምክንያቱም ቀደም ብለን

እንዳየነው በብድርም፣ ገንዘብ በማተምም ወጪ መሸፈኛው ሊገኝ ይችላል:: ዋናው እና ቁልፉ ጉዳይ ወጪ መሸፈኛ ገንዘቡን ማግኘት ሳይሆን ይህን ልማት ያለ ዋጋ ንረት (ግሽበት) መካሄዱን ማረጋገጥ ነው:: ለዚህ ደግሞ የእርሻውን ክፍለ-ኢኮኖሚ በአጠቃላይ፣ የምግብና መሠረታዊ ዕቃዎችን አቅርቦት በተለይ በተጓዳኝ ማሳደግ ወሳኝ ነው:: ስለሆነም ግብርናን ማዘመን፣ ትንንሽ የመስኖ ሥራዎችን ማስፋፋትና፣ የእርሻና እርሻ ያልሆነውን ክፍለ-ኢኮኖሚዎችን እንዲሁም የዐብይ-ኢኮኖሚውን በዕቅድ መምራት ለአሁኑ የጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ መንግስት ቁልፍ የፖሊሲ አቅጣጫዎች ናቸው:: የበፊቱ ኢህአዲግም አንዱ ችግሩ ሁለቱን ክፍላተ-ኢኮኖሚዎች እንደ ሰልፈኛ አይቷቸው አንዴ እርሻን ላስቀደም ነው (እርሻ-መር)፣ አሁን ደግሞ ኢንዱስትሪን ላስቀድም ነው (ኢንዱስትሪ-መር) ማለቱ ነው:: ጠቅለል ሲደረግም መገንዘብ ያለብን ጉዳይ በፈጣን የልማት ሂደት ወይም ጉዞ ውስጥ የእርሻው ክፍለ-ኢኮኖሚ አመራረት የአቅርቦት ኢ-ቅቡልነት (inelastic supply) እና በኢንዱስትሪው ክፍለ-ኢኮኖሚ የሚከሰተው የጠቅልልነት (ሞኖፖሊ) አዝማሚያ የግሽበት ሥርወ-መሠረታዊ ምክንያቶች መሆናቸውንና ፖሊሲ አውጪዎች ልብ ሊሉት የሚገባ ነገር መሆኑን ነው::

## 3 የኢኮኖሚ ዕድገቱ መዋቅራዊ ለውጥ አለማምጣት

ጠቅለል ባለ መልኩ ሲገለፅ መዋቅራዊ ለውጥ ማለት ደካማ ምርታማነት ካለበት ክፍለ-ኢኮኖሚ ከፍተኛ ምርታማነት ወዳለበት ክፍለ-ኢኮኖሚ መሸጋገር ማለት ነው:: ባጠቃላይም ከእርሻ ወደ ኢንዱስትሪ መሸጋገር ማለት ነው:: ድህነትን ለመቀነስ የኢኮኖሚ ዕድገት ብቻ በቂ አይደለም፤ የመዋቅራዊ ሽግግርም እንጂ:: እንደፈረንጆቹ አቆጣጠር ከ2002 እስከ 2014 ባሉት ዓመታት ውስጥ የአፍሪካ አገሮች በአማካይ ከ5 በመቶ በላይ በማደግ አህጉሪቱ ከዓለም አገሮች ሁሉ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ከ10 ዓመታት በላይ በማስመዝገብ ተደንቃለች:: ይህ የኢኮኖሚ ዕድገት ግን ይህ ነው የሚባል የድህነት ቅነሳ አላመጣም:: በመሆኑም የድህው መጠን (በቀን ከ1.25 አሜሪካን ዶላር በታች የሚያገኘው ህዝብ ብዛት) በ4 ነጥብ ብቻ ቀንሶ በ2002 ከነበረበት 51 በመቶ ዛሬ 47 በመቶ ላይ ቆሟል (ይህ ማለት ከ1.2 ቢሊዮን በላይ ከሚገመተው የአፍሪካ ህዝብ ግማሹ ማለትም 600 ሚሊዮን ገደማው ድሀ ነው ማለት ነው):: ለዚህ ደግሞ ዋናው ምክንያት የአፍሪካ ዕድገት መዋቅራዊ ለውጥ አለማምጣቱና የዕድገቱም ዋንኛ መሠረት በዓለም-አቀፍ ገበያ ላይ አፍሪካውያን የሚሸጧቸው የጥሬ ሸቀጦች ዋጋ መጨመሩ መሆኑ ነው:: በአንፃሩም ዕድገታቸው መዋቅራዊ ለውጥ ያመጣው የምስራቅ ኤስያ ልማታዊ መንግስታት (ለምሳሌም ቻይና፣ ኮሪያ፣ ታይዋን ወዘተ) የድህነታቸውን መጠን በ1981 እ.ኤ.አ ከነበረበት 77 በመቶ በ63 ነጥብ ቀንሰውት በ2008 እ.ኤ.አ 14 በመቶና በ2018 ከ13 በመቶ በታች አድርገውታል:: በተመሳሳይ ወቅት በአፍሪካ ግን የድህው መጠን በ1981 ከነበረበት 163 ሚሊዮን ህዝብ በ1990 ወደ 278 ሚሊዮን አድጎ፣ በ2018 እ.ኤ.አ እንደገና ወደ 413 ሚሊዮን አሻቅቧል:: ይህም ማለት የአፍሪካ ዕድገት እንደ ምስራቅ

ኤስያ አገሮች መዋቅራዊ ለውጥ አምጥቶ ስራ መፍጠርና ድህነትን መቀነስ አልቻለም ማለት ነው።

በኢትዮጵያም የታየው ዕድገት ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች ተመሳሳይና ላለፉት 40 ዓመታት መዋቅራዊ ለውጥ ማምጣት የተሳነው ነበር። ዛሬም ኢንዱስትሪው ከዓመታዊ አገራዊ ምርት ውስጥ ያለው ድርሻ ለ40 ዓመታት ከቆመበት 10 በመቶ ብዙ ፈቀቅ አላለም። በአማካይ ወደ 16.8 በመቶ ትንሽ ፈቀቅ ያለውም ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ ነው። ይህም ቢሆን እንደ ምስራቅ ኤስያ አገሮች የመፈብረክ አቅማችን አድጎ ሳይሆን፣ የግንባታው ንዑስ ክፍለ-ኢኮኖሚ በኢንዱስትሪው ክፍለ-ኢኮኖሚ ስር ስለሚጠቃለልና የእርሱም ዕድገትና ድርሻ በጣም ከፍተኛ ስለሆነ ነው (ለምሳሌም በ2010 ግንባታው በኢንዱስትሪው ክፍለ-ኢኮኖሚ ያለው ድርሻ 70 በመቶ ደርሷል)። ለመዋቅራዊ ለውጥ ወሳኝ የሆነው የተፈበረኩ ምርቶችን የማምረት አቅማችን ምንም ሳያድግ፣ የተፈበረኩ ምርቶች ከጠቅላላው አገራዊ ምርት ውስጥ ያላቸው ድርሻ እንዳለፉት 30ና 40 ዓመታት ዛሬም ከ5 በመቶ በታች ነው። የአገልግሎት ዘርፉ ባለፉት 10 ዓመታት በአንፃራዊነት ቢያድግም፣ ያደገው ከፍተኛ ምርታማነት ያለው የአገልግሎቱ ክፍል ኢኮኖሚ ሳይሆን ደካማው ክፍሉ ነው። ስለሆነም እንደ ዛሬ ሰላሳና አርባ ዓመታት ሁሉ አሁንም 85 በመቶ የሚሆነው ህዝባችን በግብርናው ክፍለ-ኢኮኖሚ ውስጥ ያለና በእርሱም የሚተዳደር ነው። ይህም ለሽፍንፍኑም ሆነ ለግልፁም ስራ-አጥነት መብዛት፤ ከገጠር ወደ ከተማ ለሚደረገው ከፍተኛ ፍልሰትና ለድህነቱ ዋንኛው ምክንያት ነው።

ባጠቃላይ እንደኛ ባሉ ታዳጊ አገሮች ያለው የሥራ-አጥነት ችግር መዋቅራዊና (structural) በአደጉ አገሮች ካለው የሥራ-አጥነት አይነት የተለየ ነው። የችግሩም ዋነኛ ምንጭ የአቅምና የካፒታል ዕቃዎች (የማምረቻ ዕቃዎች) ዕጥረት ነው። ዋናው የልማት ጥያቄም በትንሽ ካፒታል ብዙ የሰው ሀይል የሚቀጥሩ ስልቶችን በመተግበር ሥራ-አጥነትን መቀነስ ይቻላል ወይ? የሚለው ነው። ከልማት ሀቲቶች የምንረዳው፣ ለዚህ ችግር ፈጣን የኢንዱስትሪ ልማት ዋነኛ ፖሊሲ መሆን እንዳለበትና የኢንዱስትሪ ልማቱ ዕድገትም በምርታማነትም በሥራ ዕድል ፈጠራም (ምንም እንኳን ብዙ ጊዜ ሁለቱ በተፃራሪ የሚሄዱ ክስተቶች ቢሆኑም) ላይ የተመሠረተ መሆን እንዳለበት ነው። የኢንዱስትሪ ልማት በማምጣት ለሥራ አጥነት (ለግልፅም ሆነ ለሽፍንፍኑ) ዘላቂ መፍትሔ መስጠት ዋነኛ ተግባር ቢሆንም፤ ይህንን ለማድረግ ከኢንዱስትሪ ልማቱ በተጓዳኝ ቀደም ብለን እንደገለጽነው አብዮታዊ የሚባል የእርሻ ምርት ዕድገት ማምጣትም የዐቢይ-ኢኮኖሚው እንዳይናጋ የሚያስፈልግ ቁልፍ ጉዳይ ነው።

የኢህአዴግም የእስከ አሁኑ ጉዞ የሚያሳየው የዚህ አይነቱን ከፍ ያለ ስራ አጥነት፣ ደካማ የእርሻው ክፍለ-ኢኮኖሚ ምርታማነት፣ ተያይዞ የመጣውን ግሽበትና የዐብይ-ኢኮኖሚው መናጋት ነው። ለአብነትም በአሁኑ ጊዜ በከተማ የወጣት ስራ-አጡ ብዛት እስከ 27 በመቶ መድረስ፣ ከስራ-አጥነትና ድህነት ብዙም የማይለየው ኢ-መደበኛ (informal) ኢኮኖሚ

ውስጥ የሚሳተፈው የሰው ሀይል ከ40 በመቶ በላይ መሆን፣ ሽፍንፍኑ ስራ-አጥነት (መስራት ከሚችሉት በታች የሚሰሩ ሰራተኞች ብዛት) ከ42 እስከ 49.5 በመቶ መሆን፣ የእርሻው ክፍለ-ኢኮኖሚ ምርታማነት ደካማ መሆን (ለምሳሌም ከ2006-2009 ዓ.ም ባሉት ዓመታት በእርሻ የተሰማራው የሰው ሀይል የምርታማነት ዕድገት እንደ ዝናቡ ሁኔታ በጣም የሚዋዥቅና ዓመታዊ አማካይ ዕድገቱም ከህዝብ ዕድገት በታች በመሆን 2.5 በመቶ ብቻ መሆኑ) እና በየቀኑ እየባሰበት የመጣው የኑሮ ውድነት ከአመላካቾቹ ጥቂቶቹ ናቸው (ይህ ጥናታዊ ወረቀት በሚጻፍበት በሰኔ 2011 ዓ.ም በመንግስት በኦፊሴል የተነገረው አጠቃላይ ግሽበት 16 በመቶ ሲሆን የምግብ ሸቀጦች ግሽበት 20 በመቶ ደርሷል፣ ዕውነታው ግን ከዚያም ሊበልጥ ይችላል)።

የአገሪቱ የስራ-አጥ ሁኔታ አሀዝና በየክፍላተ-ኢኮኖሚያችን ያለው የማምረት አቅምና መዋቅራዊ ለውጥ የማጣት ውጤት የሆኑት የድህነት አሀዞችም ይህ መሠረታዊ ችግር መንሰራፋቱን የሚያሳዩ ናቸው። ለምሳሌም መንግስት በአሁኑ ጊዜ ያለው የድሀ ብዛት ከመቶ ሚሊዮን ህዝባችን ውስጥ 22 ሚሊዮን ብቻ ነው፣ ይህንንም የዛሬ 15 ዓመት ከነበረበት 45 ሚሊዮንና የዛሬ 10 ዓመት ከነበረበት 30 ሚሊዮን ህዝብ ብዛት ቁጥሩን በፍጥነት አውርጀው ነው ይላል። ይህንን ግን የሚያሰላው አንድ ሰው በቀን ከ20 ብር (በወር ከ600 ብር) በላይ ከአገኘ በዚህ ምግቡንም ምግብ ያልሆነውን ወጪውንም ሁሉ ሸፍኖ ይኖራልና ድሀ አይደለም ብሎ ነው። የዛሬን የዋጋ ንረት ለሚያውቀው፣ በዚህ ገንዘብ መኖር ከባድ ነው። ይህንን የድህነት ወለል መለኪያ ትተን አንዱን ያውም ትንሹን ዓለም-አቀፍ የድህነት ወለል መለኪያ፣ ለምሳሌም ለአንድ ሰው በቀን 37 ብር ማለትም በወር 1100 ብር (ወይም $1.25 በቀን፣ በ1 ዶላር 29 ብር ተመን ሂሳብ) ብናደርገው፣ የድሀው ብዛት ከመቶ ሚሊዮኑ ህዝባችን 71 ሚሊዮን በላይ ይሆናል። ይህ ደግሞ ከባድ ድህነት ብቻ ሳይሆን አስፈሪም፣ አሳፋሪም ነው። ወደፊት ግጭትና የፖለቲካ አለመረጋጋት ሊያመጣ እንደሚችልም አመላካች ነው።

በሁለተኛ ደረጃ፣ ይህንን ድህነት ለመቀነስ ፈጣንና ከፍተኛ መዋዕለ-ንዋይ ማፍሰስ ይጠይቃል። የግል ክፍለ-ኢኮኖሚያችንም ደካማ ብቻ ሳይሆን በተፈለገው ልክና አይነት ስለማይገኝ፣ መንግስት በኢኮኖሚው ውስጥ ገብቶ ከፍተኛ ሚና መጫወቱ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። ነገር ግን መንግስት ይህን በሚያደርግበት ሂደት፣ በሚቀጥለው ክፍል ጠቅለል አድርጌ ያቀረብኳቸው፣ ከፍተኛ የሆኑ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ተግዳሮቶች ይጋረጡበታል። እነዚህ ተግዳሮቶች የዛሬው የኢትዮጵያ መንግስትም ከፊቱ የተጋረጡበት ጉዳዮች ናቸው።

## 4 የ“ልማታዊ መንግስቱ” ሚናና ችግሩ ምን ነበር?

ከላይ ከዘረዘርነው የልማት ወጪ አሸፋፈን ችግርና የጠራ የንድፈ-ሀሳብ ዕይታ የማጣት ችግር በተጨማሪ በዕውቀትና በባለሙያ ላይ የተመሠረተ ኢኮኖሚ መገንባት አለመቻሉና

የዚህም የፖለቲካ አንድምታ ሌላው ዋነኛ የቀድሞው የኢህዲግ ልማታዊ መንግስት ችግርና ለለውጡም ምክንያት ነበር።

የልማታዊ መንግስት ንድፈ-ሀሳቦች እንደሚያስረዱን በፍጥነት ያደጉት የእስያ ሀገሮች ሁለት ገፅታዎች ነበሯቸው፣ እኗቸውም። አንዱ በመላው አገሩ የሰፈነና ልዕለ-ሀያል ሆኖ የገነነ "የልማት ርዕዮተ-ዓለም" እና መንግስት ከህዝቡ ቅቡልነት ለማግኘት "እያለማሁ" ወይም "ድህነት እየቀነስኩ" ነው ማለቱ ሲሆን፤ ሁለተኛው ይህንን ልማት ለማምጣት በዕውቀት ላይ የተመሠረተ የቴክኒክና የፖለቲካ አቅም፣ በተያያዥም በሙያ የተካነ ቢሮክራሲ (የመንግስት ሰራተኛ) መኖር ናቸው። የኢህአዲግ *"ልማታዊ መንግስት"* በዋነኛነት ርዕዮተ-ዓለሙ እንጂ የሰለጠነና በዕውቀት የሚመራ የሰው ሀይል መሠረት አልነበረውም። ፖለቲካዊ ባህሪውም አፋኝና ኢ-ዲሞክራሲያዊ ብቻ ሳይሆን ይህን በዕውቀት የተካነ የሰው ሀይል ማጣትን የሚያባብስ ነበር።

## 4.1 የኢህአዲግ የፖለቲካና-ኢኮኖሚ ገፅታና የዐብይ-ኢኮኖሚው መናጋት ያለው ትስስር

ከፖለቲካና ኢኮኖሚ ትንተና አንፃር የኢህአዲግ የአፈጣጠሩ ቁመና ቀጣይነት ያለው የልማት ወጪን ለመሸፈንና የተረጋጋ ዐብይ-ኢኮኖሚ ለማምጣት ያልተመቸ እንደሆነ ማየት እንችላለን። የኢህአዲግን ጥንቅርና ለልማት ወጪ የሚሆን ገንዘብ የመሰብሰብ አቅምና ሁኔታን ስንመለከት፤ አንደኛ፣ ከመንግስትና ከገዢው ፓርቲ ጋር የተቆራኙ ግለሰቦችና ድርጅቶች ("ኢንዶውመንት" የሚባሉትን ጨምሮ) ቀረጥ በአግባቡ መክፈል አይፈልጉም፣ ብዙዎቹም ይሳካላቸዋል፤ ከፍተኛ የመንግስት ባንክ ብድርና የፖሊሲ ተጠቃሚዎችም ናቸው (አንዳንዴ ብድሩን መልሰው መክፈል ባይችሉ እንኳን ተመልሰው ብድር ያገኙ ነበር)፣ አትራፊ ስራ ላይም ቅድሚያ ይሰጣቸዋል። ስለዚህ ከነዚህ ወገኖች ለልማት ወጪ መሸፈኛ ማግኘት አይቻልም። ሁለተኛ፣ ፓርቲው ሰፊ ደጋፊዬ ነው የሚለው የእርሻው ክፍለ-ኢኮኖሚ/ገበሬው ላይ ብዙ ቀረጥ መጣል አይፈልግም፤ ለመጣል ቢያስብም ገበሬው በድህነት ምክንያት ብዙ አቅም የለውም (ባለፉት ሦስት ዓመታት የገጠር የመሬት አገልግሎት ግብር ከጠቅላላው የአገሪቱ ዓመታዊ ግብር በአማካይ ከሁለት በመቶ በታች ነው)። ሦስተኛ፣ የመንግስት ድርጅቶች መሠረታዊና አስፈላጊ የሚባሉ ሸቀጦችንና አገልግሎቶችን በርካሽ እንዲያቀርቡ ይጠበቅባቸዋል። ስለሆነም መንግስት በተለይ በመሠረታዊ ዕቃዎች ላይ ለምሳሌም እንደ ዳቦና/ስንዴ፣ ዘይትና ነዳጅ አይነት ሸቀጦች ላይ በየዓመቱ ከፍተኛ ድጎማ ያደርጋል። ለዚህም የሚሆነውን ከፍተኛ ገንዘብ በከፊል የሚያገኘው አትራፊ ከሆኑት ከንግድ ባንክና ከኢትዮጵያ ቴሌኮም ነው፤ ለምሳሌም ያህል በዚህ ዓመት መንግስት ከልማት ድርጅቶቹ ካተረፈው ወደ 45 ቢሊዮን ብር ውስጥ ወደ 60 ከመቶውን ከኢትዮ ቴሌኮም ሲያገኝ ወደ 30 በመቶ የሚሆነውን ደግሞ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ነው ያገኘው (እነዚህን የልማት ድርጅቶች መሸጥ ማለት መንግስት ድህነትን በፍጥነት ለመቀነስ የሚያስፈልገውን ገንዘብና ያለውን አቅሙን

መሸጥ ማለት እንደሆነ ልብ ይሏል):: በከተማ ያለው ብዙው ነጋዴ ደግሞ ከቀረጥ መክፈል ለማምለጥ መታተሩ መገለጫው ነው፣ በተለይ ከገዢው ፓርቲና ከአገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣኖች ጋር በመመሳጠር:: የተቀረው የበዛው የከተማ ሰውም ወይ ስራ የሌለው ነው፣ ቢኖረውም በድህነት ምክንያት መክፈል አይችልም (በ2008 ዓ.ም ከ40 በመቶ የሚበልጠው የከተማው የሰው ሀይል ኢ-መደበኛ በሚባለው እንደ ጉሊት፣ ሊስትሮ፣ ወዘተ አይነት ክፍለ-ኢኮኖሚ ውስጥ የሚገኝ ነው:: ከ70 እስከ 75 በመቶ የሚሆነውና በግልም በመንግስትም ተቀጥሮ የሚሰራው ሰራተኛ ደግሞ የወር ደሞዙ ከ2500 ብር በታች የሆነና በዓለም-አቀፍ የድህነት መመዘኛ ድሀ የሚባል ነው):: ስለሆነም ዘላቂነት ያለው የልማት ወጪ የሚሸፈንበት ገንዘብ ማግኘት በጣም አስቸጋሪ ነው:: በእነዚህ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ገፅታዎች የልማት ወጪን መሸፋኛ/ፋይናንስ/ የማግኘቱ ሁኔታ ይህ ከሆነ፣ "የልማት ወጪዎችን ማን ይሸፍናቸዋል?" የሚለው ጥያቄ መሠረታዊ ጥያቄ ነው:: ይህ ጥያቄ ለአሁኑም ኢህአዴግ (ለጠቅላይ ሚኒስቴር ዐቢይ መንግስትም) አሳሳቢና መታሰብ ያለበት ጥያቄ መሆኑን ልብ ማለት ጥሩ ነው::

ለኢትዮጵያ የልሂቃን አገዛዙ (ለኢህአዲግ) የዚህ ጥያቄ መልሱ በፖለቲካ የማይቀየም፣ ቢቀየምም ብዙ ለውጥ የማያመጣ የሚለው ነው የሚሆነው:: ለዚህ ደግሞ ጥሩው የፖለቲካ አማራጭ ተብሎ በኢህአዲግ የተወሰደው፣ ከላይ በተገለጸው መልክ መሰብሰብ ቀላል ከሆነው የቀረጥ አይነትና የግብር ከፋይ አይነት በተጨማሪ ወደ ብር ማተሙና በየዓመቱ እያሻቀበ ወደሄደው ብድር መሄድ ነው:: ለምሳሌም ባለፉት 3 ዓመታት ለመቅረጥ ቀላል ከሆነው ቀጥተኛ ያልሆነው እንደ የተጨማሪ ዕሴት ዓይነትና ከውጭ ንግድ ዓይነቱ ኢኮኖሚ የሚሰበሰበው ግብር የጠቅላላው የአገሪቱ ዓመታዊ ግብር 60 በመቶ አካባቢ ነው:: ኃላፊነት ተሰምቶት የተረጋጋ ዐብይ-ኢኮኖሚ የሚፈልግ፣ የወደፊት የብድር ጫና የሚያስፈራው፣ ባጭር ሳይሆን በረዥሙ (ትውልድ አሻግሮ) የሚያይ፣ በዕውቀትና በዕቅድ የሚመራ መንግስት በሌለበትና፣ በማንኛውም መንገድ (በማወቅም ይሁን ባለማወቅ) የዛሬ ውሎውን እንጂ የወደፊቱን የአገሪቱን ኢኮኖሚ ሁኔታ ባለማሰብ ስልጣን ላይ መቆየትን ብቻ የሚመርጥ እንደ ኢትዮጵያ መንግስት [1983-2009 ዓ.ም] አይነት አገዛዝ ባለበት አገር፣ የውጪ ብድርና ገንዘብ ማተምም ሁነኛ የልማት ወጪ መሸፈኛ አማራጭ ነው:: ይህም የወጪ አሸፋፈን ሁኔታ፣ ይህንንም ተከትሎ (በተለይም ደግሞ የከሸፈውን የ1997 ዓ.ም ዲሞክራሲያዊ ምርጫ ተከትሎና የሌጋሾች እጅ ማጠርን/እና አለጋገስ መለወጥ/ ተከትሎ) ለተከሰተው ከፍተኛ የዋጋ መናርና ከዚህም ጋር ተያይዞ ለመጣው የዐብይ-ኢኮኖሚው መናጋት አገሪቱን ዳርጓታል::

ሌላው ከዚህ የፖለቲካና የፋይናንስ ሁኔታ ጋር ተያይዞ የመጣው ጉዳይ ደግሞ ሌብነት ነው:: ከሌብነት ጋር የመጣው ሌብነትን የማድነቅ የህብረተሰብ የሞራል ልሽቀትም ሌላው ወደ ልማት ችግር የገባና በአሁኑ ጊዜ በፍጥነት በመጓዝ ላይ ያለ ማህበራዊ ቀውስ ነው:: (አቶ ጠና ደዎ በዚህ ርዕሰ-ጉዳይ ላይ ከ500 ገፅ በላይ በመፃፍ የደከሙበትና የአ.አ ዩኒቨርስቲ ያሳተመውን ግሩም መፅሀፍ ይመልከቱ):: ሌብነት/ሙስና በግሉም፣ በከፊል-

በመንግስትም (የፓርቲ ድርጅቶች)፣ በመንግስት ድርጅቶችም (በተለይ የመከላከያና ብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ቴክኖሎጂ /ሜቴክ/ በሚባለው የጦሩ የልማት ድርጅት) መንሰራፋቱ ሀቅ ነው። ብዙ ጊዜ እንደዚህ አይነቱ የተሰረቀ ገንዘብ የሚጠፋው በመሠረታዊ ዕቃዎች ላይ ሳይሆን በቅንጦት ሸቀጦች ላይ ነው። በኢትዮጵያ ሁኔታ ግን ከዚህ በተጨማሪ፣ ዘራፊዎቹ የከተማ ህንፃ ግንባታና የአገልግሎት ድርጅት ማቋቋም ላይ ገንዘቡን ሲያጠፉት(ለዚህም መረጃዎች አሉ)፣ የተቀጣሪ ሰራተኞች የፍጆታ መጠንና ፍላጎት ስለሚጨመር ግሽበቱን ያባብሰዋል። በተጨማሪም በካፒታል/በሀብት ፍልሰትም (ወደ ውጪ ማሸሽም) ላይ ይውላል። በቅርቡ ከአንዱ ተማሪዬ ጋር ባደረግኩት ጥናትና ትንበያ ኢህአዴግ ወደ ስልጣን ከመጣ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ከአገር የወጣው ገንዘብ ወደ $30 ቢሊዮን ዶላር ወይም አንድ ትሪሊዮን ብር ይጠጋል። ይህም ከ10 ዓመት በላይ ከውጪ ንግዳችን የምናገኘው ገቢ ተደምሮ ወይም ደግሞ ካለፈው 10 ዓመታት የመንግስት በጀት ውስጥ የስድስት ዓመት ተከሉን የአገሪቱ በጀት እንደ ማለት ስለሆነ በጣም ትልቅ ገንዘብ ቢሆንም፣ ይህን ለማወቅ የተጠቀምንበትን የሂሳብ ቀመርና ምስለ-ኢኮኖሚ ስመዝነው፣ አሳንሼ ሳልተነብየው አልቀርም ብዬ አስባለሁ። የተሰረቀው ገንዘብ አጠፋፍም ለዐብይ-ኢኮኖሚው መናጋት፣ ለዕዳ ጫና፣ ለብክነትና ለውጪ ምንዛሬ ዕጥረቱ መባባስና እየተባባሰ ለመጣው ግሽበትና ኢ-እኩልነት (inequality) (በተለይ የልሂቃን ቡድኖች ኢ-እኩልነት፣ horizontal inequality) ምክንያት ሆኗል። ይህ ደግሞ በ2010 ዓ.ም የታየውን በአመፅ የታጀበ የፖለቲካ አለመረጋጋትና የአመራር ለውጥ ማምጣቱ ብዙም አይገርምም።

ይህ የወጪ አሸፋፈን (ፋይናንሲንግ) ችግር በ2010 ዓ.ም የታየውን አይነት መሠረታዊ የፖለቲካ ለውጥ እሰከ 2010 ዓ.ም ድረስ ለምን ማምጣት አልቻለም ነበር? የሚለው ጥያቄ በጣም ጥሩ ጥያቄ ነው። ለዚህ አንዱና ዋነኛው ምክንያት በኢትዮጵያ ሥራ አጦችና የስቃይ ኑሮ የሚገፉት የከተማና የገጠር ድሀ ለፍቶ አደሮች ብዙ ቢሆኑም፣ ተደራጅተው ይህ ነው የሚባል ሥጋትና ተፅዕኖ በአገዛዙ ላይ ስለማያመጡ ነው ልንል እንችላለን። እነዚህን ድሆች አደራጅቶ ፖለቲካዊ ጫና ለማምጣት የሚደረግ ጥረትም (ለምሳሌም ያህል በከሸፈው የ1997ቱ ዲሞክራሲያዊ ምርጫ ማግስት እንደታየው) በፍጥነት በመንግስት ይመታል። በ2010 ግን የኢኮኖሚውና ፖለቲካው ችግር ግዝፈት ከስርዓቱ አፋኝነትና እየተባባሰ ከመጣው ሰብአዊ መብት ጥሰት ጋር ተደማምሮ ከፍተኛ ደረጃ መድረሱ ብቻም ሳይሆን፣ የአይነት ለውጥም አምጥቶ በአገዛዙ ልሂቃን መሀከልም ሰፊ መከፋፈል መፈጠሩ እንደ 1997ቱ አመፅ አገዛዙ አንድ ሆኖ እንዳይመታው፣ ለውጡም አብዮታዊ ከመሆን ይልቅ ጥገናዊና ዝግመታዊ እንዲሆን ያደረገው ይመስላል። ይህም ማለት በየክልላቸው በተነሳ ህዝባዊ አመጽ ታጅቦ፣ በኢህአዴግ አባል የብሔር የልሂቃን ድርጅቶች መሀከል የነበረው የሀይል ሚዛን መለወጥ፣ ለዚህ ለውጥና በዚህ መልክ ለመለወጡ ሌላው ምክንያት ነበር ማለት ነው።

## 4.2 የሰለጠነ የሰው ሀይልና ቢሮክራሲ የሌለው "ልማታዊ መንግስት"

እስካሁን የዘረዘረነውን አይነት የዐብይ ኢኮኖሚ መናጋት ሳያመጣ፣ ጤነኛ የልማት ወጪ አሸፋፈን ተከትሎ ስራ-አጥነትንና ድህነትን በፍጥነት የሚቀንስ ልማት ለማምጣት፣ በዕውቀት ላይ የተመሰረተ የሰውሀይል ያስፈልጋል። ይህ ማለት የልማት ፖሊሲ ምርምር የማያካሄድ፣ ዕቅድ ማዘጋጀትና ማስፈጸም የሚችል ከፍተኛ ዕውቀትና ችሎታ ያለው ቢሮክራሲ (የመንግስት ሰራተኛ) እና ፖሊሲ አውጪ ያስፈልጋል ማለት ነው።

ይህም ማለት ቀደም ብለን እንደገለጽነው እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ታዳጊ አገሮች የልማት ዋነኛ ዓላማ የማምረት አቅምን መገንባትና ስራ-አጥነትንና ድህነትን ማስወገድ ነውና፣ ለዚህ ጉዳይ ተብሎ ትላልቅ የመዋዕለ-ንዋይ ፕሮግራሞች በመንግስትም በግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚም (ምንም እንኳን ደካማ ቢሆንም) መካሄድ አለባቸው ማለት ነው። እንደ እነዚህ ያሉ ፕሮግራሞች ደግሞ የተቀናጀ ዕቅድ ይፈልጋሉ። እንደነዚህ አይነት ፕሮግራሞች ላይ የተቀናጀ ዕቅድ ሳይዙ መግባት ማለት፣ ግዙፍ ብክነት ውስጥ መዘፈቅ ነው (እዚህ ላይ ኢትዮጵያ ውስጥ በአሁኑ ጊዜ የስኳርና የህዳሴውን ግድብ ጨምሮ በብዙ ፕሮጀክቶች ያለውን ብክነት ልብ ይሏል)። ከአንድ ሁለት የዕቅድና አፈጻጸም የምርምር ጥናቶቼ የተረዳሁት፣ የኢህአዲግ መንግስት የ10 ዓመቱ ዕቅድ ከመካከለኛ ጊዜ (ለምሳሌም ከአምስትና እና ከሦስት ዓመት) ዕቅድ ጋር፤ ይህ ደግሞ በተራው ከዓመታዊ በጀት ጋር እንደማይያዝ ነው። በተጨማሪም የየክፍለ-ኢኮኖሚው (ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች) የረዥም ጊዜ ዕቅድ እርስ በርሱና ከአገሪቱ አጠቃላይ ብሔራዊ ዕቅድ፤ እንዲሁም ከዐብይ ኢኮኖሚው ፍኖት ጋር በውልና በአሀዝ ያልተያያዙ ናቸው። ባጠናኋቸው የናሙና ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችም ሙያዊ ዕቅድ ማውጣትና የፕሮጀክቶችና የአዋጪነት ጥናት ለመስራትም ሆነ ለማስፈፀም የሚችል የሰለጠነ የሰው ሀይል የለም። ለዚህም ነው በመጀመሪያው "የዕድገትና የመዋቅራዊ ለውጥ" (ኢህአዲግ ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የሚለው) ዘመን ከተቀመጡትና 18 ከሚሆኑት ዋና ዋና ከሚባሉት አገራዊ ግቦች ውስጥ መንግስት ሊያሳካ የቻለው 25 በመቶውን ብቻ የነበረው። ለዚህም ዋነኛና መሠረታዊው ምክንያቱ በአገር ደረጃም ሆነ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ደረጃ ዕቅድና ፕሮጀክቶችን መንደፍና ማስፈፀም የሚችል የተማረ የሰው ሀይልና ባለሙያ አለመኖሩ ነው። አንዱ ትክክለኛ የሆነ የልማት ሃቲት መልዕክትም "እንኳን ዕቅድ ማጣት፣ በውልና በዕቅድ የተመራ የመዋዕለ-ንዋይ ፍሰትም እንኳ ቢሆን የግሽበት (የዋጋ ንረት) ጫናና የዐቢይ ኢኮኖሚ መናጋት ሊያመጣ ይችላል የሚለው ነው"።

ይህ በዕውቀት የተካነ የሰው ሀይል ችግርም ከአህአዲግ ፖለቲካ ጋር በብርቱ የሚያያዝ ነው። ስለሆነም የኢህአዲግ (የልህቃን) አገዛዝ የፖለቲካ አሰላለፍ ሌላ ያስከተለው መሠረታዊ ነገርና መንግስትን ባለፉት አስርተ-ዓመታት ትክክለኛ ልማታዊ መንግስት እንዳይሆን ያደረገው ቁልፍ ጉዳይ ዕውቀትና ክህሎት ያላቸውን ምሁራን፣ የቴክኒክ ሰዎች፣ የአስተዳደርና የአመራር ባለሙያዎችን ወ.ዘ.ተ ማግለሉም ነው። እንደዚህ አይነት

ከፍተኛ ባለሙያዎች በዕቅድ አወጣጥ፣ በፕሮጀክት አዋጭነት ትንተናና ጥናት፣ በፕሮጀክት አፈጻጸምና ግምገማ ስራ ላይ፣ በገንዘብ-ነክና በመንግስት ወጪና ገቢ ፖሊሲ ላይ እንዳይሰሩ ስለተደረጉና፣ እንደነዚህ አይነት ቦታዎች (ገንዘብ ሚኒስቴር፣ ልማትና ዕቅድ ሚኒስቴር፣ ብሔራዊ ባንክ፣ ኢንዱስትሪ ሚኒስትር፣ የጠቅላይ ሚኒስቴር የኢኮኖሚ አማካሪና ምርምር ቦታዎች የመሳሰሉት) የተያዙት ከሀያ ዓመታት በላይ አገሩን የገዙት የወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር በአደባባይ እንዳሉት "ዕውቀት ባይኖራቸውም የፓርቲ አባልና ደጋፊዎች እስከሆኑ ድረስ እነሱን ነው የምፈልገው" ብለው ባስቀመጧቸው ሰዎች ስለነበረ፣ "ልማታዊ መንግስቱ" በዕውቀት ላይ የተመሰረተ የሰውሀይል መሠረት አልነበረውም። የመንግስት አወቃቀር ደግሞ በብሔር ፌደራሊዝም ላይ የተመሠረተ መሆኑ ደጋፊዎቹና በብድርም፣ በፖሊሲም በሌላም ነገር የሚረዳቸው ስብስቦች በአንደኛ ደረጃ ከብሔሩ (በሁለተኛ ደረጃ ከሌሎች ተባባሪዎች) እንዲሆኑ ግድ ስለሚል፣ ከላይ የጠቀስናቸውን ችግሮች - ኢ-ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍል በሚል በራሱ በኢህአዴግ ውስጥ ባሉ የብሔር ልሂቃን መሀከል በተነሳ ቅራኔ ሳይቀር - አባብሷቸዋል። በመሆኑም በ2010 ለተከሰተው የቀድሞው ኢህአዴግ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ውድቀቱም ሌላኛው ዋነኛ ምክንያት ይህ የዕውቀት ችግርና የፖለቲካና ኢኮኖሚው እንድምታውም ነው።

## 5 ማጠቃለያ፡- የመንግስት ሚና በኢኮኖሚው ውስጥ ምን መሆን አለበት?

ከእስካሁን ትንተናችን እንደተረዳነው የኢትዮጵያ የዐብይ-ኢኮኖሚው መናጋት (የውጪ ንግድና የክፍያ ሚዛን መዛባት፣ የውጪ ምንዛሬ ዕጥረትና የዕዳ ጫናን ጨምሮ) እና የድህነትና የስራ-አጥነት መንሰራፋት ችግሮች መዋቅራዊ እንጂ ገንዘብ-ነክ (financial /monetary) አለመሆናቸውን ነው። ችግሩ መዋቅራዊ ስለሆነ መፍትሔውም መዋቅራዊ እንጂ ገንዘብ-ነክ አለመሆኑንም መረዳት ያስፈልጋል። ይህን ችግር ለመፍታት ገንዘብ-ነክ ፖሊሲዎች፣ ለምሳሌም የብርን አቅም ማርከስ (devaluation) አይነት የስንፍና የሚመስሉ መፍትሔዎች ውጤት አልባ (quick-fix) መሆናቸውን መንግስት ራሱ በቅርቡ በ2011 ለፓርላማ ባቀረበው ሪፖርት ያመነው ጉዳይ ስለሆነ፣ ከገባንበት መዋቅራዊ የዐብይ-ኢኮኖሚ መናጋት ልንወጣ የምንችለው፣ ሌላ ዘርዘር ያለ መዋቅራዊ የመፍትሔ ፖሊሲ በመከተል ነው። ይህም ማለት የማምረት አቅም መፍጠርን ሰው-ሰራሽ (አርቲፊሻል) በሆነ የገንዘብ-ነክ ማቄል (financial trick)፣ ማለትም በብድር በተሸፈነ የመንግስት ወጪ ወይም በበጀት ጉድለት (ብር በማተም) በሚገኝ ገንዘብ በዘላቂነት ማምጣት አይቻልም[2]። የኛም አገር የዛሬው የዐብይ-ኢኮኖሚ መናጋትና በአገሪቱ

---

[2] ይህ ገንዘብ-ነክ ማቄል ያልነው ፖሊሲ በአደጉ አገሮች ግን ይሰራል። ምክንያቱም የእነርሱ ችግር አቅም ማጣት ሳይሆን፣ በውጤታም ፍላጎት መጣት ምክንያት ከአቅም በታች መከወን ነውና። በአሜሪካና በአውሮፓ ታላቁን የ 2008/2009 ዓለም-አቀፍ የኢኮኖሚ ቀውስ ተከትሎ "ማነቃቂያ ጥቅል ዕርዳታ" (ስቲሙለስ ፓኬጅ) በሚል በአሜሪካ፣ ፕሬዘዳንት ኦባማ ፕሬዘደንትነታቸወን በጀመሩበት ወቅት ብቻ ከ700 በሊዮን ዶላር በላይ መንግስት ኢኮኖሚው ላይ ማጥፋቱና የኢኮኖሚ ቀውሱን ችግር መታደጉ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። ይህ ግን መንግስት በኢኮኖሚ ውስጥ መግባት የለበትም ከሚለው ከራሳቸው

የተንሰራፋው ድህነት የዚህ አይነት አካሄድ ውጤት መሆኑን ልብ ልንለው የሚገባ ጉዳይ ነው።

የስራ-ዕድል በመፍጠር ድህነትን ለመቀነስና ለዚያም የሚያስፈልገውን የማምረት አቅም የመፍጠር ምኞትን ለማስፈጸም ግንከአብዮት ያልተናነሰ ጠለቅ ያለ የፖሊሲና ተቋማዊ ማሻሻያ፣ ከዚያም ሲያልፍ ለውጥ ያስፈልጋል። እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ታዳጊ አገሮች ያለውን ከፍተኛ ስራ-አጥነትና ድህነት ለመቀነስ የማምረቻ አቅምን መፍጠር ብቻ ሳይሆን በፍጥነትም ማሳደግና ማስፋፋትም ይጠይቃል። ታዳጊ አገሮች ይህን ለማድረግ ሲነሱ ቢያንስ ሦስት ዋና ዋና ኢኮኖሚያዊ ተግዳሮቶች ይገጥማቸዋል፡ በመጀመሪያ፣ ባላደጉ አገሮች የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ (በተለይ የአገር ተወላጁ) ደካማ ስለሆነ ከፍ ያለ የግል መዋዕለ-ንዋይ ፍሰት ማግኘት በጣም ከባድ ነው። ስለሆነም የግል መዋዕለ-ንዋይ ባልተገኘ ቁጥር የታለመውን ከፍተኛ ዕድገት ለማምጣት የመንግስት መዋዕለ-ንዋይን በመጨመር መንግስት በኢኮኖሚው ውስጥ ንቁ ተሳታፊ መሆን አለበት። በሁለተኛ ደረጃ፣ ታዳጊ አገሮች የማምረቻ መሳሪያዎችን አያመርቱምና ይህንን ከሆነ ቦታ ወይም በሆነ መንገድ ማግኘት አለባቸው። ይህ ደግሞ ከውጪ ንግድና የውጪ ዕዳ ጫና ጋር ይያያዛል። በሦስተኛ ደረጃ፣ ይህ ቢቻል እንኳ፣ የመዋዕለ-ንዋይ ፍሰቱ ሲካሄድና ኢኮኖሚው ሲያድግ የአቅርቦታቸው ሁኔታ ደካማ በሆነው መሠረታዊ ሸቀጦች ላይ፣ በተለይ ደግሞ በምግብ አቅርቦት ላይ፣ ከፍተኛ የፍላጎት ጫና ከዚያ ግሽበት ይመጣል።

መንግስት እነዚህን ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ለመፍታት በሚያደርገው ጥረት ሦስት ፖለቲካዊ ችግሮችም ይገጥሙታል። አንደኛ፣ የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ ደካማና በተፈለገው መጠንና አይነትም ስለማይገኝ፣ መንግስት የመዋዕለ-ንዋዩን መጠንና ጥንቅር ለመወሰን በኢኮኖሚ ውስጥ የመግባቱ፣ ኢኮኖሚውን ማቀዱና የግሉን ክፍለ-ኢኮኖሚ መቆጣጠሩ ከውስጥም ከውጭም (በተለይ ከምዕራብ አገሮችና ዓለም-አቀፍ የገንዘብ ድርጅቶች) የፖለቲካ ችግር ማምጣቱ የማይቀር ጉዳይ ነው። ሁለተኛ፣ በእርሻው ክፍለ-ኢኮኖሚ ያሉ ተቋማዊ ችግሮችን ፈትቶ ከፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገቱ ጋር (ከልማቱ ጋር) የሚሄድና ግሽበት የማያመጣ ዕድገት በእርሻው ክፍለ-ኢኮኖሚው ማምጣትም እንደ የመሬት ይዞታውን የመፈተሽ አይነትና ሌሎችም ተያያዥ ፖለቲካዊ ችግሮች ያመጣል። ሦስተኛ፤ መዋዕለ-ንዋዩን ለማስፋፋት በቀ ቀረጥ በህዝቡ ላይ ባጠቃላይ በተለይ ደግሞ በሀብታሞች ላይ ከመጣሉ ጋር የሚያያዘው ነው። እነዚህ ጉዳዮች የአብዮትን ያህል አስፈሪና ከባድ የፖለቲካ ተግዳሮቶች ናቸው።

በመጨረሻም ከዐብይ-ኢኮኖሚ መናጋቱ ጋር የተያያዘውና በአሁኑ ጊዜ አስቸኳይ መፍትሔ የሚሻው ጉዳይ በብርቱ ቀስፎ የያዘን የውጪ ኢኮኖሚ ሁኔታና በውጪ

---

የምዕራብ አገሮችና ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅቶች ርዕዮተ-ዓለም ከሆነው የኦርቶዶክሱ (የተለመደው) ኢኮኖሚክስ የነፃ ገበያ አስተምህሮት ያፈነገጠ ፖሊሲ መሆኑን ልብ ይሏል።

ካፒታል ላይ (ብድር፣ ዕርዳታ፣ ቀጥተኛ የውጪ መዋዕለ-ንዋይ ፍሰት፣ የውጪ ንግድና የውጪ ሃዋላ) ያለን ከፍተኛ ጥገኝነት ነው። መንግስት ራሱ እንደ መንግስት፣ ይህንን ጉዳይ ገምግሜዋለሁ ወይ? ብሎ ራሱን መጠየቅ አለበት። በእኔ እምነት መንግስት ይህን ጉዳይ ለዓመታት አላደረገም። ታይዋንና ደቡብ ኮሪያ የልማታዊ መንግስት ፖሊሲያቸውን በጀመሩበት ወቅት ይህ አስፈሪ የውጪ ጥገኝነት አጋጥሟቸው ነበር። በጣምም አሳስቧቸውም፣ አስፈርቷቸውም ነበር። ምክንያቱም ልማታቸውን በጀመሩበት አካባቢ የእነዚህ አገሮች ለምሳሌም የኮሪያ እስከ 75 በመቶ የሚሆነው የመዋዕለ-ንዋይ ወጪዋና 70 በመቶ የሆነው የገቢ ንግዷ ወጪ የሚሸፈነው በዕርዳታ፣ በተለይ ደግሞ በአሜሪካ ዕርዳታ ነበር። በተመሳሳይም፣ ይህ የአሜሪካን ዕርዳታ ለታይዋንም ወደ ውጪ ሸቀጥ ልካ ከምታገኘው ገቢ እጥፍ ከውጪ በገቢ-ንግድ መልክ እንድታስገባ ረድቷት ነበር። በ2019 እ.ኤ.አ. (2011 ዓ.ም) በፃፍኩትና ***የአፍሪካ ኢኮኖሚ ቀውስ ታሪካዊ አፈጣጠር፡ ከቅኝ ግዛት እስከ ቻይና*** (The Historical Origins of the African Economic Crisis: From Colonialism to China) ባልኩት መፅሀፍ ላይ በዝርዝር እንደዘገብኩት፣ የኮሪያና የታይዋን መንግስታት በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጪ ያሏቸውን ምሁራን በመሰብሰብና በማወያየት፣ ከዚያም በዕውቀት የተካነ ተመራማሪና ቢሮክራሲ ከተገቢ የማትጊያ ስልት ጋር በመፍጠር፣ እንዴት ከዚህ ጥገኝነት እንደሚወጡ ወጥነውና ከውነው፣ አገሮቻቸውን በፍጥነት ለማልማትና የኢኮኖሚ ነጻነታቸውን ለመቀዳጀት ችለዋል። ኮሪያዎች ይህንን በጀመሩበት በ1960 አካባቢ ዓመታዊ የአገራቸው የነፍስ-ወከፍ ገቢ $100 ዶላር ብቻ ሆኖ ከኢትዮጵያ፣ ከቻድ፣ ከታንዛኒያና ከመሳሰሉት አገሮች የነፍስ-ወከፍ ገቢ ጋር ዕኩል ነበር። ዛሬ የኮሪያ የነፍስ-ወከፍ ገቢ 29ሺ ዶላር ደርሶ አገሪቱ ከበለፀጉ የአውሮፓ አገሮች ተርታ ገብታለች። በዚያን ጊዜ 90 በመቶ ከነበረው የግብርናና የጥሬ ዕቃ የወጪ ንግዷ ሙሉ በሙሉ ተላቅቃ ዛሬ የተፈበረኩ ሸቀጦችን ለዓለም በማቅረብ ከዓለም 5ኛ ደረጃ በመድረስ ከካናዳ፣ ከፈረንሳይ፣ ከጣሊያንና ከእንግሊዝ በላይ ሆናለች። ይህንን ስኬት ያገኙት በዕውቀት የተካነ የሰው ሀይል በመያዝና በመገንባት ነው። የዛሬው የኢትዮጵያ መንግስትም ከእነዚህ አገሮች ልምድና በዚህ ፅሁፍ ከተነሱት ሀሳቦች በመነሳት በአስቸኳይ ሊተገብረው የሚገባ አንገብጋቢ ጉዳይ ነው። እነዚህ አገሮች የዚህ ዓይነት የልማት ፖሊሲ ተመራማሪና ዕቅድ ነዳፊ ቢሮክራሲን (የመንግስት ሰራተኛ) ያገኙት እነደ መና ከሰማይ ወርዶ ሳይሆን፣ ስራዬ ብለው ለፍተው ገንብተውት እንደሆነ የጉዳዩ ዕውቅ ተመራማሪ ኢቫን በ2010 ፅሁፋቸው የነገሩን ጉዳይ ነው። ኢቫን እንደሚሉት ደግሞ የዚህ ዓይነቱን ድንቅ ማክስ ዌበር የተባለው ጀርመናዊ የዚህ ጉዳይ ሊቅ ያሰበውን ዓይነት ቢሮክራሲ (እና የፖሊሲ ተመራማሪ) የመፍጠር ጉዳይ፣ ከሌሎች የነዚህ የኤስያ አገሮች የተለያዩ ጥሩ የልማት ተሞክሮዎች፤ በተለይ በሌሎች ታዳጊ አገሮች ተኮርጆ ወደ ራሳቸው ሊያሸጋግሩት የሚችሉት ጉዳይ ብቻ ሳይሆን፣ በዕድገትና ልማት ላይ የሚያመጣው ውጤትም ታምራዊ የሚባል ነው። የአሁኑ የጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ መንግስትም ይህንን ሳያደርግ ቀርቶ እንደበፊቱ ኢህአዲግ አሁን ባለው የፖሊሲ ተመራማሪ፣ ቢሮክራሲና ቢሮክራሲያዊ መዋቅር አገሪቷን ለማልማት ካሰበ፣

አይንሽታይን እንዳለው ተመሳሳይ ነገር እያደረጉ የተለያየ ውጤት መጠበቅ የዕብደት ብየና ነውና በብርቱ ሊታሰብበት የሚገባ ጉዳይ ነው።

ለማጠቃለል፣ የኢትዮጵያ መንግስት ከላይ ከተጠቀሰው ዕውቀትና ክህሎት ካለው የሰው ሀይል በተጨማሪ በዚህ ፅሁፍ ከተዘረዘሩት የዐቢይ-ኢኮኖሚው ችግሮችና ተያያዥ ፖለቲካዊ ችግሮች እንዴት መውጣት ይችላል? እንደ መንግስትስ ወደፊት ሚናው ምን መሆን አለበት? የሚሉት ጥያቄዎች ከባድና ሰፋ ያለ ምርምርና ውይይት የሚፈልጉ ቢሆንም፣ የሚከተሉትን አመላካቾች በዚህ ፅሁፍ ማጠቃለያ መልክ ማየት ጠቃሚ ነው።

(ሀ) መንግስት፣ ታንዲካ ማከንደዌሬ የተባሉ ዕውቅ አፍሪካዊ ተመራማሪ እንደመከሩት፣ ምዕራባውያንና ዓለም-አቀፍ የገንዘብ ድርጅቶች የአፍሪካን መንግስታት “ከኢኮኖሚው ውስጥ እጃችሁን አውጡና ኢኮኖሚውን የሚቆጣጠር ‘ደካማ የለሊት ዘብ’ (Night watch man) ብቻ ሁኑ” የሚሉትን ምክራቸውን ትቶ፣ ድህነትን በፍጥነት ለመቀነስ ከፍ ያለ አቅም ስለሚያስፈልገው፣ በኢኮኖሚው ውስጥ የሚኖረውን ሚና መቀነስ ሳይሆን በዕውቀት ላይ የተመሠረተና ተዐማኒነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት በማድረግ የበለጠ እያሻሻለ መሄድ ይኖርበታል። (የኢትየጵያ አየር መንገድ በዕውቀት ላይ ለተመሠረተ የመንግስት ድርጅት ጥሩ ምሳሌ ነው)። በተጓዳኝም የግሉንም ክፍለ-ኢኮኖሚ እያጎለበተ መቀጠል አለበት። ከተቻለም ይህን ሀሳብ የፖለቲካ መወዳደሪያ ሳይሆን ብሔራዊ ስምምነት ያለበት አገራዊ ጉዳይ ማድረግ ጥሩ ነው። ይህ የሚያስፈልገው አገር-በቀሉ የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ደካማ ስለሆነ ብቻ ሳይሆን፣ የሚፈለገው የልማት ዓይነት (ድሀ-ተኮር) ግዙፍ መዋዕለ-ንዋይ የሚጠይቅ ብቻ ሳይሆን በአብዛኛው ድሀ-ተኮር የሆነው የልማት መስክ የግሉን ክፍለ-ኢኮኖሚ የሚያማልል ስላልሆነም ጭምር ነው። የአገራችን ህዝብም በኢህአዲግና በትክክለኛው የልማታዊ መንግስት ዕሳቤ መሀከል ግዙፍ ልዩነት እንዳለ ተገንዝቦ፣ ለበፊቱ ኢህአዲግ ያለውን ጥላቻ በልማታዊ መንግስት ሀሳብ ላይ ሊያደርገው አይገባም።

(ለ) ሌብነትን ለማስወገድ፣ ሠብዓዊ መብትን ለማክበር፣ ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍል ለማምጣትና በአጠቃላይ ለልማቱ ቅድመ-ሁኔታ የሆነውን ፖለቲካውን ለማረጋጋት፣ መንግስት ልማታዊ መንግስት ብቻ ሳይሆን የግድ ዲሞክራሲያዊ ልማታዊ መንግስትም መሆን አለበት።

(ሐ) ድህነትን በፍጥነት ለመቀነስ ከዓለም ኢኮኖሚ ከፍተኛ የመዋዕለ-ንዋይ ወጪ መሸፈኛ የሚሆን ሀብት ማሰባሰብ በጣም አስፈላጊ ስለሆነ፣ በለጋሾች ፉክክር ይህ እንዳይቀር በጥበብ መከወንና ፅንፍ የያዘ ርዕዮተ-ዓለም አለመከተል፤ ለምሳሌ በቻይና እና በምዕራብ አገሮች መሀከል ያለውን ፉክክር ከሁለቱ ላንዱ ሳይወግኑ እና ከአህጉራዊ ብሔርተኝነት (ከፓን-አፍሪካን) ውገና ጋር በመቃኘት ፉክክሩን በጥበብ ለብሔራዊ ጥቅም ማዋል።

(መ) ከወጪ አሸፋፈን ችግራችን በዘላቂነት ለመውጣት የአገር ውስጥ ቁጠባን ለማሳደግና ሌሎች ለልማት የሚያስፈልጉንን ሀብት ለማሰባሰብ ቴክኒካዊና ተቋማዊ አቅም መገንባትና ለዚህም ፖለቲካዊ ስምምነት መፍጠር።

(ሠ) ከስኬታማ የምስራቅ እስያ ልማታዊ መንግስታት (ቻይናን ጨምሮ) ትምህርት በመውሰድ፣ የግል ወይም የመንግስት ኢኮኖሚ ከሚል ፅንፍ አስተሳሰብ ወጥቶ ሁለቱም ተመጋጋቢም ተፎካካሪም፤ የመንግስት የልማት ድርጅቶችም በዕውቀት ላይ ተመስርተው እርስ በርሳቸው ተፎካካሪ እንዲሆኑ አድርጎ የቅይጥ-ኢኮኖሚ ተመሳሳይ ሀሳቦች ሊታሰቡባቸው የሚገቡ የፖሊሲ አቅጣጫዎች ናቸው።

## ዋቢ መፃህፍት

*ዓለማየሁ ገዳ* (2012 *ዓ.ም*) *የታዳጊ አገሮች ኢኮኖሚ በሚካኤል ካልስኪ፡ ከኢትዮጵያ ልማታዊ መንግስት የፖሊሲ ትግበራዎችና ተግዳሮቶች* (ትርጉም) አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የኢኮኖሚክስ ትምህርት ክፍል።

Alemayehu Geda (2008), “The Political Economy of Growth in Ethiopia”, in Benno Ndulu, Stephen A. O’connell, Jean_PaulAzam, Robert H.Bates, Augustin K. Fosu, Jan Willem Gunning and Dominique Njinkeu (eds). The Political Economy of Growth in Africa: 1960-2000. Cambridge: Cambridge University Press.

Alemayehu Geda (2018), “The Issue of Minimum Wage and Labour Market Profile in Ethiopia” (Background Study for ILO Country Office for Ethiopia, Djibouti, Eritrea, Addis, Abeba)

Alemayehu Geda (2019), “Macroeconomic Management in Fragile States of Africa”, Journal of Development Economic Review, forthcoming/ also at AERC, at www.AERCAfrica.org

Alemayehu Geda (2019). The Historical Origin of the African Economic Crisis: From Colonialism to China. Newcastle upon Tyne: Cambridge Scholars Publishing.

Alemayehu Geda (forthcoming, 2019), Readings on Ethiopian Economy II: The International Dimension and Problems of Public Spending and Planning (Unprocessed, Department of Economics, AAU)

Alemayehu Geda and Addis Yimer (2015), “Political and Development Imperative of Growth, Poverty and Inequality in Ethiopia in the last Decade (2000-2013), in Desalegne Rahameto et al, eds.

2015. Rethinking Development Strategy in Ethiopia. Addis Abeba: FSS and GTZ.

Alemayehu Geda and Addis Yimer (2016), "Capital Flight and its Determinants: The Case of Ethiopia", Journal of African Development, Vol 28, No S1: 39-49.

Alemayehu Geda and Addis Yimer (2017), 'The Effects of Capital Flight on Growth and Poverty Reduction in Ethiopia, in R. Almas (ed). Routledge book series "Economic Transformation for Poverty Reduction in Africa" Chapter 9, 2017.

Alemayehu Geda and Kibrom Tafere (2011), "The Galloping Inflation in Ethiopia: A Cautionary Note for Aspiring Developmental States" in Alemayehu Geda (2011) Readings on Ethiopian Economy. Addis Abeba: Addis Abeba University Press.

# የኢትዮጵያ የማክሮ ኢኮኖሚ ሚዛን መዛባት እና ቀጣይ አቅጣጫዎች

*ቴዎድሮስ መኮንን*

## 1 የዕድገት መርህ

ኢህአዴግ ስልጣን ይዞ እስከ 1996 ዓ.ም ባሉት ዓመታት ይከተል የነበረው መርህ በተወሰነ መልኩ የገበያ-መር ሆኖ በሶሻሊስት ስርዓት በመንግስት ተይዘው የቆዩ የኢኮኖሚ አውታሮችን ወደ ግል በማዛወርና የገበያ-መር ስርዓቶችን በመገንባት ላይ ያተኮረ ነበር:: ዋናው የኢኮኖሚ ዕድገት ስትራቴጂ ማዕቀፍ የግብርና ልማት-መር ኢንዱስትሪ ዕድገት የሚል ነው:: ይህም የግብርናን ምርታማነት ብናሳድግ በነፍስ-ወከፍ የሚመረተውን የግብርና ምርት ሳንቀንስ የሰው ሀይልን ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ ለማሸጋገር ያስችላል በሚል የተቀረፀ ስትራቴጂ ነው:: በተጨማሪም የግብርና የነፍስ-ወከፍ ገቢ ስለሚያድግ ለኢንዱስትሪ ምርት ገበያ መፍጠር ያስችላል:: የኢንዱስትሪ ግብዓቶችንም ከግብርና ምርቶች ጋር በማያያዝ ሰፊ የዘርፎች ትስስር ይፈጠራል በሚል ፅንሰ-ሀሳብ ላይ የተመረኮዘ ስትራቴጂ ነው:: ስለሆነም የግብርና ምርታማነትን ለመጨመር ብዙ የፖሊሲ ርምጃዎች ሲወሰዱ ነበር:: በተለያዩ ምክንያቶች የግብርና ምርታማነት እንደታሰበለት ሊያድግ አልቻለም:: ከነዚህ ምክንያቶች ውስጥ በነፍስ-ወከፍ ያለው የመሬት ይዞታ ትንሽ መሆን፣ በቂ የግብርና ግብዓት አቅርቦት አለመኖር፣ ኋላ ቀር የአስተራረስ ዘይቤ ሊጠቀሱ ይችላሉ::

ከ1997 ዓ.ም በኋላ የመንግስት የዕድገት መርህ ተቀየረ:: የገበያ-መር ስርዓት ሊያስገኝ የማይችላቸው ነገሮች እንዳሉ በማመንና ፈጣን ዕድገት ሊገኝ የሚችለው መንግስት በኢኮኖሚው ውስጥ ያለውን ተሳትፎ ሲያሳድግ መሆኑን መንግስት መግለፅ ጀመረ:: በመሆኑም ለኢትዮጵያ ፈጣን ዕድገት የሚያዋጣው የልማታዊ መንግስት መርህ መሆኑን መንግስት አቋም አወጣ:: የልማታዊ መንግስት ፅንሰ-ሀሳብ መንግስት በኢኮኖሚው ውስጥ ጎላ ያለ ሚና የሚጫወትበት፣ የተለያዩ መዘውሮችን በመጠቀም የተመረጡ ዘርፎች በፍጥነት እንዲያድጉና ምርታማነታቸውና ተወዳዳሪነታቸው እንዲጨምር ለማድረግ የሚያስችል ብዙ ሀገሮች ለዕድገት የተጠቀሙበት መርህ ነው:: ከሚጠቀምባቸው መዘውሮች መካከል ታሪፍ፣ ድጎማ፣ የመንግስት ወጪ፣ የታክስ ማበረታቻ፣ የገንዘብ ፖሊሲ፣ የውጭ ምንዛሬ ተመንና ዘርፍ-ተኮር ድጋፎች

ይገኙበታል፡፡ በመንግስት የሚቋቋሙ ባንኮችም የፋይናንስ ሀብት ወደ ተፈለገው አቅጣጫ እንዲሄድ ያግዛሉ፡፡ በዚህ መርህ መሠረት ፖለቲካውና ኢኮኖሚው ትስስር በመፍጠርና ለዚህም ሲባል ለየት ያለ ስልጣን ያለውና የልማት ጥረቶችን የሚደግፍ ቢሮክራሲ በማዋቀር ልማትን ማፋጠን ያስፈልጋል የሚል ነው፡፡ በዚህ መርህ ተጠቅመው ካደጉ ሀገራት መካከል ጃፓን፣ ደቡብ ኮሪያ፣ ሲንጋፖርና ሌሎች የሩቅ ምስራቅ ሀገሮችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ እነዚህ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በዚህ መርህ ተጠቅመው ያደጉ ሀገሮች ቢሆኑም፤ አውሮፓ በ16ኛውና በ17ኛው ክፍለ ዘመን፣ አሜሪካ ደግሞ በ19ኛው ክፍለ ዘመን የዚህ መርህ ተጠቃሚዎች እንደነበሩ ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡

በ20ኛው ክፍለ ዘመን በልማታዊ መንግስት መርህ ካደጉ አገራት በስኬት የምትጠቀሰው ጃፓን ስትሆን አገሪቱ በ1941 ዓ.ም ባቋቋመችው የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር (ሚቲ) አማካኝነት የኢኮኖሚውን አቅጣጫ ለመቆጣጠር ችላለች፡፡ በመጀመሪያዎቹ ዓመታት ሚኒስቴሩ ለኢንዱስትሪ የሚያስፈልጉ ሀሳቦችን ሲያመነጭና ስትራቴጂ ሲቀርፅ ቆይቶ በ1946 ዓ.ም የገቢ እቃዎችን በመቆጣጠር ለታሰቡት ዘርፎች ዕድገት የሚያስፈልገውን ቴክኖሎጂ ማስመጣት ጀመረ፡፡ ተያይዞም የጃፓን ልማት ባንክን በማቋቋም መሠረታዊ ኢንዱስትሪዎችን፤ ማለትም የብረታ ብረትና የኃይል ኢንዱስትሪዎችን ለማቋቋም የሚያስችል ብድር መስጠት ጀመረ፡፡ የጃፓኑ ሚቲ በማስፈጸም ብቃቱ በጣም ጠንካራ የነበረና አገሪቱ ውስጥ በተለይም ከቶኪዮ ዩኒቨርስቲ በትምህርት ላቅ ያለ ውጤት ያስመዘገቡ ሰዎች የሚሰሩበትና የሚያስተዳድሩት ተቋም ነበር፡፡ ከጊዜ ወደ ጊዜም በብቃት እየጠነከረ የሄደና እንደ ዕድገት መጠኑ ራሱን እያሻሻለና እየለወጠ የሄደ ተቋም ነው፡፡ ለምሳሌ በ1950ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ እስከ 1960ዎቹ ድረስ ትኩረቱ ትክክለኛውን አቅጣጫ ማመላከት፣ የውጭ ንግድ የሚያስፋፉ ዘርፎችን መፍጠርና ከፍተኛ ቴክኖሎጂን የሚጠቀሙ የፍጆታ ዕቃዎችን ማምረት ላይ ነበር፡፡ በ1970ዎቹ ደግሞ ከፍተኛ የዕድገት ቴክኖሎጂዎችን ማስፋፋት ጀመረ፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ ሁሉ የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ ጠንካራ የነበረውና ሚናው እያደገ እንዲሄድ ተደርጓል፡፡ በ1980ዎቹ ቀጥተኛ የሆነ የመንግስትና የግል ትብብር ያለባቸው ፕሮጀክቶች ተቀርፀው ተተግብረዋል፡፡

ሌላዋ በዚህ መርህ ያደገችው ሀገር ደቡብ ኮሪያ ነች፡፡ ደቡብ ኮሪያም እንደጃፓን የኢኮኖሚ ፕላኒንግ ቦርድ የሚባለውን ተቋም በማቋቋምና ይህ ተቋም ባወጣቸው ባለ አምስት ዓመታት ዕቅዶች ላይ ተመርኩዛ የልማታዊ መንግስትን ዓላማዎች ማስፈጸም ችላለች፡፡ በመጀመሪያዎቹ ሁለት የአምስት ዓመት ዕቅዶች የመንግስትን የማስፈፀም ብቃት ማሳደግና ራስን ማስቻል ላይ ያተኮሩ ነበሩ፡፡ ይህ ከሞላ ጎደል ከተሳካ በኋላ በሶስተኛው የአምስት ዓመት ዕቅድ የገጠር ልማትን፣ የወጪ ንግድ ዕድገትንና የከባድና የኬሚካል ኢንዱስትሪዎች መስፋፋት ላይ ትኩረት አድርገዋል፡፡ በዚህ

የዕድገት ደረጃ ላይ ሆነው በቤተሰብ የሚያዙ ንግዶችን በማበረታታት አሳድገዋቸዋል፡፡ አሁን የደቡብ ኮሪያን ኢኮኖሚ የሚቆጣጠሩት እነዚህ ንግዶች ናቸው፡፡ በኋላም በ1980ዎቹ መጨረሻ ከፍተኛ ቴክኖሎጂ የሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎች ላይ ትኩረት ተደረገ፡፡

ከነዚህ ሁለት ሀገሮች እንደምንማረው ዋና ዋና የልማታዊ መንግስት መገለጫዎች አሉ፡፡ አንደኛ ልማታዊ መንግስት መርህ መንግስት በኢኮኖሚው ውስጥ ያለው ተሳትፎ ጠንካራ የሆነበት የዕድገት መርህ ነው፡፡ ሁለተኛ በልማቱ ውስጥ የመንግስት ተሳትፎ ጠንካራ ቢሆንም ይህ ተሳትፎ የኢኮኖሚ አውታሮችን በባለቤትነትና በይዞታ በመቆጣጠር ሳይሆን የተለያዩ ማትጊያዎችን በመጠቀም ከግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ ጋር በመተባበር ልማትን የሚደግፍበት መርህ ነው፡፡ ሦስተኛ የልማታዊ መንግስትን ዓላማ ለማስፈጸም ብቁና ጠንካራ ተቋም እንደሚያስፈልግ በዚህ መርህ ያደጉ ሀገራት ተሞክሮ በግልፅ ያሳያል፡፡ ይህ ተቋም በተለይ የማስፈፀም ብቃትና የግሉን ዘርፍ መሸለምና መቅጣት የሚያስችል ስልጣን ሊኖረው ይገባል፡፡ በመጨረሻም የልማታዊ መንግስትን መርህ ለማስፈፀም የሚችልና አጋር ሊሆን የሚችል የግል ዘርፍ ያስፈልገዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በቅርብ ጊዜ በደቡብ ኮሪያ የተደረገ ጥናት እንደሚያሳየው ለልማታዊ መንግስት መርህ መሳካት የመንግስት ጥንካሬ ብቻውን በቂ አይደለም፡፡ ለስኬት ከሚያስፈልጉ ነገሮች ውስጥ የመንግስት ማህበራዊ ዝልቀት (state social embedding)፣ አመቺ ዓለም-አቀፍ ሁኔታዎችና የልሂቃን መግባባት (elite cohesion) ያስፈልጋሉ፡፡

ከነዚህ የልማታዊ መንግስት መገለጫዎች ውስጥ ኢትዮጵያ ውስጥ ሲተገበር የነበረው መርህ ምን ያህል ማሳያዎችን ይጋራል ብሎ መጠየቅ አስፈላጊ ነው፡፡ ልክ እንደ ብዙዎቹ የዚህ መርህ ተከታይ ሀገሮች ኢትዮጵያም ቀጥተኛ ያልሆኑ ማትጊያዎችን በመጀመሪያዎቹ ዓመታት ተጠቅማለች፡፡ ለምሳሌ የታክስና የታሪፍ ስርዓቱ ለካፒታል ዕቃዎች ማስገባት ምቹ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ የመንግስት ባንኮችን በመጠቀም የፋይናንስ ሀብት መንግስት ወደ ፈለገባቸው ዘርፎች እንዲተላለፍ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክና የኢትዮጵያ ልማት ባንክን ተጠቅሟል፡፡ የውጭ ምንዛሬ ተመኑን በመወሰን፣ የገንዘብ ፖሊሲውንና የመንግስት ፋይናንስ ፖሊሲውን በመጠቀም አሁንም ገንዘብ ወደ ተፈለገበት አቅጣጫ በአንፃራዊነት ሲታይ ረከስ ባለ ዋጋ እንዲፈስ አድርጓል፡፡ ባንፃሩ ደግሞ የመንግስት የማስፈፀም ብቃት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተዳከመና በብቃት ላይ የተመረኮዘ ቢሮክራሲ በመሆን ፋንታ በፖለቲካ ግንኙነት ላይ ያተኮረ ሲቪል ሰርቪስ እየሆነ መጥቷል፡፡ ይህም ከታች እንደምናነሳው ለሙስናና ብክነት በር ከመክፈቱም በላይ የተሰበሰበው የፋይናንስ ሀብት የተፈለገውን ውጤት እንዳያመጣ እንቅፋት ሆኖበታል፡፡ በተጨማሪም የልማታዊ መንግስት ዓላማዎች ሊያስፈፅም የሚችለውን የግል-ዘርፍ ከጊዜ ወደ ጊዜ ከጨዋታው ውጪ የሚያደርግ እየሆነ መጥቷል፡፡

መንግስት የሚወስደው የገንዘብና የውጭ ምንዛሬ ሀብት ወሰን ስላጣ ለግሉ ዘርፍ መሄድ የሚገባው ሀብት ወደ መንግስት ሄዶ ከማስፈፀም ክፍተቶች ጋር ሲገናኝ ከፍተኛ ውሱንነት አስከትሏል።

ይህ ማለት ግን ይህ መርህ ለኢትዮጵያ ያስገኘው ውጤት የለም ማለት አይደለም። የሚቀጥለው ክፍል ባለፉት 15 ዓመታት በዕድገትና በድህነት ቅነሳ የታየውን ስኬት ይተነትናል።

## 2 ፈጣን ዕድገት እና ድህነት ቅነሳ

ባለፉት 15 ዓመታት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ከፍተኛና ፈጣን ዕድገት ሲያስመዘግብ ቆይቷል። ይህም ከ1996 ዓ ም ጀምሮ እስከ 2009 ዓ ም ባሉት ዓመታት በዓመት በአማካይ 10.6 በመቶ ከዋጋ ነጻ አገራዊ አጠቃላይ ምርት ዕድገት ተመዝግቧል። ከ1990ዎቹ አጋማሽ በፊት አገሪቱ ካስመዘገበችው ዕድገት ማለትም 3.7 በመቶ ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ እመርታን እንዳሳየች ያመላክታል። በተጨማሪም ዕድገቱ ነዳጅ ከማያመርቱ አገራት አንፃር ሲታይ በጣም ከፍተኛ የሚባል ዕድገት ነው። ለምሳሌ ከሠሀራ በታች ያሉ አገራት በተመሳሳይ ወቅት በአማካይ በዓመት የ5.3 በመቶ ዕድገት አስመዝግበዋል። ይህ ዕድገት አኢትዮጵያ የዕድገት ተዓምር ያስመዘገበች አገር ነች እስከመባል አድርሿታል።

ከዕድገቱ ጋር ተያይዞ ፈጣን የሚባል የድህነት ቅነሳም ተመዝግቧል። በ1996 ዓ.ም ከአጠቃላይ የህዝብ ብዛት ከድህነት ወለል በታች ይኖር የነበረው 39 በመቶ የነበረ ሲሆን በ2009 ዓ.ም ወደ 23 በመቶ ቀንሷል። ከዚህ ጋር ተያይዞ በትምህርት፣ በጤናና በመሠረተ-ልማት ረገድ ከፍተኛ የሚባል መሻሻል ታይቷል። ከትምህርት አንፃር ተደራሽነት የተስፋፋ ሲሆን ጥራት ላይ ግን ችግሮች ይታያሉ። በጤና ረገድ የእናቶችና ህፃናትን ሞትን በመቀቅስና ተላላፊ በሽታዎችን በመቆጣጠር ከፍተኛ መሻሻሎች ታይተዋል። ድህነት በዚህን ያህል ቢቅንስም ባለብዙ መለኪያዎች የሆነው ለየት ያለው የድህነት መለኪያ እንደሚያሳይው አብዛኛው የአገሪቱ ህዝብ አሁንም በድህነት ውስጥ እንዳለ ያሳያል። እዚህ ላይ አገሪቷ ብዙ መስራት እንደሚጠበቅባት መረጃዎች ያሳያሉ። እነዚህ መለኪያዎች ከገቢ ባሻገር ለሰው ልጅ ኑሮ የሚያስፈልጉ ቁሳቁስና አገልግሎቶች መኖራቸውን ይለካሉ። (ለምሳሌ ንፁህ የመጠጥ ውሀ እና የመፀዳጃ አገልግሎት፣ የኤሌክትሪክ ሀይል አቅርቦት፣ የቤት ሁኔታና የሀብት መጠንን እንዲሁም ከትምህርት ጋር ተያይዞ በትምህርት ያሳለፉትን ዓመታትን ይለካል።) በዚህም መለኪያ መሠረት ከ90 በመቶ በላይ የሚሆኑት ከ10 ዓመት በታች የሆኑት የኢትዮጵያ ህፃናት ከድህነት በታች መሆናቸውን የዓለም አቀፉ የልማት ፕሮግራም መረጃ ያሳያል።

## 3 የዕድገቱ ምንጭ ምንድን ነው?

ኢትዮጵያ ባለፉት ዓመታት የታየውን ዕድገት ለማስቀጠልና ባለ መካከለኛ ገቢ ከሆኑት አገራት ለመመደብ የሚያስችል አካሄድ ላይ መሆኗ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አጠያያቂ እየሆነ መጥቷል። ይህንንም በሚገባ ለመተንተን ከአጠቃላይ ፍላጎትና ከአጠቃላይ አቅርቦት አንፃር የዕድገቱ ምንጭ ምን እንደሆነ መመልከት ተገቢ ነው።

ባለፉት 10 ዓመታት በዋነኛነት የዕድገት መንስዔ የነበረው የፍላጎት መጨመር ሲሆን፤ ይህም በይበልጥ በመንግስት ኢንቨስትመንት የሚመራ ነበር። ከአጠቃላይ የአገራዊ ምርት የኢንቨስትመንት ድርሻ በ1990ዎቹ መጀመሪያ ከነበረበት 25 በመቶ በ2009 ዓ.ም ወደ 38 በመቶ አድጓል። በቀጥታ በምርት ሠንጠረዡ ላይ ባይታይም የመንግስት የወጪ ሂሳብ እንደሚያሳየው ከፍተኛ የሚባለውን ካፒታል ያካበተው መንግስት እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል። የመንግስት የካፒታል ወጪ ከአጠቃላይ ወጪ ያለው ድርሻ በተመሳሳይ ወቅት ከ20 በመቶ ወደ 47 በመቶ ዕድገት አሳይቷል። ይህ ወጪ በዋነኛነት በኢኮኖሚ ልማት ላይ ማለትም በመንገድ፣ በኤሌክትሪክ ሀይል፣ በቤቶች ልማት፣ በውሀ አቅርቦት፣ በቴሌኮሙኒኬሽን፣ በባቡር ላይ የወጣ ወጪ ነው። ከዚህ በተጨማሪ በአንዳንድ የንግድና ማምረት ዘርፎች ውስጥም የመንግስት ተሳትፎ ነበር። ለምሳሌ፣ የስኳር፣ የሲሚንቶና የማዳበሪያ ምርቶች ላይ መንግስት ሲሳተፍ ቆይቷል።

ይህንን የመንግስት ኢንቨስትመንት ዕድገት ያነሳሳው ከ1990ዎቹ አጋማሽ በኋላ የመንግስት የልማታዊ መንግስትን የዕድገት መርህ መከተል መጀመር ነው። (በልማታዊ መንግስት ምንነትና ተያይዘው የሚነሱ ጉዳዮች ላይ በኋላ እመጣበታለሁ።) በመንግስት ኢንቨስትመንት ላይ የተሰሩ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት በድህነት ቅነሳ ላይ የመንግስት ኢንቨስትመንት ጉልህ አስተዋፆ ነበረው።

የመንግስት ከፍተኛ ኢንቨስትመንት ያበረታታቸው የግንባታና የአገልግሎት ዘርፎች በአቅርቦት በኩል ያለውን የኢኮኖሚ ዕድገት ሲመሩ ቆይተዋል። በተለይ ባለፉት ጥቂት ዓመታት የጅምላና የችርቻሮ ንግድ ዘርፉ ለዕድገት ከፍተኛ አስተዋፆ አድርጓል። በአንፃሩ ዕሴት በመጨመር ላይ የግብርና ድርሻ እየቀነሰ የመጣ ሲሆን የአምራች ኢንዱስትሪ ድርሻ ባለበት አነስተኛ ሆኖ ቆይቷል። የነዚህ ምርታማ ዘርፎች ድርሻ መቅነስና አለማደግ በወጪ ንግድ ላይ የተመረኮዘ ቀጣይ ዕድገት ማስመዝገብ ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ ይኖረዋል። ከዚህ በተጨማሪም የኢኮኖሚ መዋቅር ከማምጣት አንፃር 80 በመቶ የሚሆነው የህብረተሰብ ክፍል የሚተዳደርበት ዘርፍ (ግብርና) ከገቢ ያለው ድርሻ ሲቀንስ የሀብት ክፍፍል ልዩነትን ያባብሳል። ይህ በዕድገት ላይ ያለች አገርም ብትሆን የማህበራዊ ጠንቅ ሊያመጣባት ይችላል። የዚህ

ዓይነት ዕድገት ቋሚ የስራ ዕድል ከመፍጠርም አኳያ የሚኖረው አስተዋፆ ውስን ነው።

ሌላኛው መለኪያ ዕድገቱን የፈጠሩትን ግብዓቶች የሚያሳይ የዕድገት ሂሳብ (Growth Accounting) የሚለውን መመልከት ነው። በዚህም ስንመለከት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ዕድገት ከዝቅተኛ ምርታማ ዘርፎች ወደ ከፍተኛ ምርትማ ዘርፎች በመሸጋገር የተገኘ ሳይሆን ካፒታልን በማካበት የተገኘ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል። የዚህ ሀሳብ መነሻው በፍላጎት ላይ የተመሰረተ ዕድገት ምርታማነትንና ምርታማ ዘርፎችን ያነሳሳል የሚል ነው። ሆኖም ኢትዮጵያ ውስጥ ይህ ሊሆን አልቻለም። ምናልባት ብክነትና ሀብትን በአግባቡ አለመጠቀም እንደ አንድ ምክንያት ሊጠቀስ ይችላል።

## 4 የመንግስት ኢንቨስትመንት ገንዘብ ከየት ተገኘ?

የመንግስት ኢንቨስትመንት ገንዘብ ከሚከተሉት ምንጮች የተገኘ ነው፤

1. ***ቁጠባን ማበረታታት፡-*** የኢትዮጵያ አጠቃላይ ሀገራዊ ቁጠባ ከሀገራዊ ምርት ድርሻው በ1996 ዓ.ም ከነበረበት 9.5 በመቶ በ2009 ዓ.ም 24.3 በመቶ ደርሷል። ይህ የቁጠባ ዕድገት ቀላል የማይባል ቢሆንም ከኢንቨስትመንት አንፃር ሲታይ ግን ዝቅተኛ ነው። ካለው ከፍተኛ የዋጋ ንረት አኳያ ቁጠባን ማበረታታት አስቸጋሪ ነው። ቢሆንም መንግስት የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም ሀገራዊ ቁጠባን ለማሳደግ ተንቀሳቅሷል። ከነዚህም መንገዶች መካከል የባንክ ቅርንጫፎችን ማስፋፋት፣ የጡረታ መዋጮን በመንግስት ስርዓት ውስጥ ማጠቃለልና የመኖሪያ ቤት ቁጠባን ማበረታታት ሊጠቀሱ ይገባቸዋል። ሆኖም ከአጠቃላይ ሀገራዊ ሀብት 38 በመቶ የሆነውን ኢንቨስትመንት በቁጠባ ሊሸፈን ባለመቻሉ ሌሎች የመሸፈኛ መንገዶችን ለመጠቀም መንግስት ተገድዷል።

2. ***የታፈነ የፋይናንስ ስርዓትና ፈሰስ የተደረገ ብድር፡-*** የታፈነ የፋይናንስ ስርዓት የሚባለው መንግስታት በሀገር ውስጥ ያለውን ገንዘብ በርካሽ ለማግኘትና ዕዳቸውን ለመቀነስ ሲሉ የሚወስዷቸውን እርምጃዎች ያካትታል። ለምሳሌ መንግስት ለሚፈልጋቸው እንቅስቃሴዎች የሚሰጥ ቀጥተኛ ብድር፣ የወለድ ምጣኔን ከዋጋ ንረት በታች አድርጎ መያዝ፣ በመንግስትና በባንኮች መሀከል ጠንካራ ግንኙነት መመስረት፣ ለመንግስት ብድር የሀገር ውስጥ ገበያን ማዘጋጀትና ጠንካራ የሆነ የካፒታል ቁጥጥር ማስፈንን የመሳሰሉ እርምጃዎች ሊጠቀሱ ይችላሉ። የነዚህ እርምጃዎች ውጤት መንግስት በርካሽ ገንዘብ እንዲያገኝ ሲያስችለው የተቀረውን የኢኮኖሚ ክፍል ግን ያዛባል።

ኢትዮጵያ ውስጥ እነዚህ መሰል እርምጃዎች የተለመዱ ናቸው። በመጀመሪያ በመንግስት ይዞታ ስር ያሉ ባንኮችን በመጠቀም ከፍተኛ ብድር ወደ መንግስት እንዲፈስ ተደረገ። የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ብቻውን የሀገሪቱን 64 በመቶ ተቀማጭ ሲይዝ፤ 67 በመቶ የብድር ክምችትን ይይዛል። በአሁኑ ሰዓት ይህ ባንክ ከሰጠው ብድር 85 በመቶ የሚሆነው ለመንግስት ወይም መንግስት ለሚያስተዳድራቸው ተቋማት የተሰጠ ነው። በተጨማሪም ሁሉንም የንግድ ባንኮች የሚያስገድድ የብሔራዊ ባንክ አዋጅ ወጣ። ይህ አዋጅ ባንኮቹ ብድር ሲሰጡ ለእያንዳንዱ ብድር የ27 በመቶ የብሔራዊ ባንክ ቦንድ እንዲገዙ ያስገድዳቸዋል። የዚህም ቦንድ የወለድ ምጣኔ 3 በመቶ የነበረ ሲሆን ለአስቀማጭ ከሚከፍሉት 6 በመቶ ወለድ የሚያንስና በርካሽ መንግስት ለሚፈልጋቸው ዘርፎች በልማት ባንክ በኩል በብድር እንዲሰራጭ ሲደረግ ቆይቷል። በተመሳሳይም የንግድ ባንኮች ከሚያገኙት የውጭ ምንዛሬ 30 በመቶውን በመግዣ ዋጋው ለብሔራዊ ባንክ እንዲያስረክቡ የሚያስገድድ አዋጅም ተደንግጓል።

3. ***የብሔራዊ ባንክ የበጀት ድጎማ፡-*** ብሔራዊ ባንክ ለመንግስት የሚያደርገው ቀጥተኛ ብድር (Direct Advance) አዲስ ገንዘብ ወደ ኢኮኖሚው እንደመልቀቅ ይቆጠራል። ይህ ብድር በአማካይ በዓመት በ22 በመቶ ሲያድግ ቆይቷል። ይህ አካሄድ የዋጋ ንረትን የሚያመጣ አካሄድ ሲሆን ይህን ተከትሎ የመጣው ከፍተኛ የዋጋ ንረትም የሚጠቀስ ነው።

4. ***የውጭ ብድር፡-*** የውጭ ብድር ከ2000 ዓ.ም ጀምሮ በፍጥነት እያደገ መጥቷል። የውጭ ዕዳ ከአጠቃላይ የሀገራዊ ምርት ጋር ሲታይ በ2000 ዓ.ም ከነበረበት 10 በመቶ በ2009 ዓ.ም 32 በመቶ ደርሷል። ከአጠቃላዩ የመንግስት ዕዳ ወደ ግማሽ የሚጠጋው የውጭ ዕዳ ነው። በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የዕርዳታ ይዘት የሌላቸውን በገበያ ላይ ያሉ ብድሮችን በዋስትና ሰጭነት መንግስት ተበድሯል። የመክፈል ዓቅምን የሚያሳየውን መለኪያ ይኸውም ዕዳው ካጠቃላይ የወጪ ንግድ አንፃር ሲታይ በ2000 ዓ.ም ከነበረበት 6.5 በመቶ ወደ 44 በመቶ ከፍ ብሏል። ይህም ሀገሪቱ ዕዳ የምትከፍልበት የውጭ ምንዛሬ ዕጥረት እንደሚያጋጥማት በመገንዘብ የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ኢትዮጵያ የዕዳ ጭንቀት (Debt Distress) ውስጥ እንዳለች ጠቁሟል።

## 5 የማክሮ-ኢኮኖሚ መዛባት

ከላይ የጠቀስናቸውና መንግስት ኢንቨስትመንቱን ለማሳደግ የተጠቀመባቸው መንገዶች የማክሮ-ኢኮኖሚ መዛባት አስከትለዋል። በአጠቃላይ ከተፈጠረው መዛባት መካከል

ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ዕጥረት፣ ለግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ ከፍተኛ የፋይናንስ ዕጥረት፣ የገቢ ልዩነት መስፋት፣ የብር የመግዛት ዓቅም መውረድ፣ የዕዳ ጫና ማደግና ጠቅላላ የፋይናንስ ስርዓት አለመረጋጋት ይጠቀሳሉ።

የውጭ ምንዛሬ ዕጥረት ሊፈጠር የቻለባቸው የተለያዩ ምክንያቶች አሉ። መጀመሪያ የሚጠቀሰው የውጭ ምንዛሬ ተመን በመንግስት የተወሰነ በመሆኑና ያለ ዋጋው ዝቅ ተደርጎ ስለተያዘ ፍላጎትና አቅርቦት ሊጣጣም አለመቻሉ ነው። አቅርቦት እየጨመረ የመጣ ቢሆንም የመንግስት ኢንቨስትመንት ከሚያስገኘው የውጭ ምንዛሬ የሚያወጣው ስለሚበልጥ ከሚወጣው የብር መጠን ጋር ሊመጣጠን አልቻለም። በዚህም ምክንያት የውጭ ምንዛሬ ትክክለኛ ዋጋ መጨመር ጀመረ። በመንግስት የተተመነው የውጭ ምንዛሬ ተመን ግን ይህንን የፍላጎት መጨመር ያላገናዘበ ስለሆነ ዕቃ ወደ ውጭ የሚልኩና ከውጭ በሀዋላ ገንዘብ የሚልኩ ሰዎችን ሊያበረታታ አልቻለም። ይህ ደግሞ አቅርቦቱን ከጊዜ ወደ ጊዜ ተፅዕኖ እየፈጠረበት መጣና የወጭ ንግድ መቀነስ ድረስ ደርሷል። ተያይዞ የትይዩ የውጭ ምንዛሬ ገበያው መንግስት ከሚተምነው ተመን ጋር እየተራራቀ መጣ። አስመጭዎች ባንፃሩ በመንግስት ተመን የሚፈልጉትን ያህል የውጭ ምንዛሬ ማግኘት ስለማይችሉ፣ ወደ ትይዩ ገበያው በመግባት የውጭ ባንክ አካውንት ከፍተው የገቢ ዕቃዎችን ይገዙበታል። ይህ ደግሞ የትይዩ ገበያውን ፍላጎት ይጨምረዋል። በተመሳሳይ ሁኔታ በሀዋላ በባንክ ይላክ የነበረው የውጭ ምንዛሬ እዚያው ውጭ ባለ ሂሳብ ይቀርና የውጭ ምንዛሬውን የሚፈልጉት አካላት ሀገር ውስጥ በብር በትይዩ ገበያው ተመን ይከፍላሉ። ይህ ደግሞ የበለጠ የውጭ ምንዛሬ አቅርቦቱን ይቀንሰውና ዕጥረቱን ያባብሰዋል።

ከላይ እንደተጠቀሰው ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ ወደ መንግስትና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ይፈስ እንደነበር ይታወቃል። ይህ ከልክ ያለፈ ብድር ወደ ግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ የሚሄደውን ብድር እንዲቀንስ አድርጓል። በመሆኑም ወደ ግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ የሚሄደው ብድር ካጠቃላዩ ሲሶው ብቻ ነበር። የአምራች ኢንዱስትሪዎች የፋይናንስ አቅርቦት ከፍተኛ እክል እንደሆነባቸው ይጠቅሳሉ።

ሌላው መዛባት ከፍተኛ የመንግስት ኢንቨስትመንት የተቸራቸው የተወሰኑ ዘርፎች በነበራቸው ተጠቃሚነት የሙስና፣ የብክነትና የገቢ ክፍፍል ልዩነት መስፋትን አስከተለ። ከላይ እንደተጠቀሰው የግንባታውና የንግድ ዘርፎች በዚህ ረገድ ከፍተኛ ተጠቃሚ ነበሩ። ይህ ደግሞ የግብርናውንና የአምራች ኢንዱስትሪዎችን ሀብት በመሻማት የተፈጠረ ነው። ይህ የማትጊያ አለመመጣጠን የማምረቻ ግብዓቶች ከግብርናና ከኢንዱስትሪዎች ወጥተው ወደ ንግድና ግንባታ ዘርፎች እንዲገቡ አደረጋቸው። የነዚህ ምርታማ ዘርፎች ዕድገትና የወጪ ንግድ ዕድገትም የተሳሰረ ነው። የነዚህ ዘርፎች ሚና በመቀነሱ የወጪ ንግዱም እንደታሰበለት ሊያድግ

አልቻለም፡፡ ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው የነዚህ ዘርፎች መቀዛቀዝ ከገቢ ልዩነትም አንፃር ሌላ አንደምታም አለው፡፡ ይኸውም በነዚህ ዘርፎች ውስጥ ኑሯቸውን የመሠረቱ ሰዎች አንፃራዊ ገቢም ይቀንሳል፡፡ ለምሳሌ በ1996 ዓ.ም ከአጠቃላይ የሀገራዊ ምርት ግብርና የነበረው ድርሻ ወደ 50 በመቶ የሚጠጋ የነበረ ሲሆን፤ ከህዝቡ 85 በመቶ የሚሆነው በዚህ ዘርፍ ይተዳደር ነበር፡፡ በ2009 ዓ.ም የግብርና ድርሻ ወደ 36 በመቶ ቢወርድም፣ በዚህ ዘርፍ የሚተዳደረው የህዝብ ብዛት ግን አሁንም ከ80 በመቶ በላይ ነው፡፡ ይህ ማለት ዘርፋዊ መዋቅራዊ ለውጥ ቢኖርም ህዝቡ ግን ወደ ከፍተኛ ዕሴት ዘርፎች አለመዞሩ ይታያል፡፡ ይህ ደግሞ ከፍተኛው የገቢ መጠን በጥቂት ሰዎች መያዙንና ተያይዞም የገቢ ክፍፍል ልዩነትም እየጨመረ መምጣቱን ያሳያል፡፡ በቅርቡ በዓለም ባንክ በተሰራ ጥናት እንደተመለከተው ከ2003-2008 ባሉት ዓመታት በገጠር የሚገኙ ሰዎች የተጣራ ፍጆታ በአማካይ በዓመት አንድ በመቶ የጨመረ ሲሆን በአንፃሩ በከተማ የሚኖሩ ሰዎች ፍጆታ በስድስት በመቶ ጨምሯል፡፡ ይህ የሚያሳየው ዕድገቱ በአብዛኛው የጠቀመው በከተማ የሚገኙ ሰዎችን መሆኑ ነው፡፡ ከፍተኛ የመንግስት ኢንቨስትመንት ሌላው ተፅዕኖው ለሙስናና ብክነት በር መክፈቱ ነው፡፡ በ2010 በወጣው የዓለም ተወዳዳሪነት ሪፖርት ድርጅቶች በሰጡት ሀሳብ መሠረት ከሚያጋጥሟቸው ችግሮች በሁለተኛ ደረጃ የሚያስቀምጡት ሙስናን ነው፡፡

ሌላው መዛባትን የፈጠረው ጉዳይ ልቅ የሆነው የገንዘብ ፖሊሲና የመንግስት ወጪ ነው፡፡ ከብሔራዊ ባንክ ለመንግስት የሚሰጠው ቀጥተኛ ብድር በኢኮኖሚው ውስጥ ያለውን የገንዘብ መጠን በመጨመር የዋጋ ንረት ላይ የራሱን ተፅዕኖ አምጥቷል፡፡ የዋጋ ንረት በተለያየ ምክንያት ሊፈጠር ይችላል፡፡ ከአቅርቦት አንፃር ከማምረቻ ወጪ፣ ከማከፋፈያና ከገቢ ንግድ ጋር የሚያያዙ ምክንያቶች የዋጋ ንረት ሊያመጡ ይችላሉ፡፡ ከፍላጎት አንፃር የገንዘብ ልቀት፣ የገቢ መጨመር፣ ወቅታዊ የፍጆታ መጨመርን የመሳሰሉ ምክንያቶች ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ መንግስት ኢንቨስትመንት ለማድረግ ሲል ቀጥተኛ ብድር በመውሰዱ ምክንያት የገንዘብ ልቀት ጨምሯል፡፡ ይህ ደግሞ ለዋጋ ንረት መጨመር አስተዋፅዖ አድርጓል፡፡ ከፍተኛ የዋጋ ንረት የጀመረበት 1998 ዓ.ም በዓለም የምግብ ዋጋ ጨምሮ ነበር፡፡ ኢትዮጵያም ውስጥ የታየው የዋጋ ንረት ከውጭ የተወሰደ መሆኑን መንግስት ሲገልፅ ነበር፡፡ ሆኖም 2000 ዓ.ም የዓለም ኢኮኖሚ ቀውስ ውስጥ ሲገባና የዕቃዎች ዋጋ ሲወርድ ኢትዮጵያ ውስጥ ግን ባንፃሩ በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሮ በዓመት እስከ 48 በመቶ ደረሰ፡፡ ከዚያ በኋላ ባሉት ዓመታት የዋጋ ንረት ቀላል የማይባል ዕድገት አሳይቷል፡፡

ከፍተኛ የሆነ የዋጋ ንረት የራሱ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ አለው፡፡ በመጀመሪያ ገቢያቸው ከዋጋ ንረቱ ዕኩል የማይጨምር የህብረተሰብ ክፍሎች የመግዛት ዓቅማቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ መጥቷል፡፡ ይህ በተለይ በከተማ የሚገኙ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን

ሰዎች ያጠቃቸዋል። ገንዘብን በማተም የሚደረግ የበጀት ድጎማና ተያይዞ ሊከሰት የሚችለው የዋጋ ንረት እንደ አዲስ ታክስ ይቆጠራል። ውሱን ገቢ ያላቸው ሰዎች የመግዛት አቅም ቀንሶ የመንግስት በጀት መጨምሩ ታክስ ከመሰብሰብ ጋር ይመሳሰላል። ሁለተኛ የዋጋ ንረት የገቢ ክፍፍል ልዩነትን የበለጠ እንዲሰፋ ያደርገዋል። የዚህ ምክንያት ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው አካላት ገቢያቸውን በድርድርም ሆነ በውሳኔ መጨመር ስለሚቸገሩ የዋጋ ንረት የገቢ ልዩነትን ያባብሰዋል። በተጨማሪም ከዋጋ ንረት ጋር የቁጠባ የወለድ ምጣኔ በትክክለኛ ከዜሮ በታች ስላልሆነ ሌሎች የሀብት ማስቀመጫ መንገዶችን ሰዎች ይጠቀማሉ። ከነዚህም መካከል የውጭ ምንዛሬ፣ ወርቅና ጌጣጌጥ፣ መኪናና ቤት የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል። ይህ ደግሞ በነዚህ ዕቃዎች ገበያ ላይ የራሱ የሆነ የዋጋ ንረት ያስከትላል። በወጪ ንግድ የሚላኩ ዕቃዎች የሀገር ውስጥ ዋጋ መጨመርም ወደ ውጭ ከሚላኩ ሀገር ውስጥ ቢሸጡ ስለሚያዋጣ የወጪ ንግዱን ያዳክማል።

ሌላው በመንግስት ብድር ምክንያት የተፈጠረው ዕዳ በፋይናንስ ተቋማትም ሆነ በመንግስት በጀት ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል። በመንግስት ዋስትና ሰጪነት ከሀገር ውስጥ ባንኮች የተወሰደው ብድር ጊዜውን ጠብቆ ሊመለስ የማይችልበት አስጊ ሁኔታ አለ። ምክንያቱም ብድሩን የተበደሩት የመንግስት ተቋማት ብድሩን ለመክፈል የሚያስችል ምርታማነትና ትርፋማነት ያላቸው መሆኑ አጠያያቂ መሆኑ ነው። የውጭ ዕዳን በተመለከተ በውጭ ምንዛሬ መክፈል ስላለበት በቂ የውጭ ምንዛሬ ማግኘት አስፈላጊ ይሆናል። አሁን በተከሰተው የውጭ ምንዛሬ ዕጥረት ለዕዳ ክፍያ የሚሆን የውጭ ምንዛሬ ማግኘት አዳጋች ሊሆን ይችላል።

## 6 የማክሮ ኢኮኖሚ ሚዛንን መመለስና ቀጣይ ዕድገት

በዚህ ክፍል ከላይ የተጠቀሰውን የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባት ሊያስተካክሉ የሚችሉ ጠቃሚ ሀሳቦችን ያስቀምጣል። እነዚህን የማሻሻያ ሀሳቦች ከማስቀመጤ በፊት ስለሁኔታው ውስብስብነት ማወቅ እንደሚያስፈልግ መጥቀስ እፈልጋለሁ። ችግሩን ለመፍታት በሚደረገው ጥረት ውስጥ ቀላል የሚባልና ወጪ የሌለው መፍትሔ አለ ብዬ አላምንም። ሁለተኛ ያለውን ችግር ለማስተካከል የዕድገት መርህ ለውጥ ማምጣት አለብን የሚለው ክርክር ጋር ከመድረሳችን በፊት ችግሮቹን ለማስተካከል ሊወሰዱ የሚችሉ ብዙ እርምጃዎች አሉ ብዬ አምናለሁ። በእኔ እምነት ጠንከር ያሉ የማስተካከያ እርምጃዎች ካልተወሰዱ የኢኮኖሚ ዕድገቱ ቀጣይነት አጠያያቂ ነው። ምናልባትም የኢኮኖሚ መዛባቱን ማስተካከል ካልተቻለ የከፋ ቀውስ ሊያስከትል እንደሚችልም እሰጋለሁ።

መወሰድ አለባቸው ብዬ የማስባቸው መፍትሔዎች እርስ በርስ የሚደጋገፉና ሁሉን አቀፍ ይዘት ያላቸው መፍትሔዎች ናቸው። በዋነኛነት የመፍትሔዎቹ የመጨረሻ ዓላማ መሆን ያለበት የማክሮ ኢኮኖሚ (ዐብይ ኢኮኖሚ) መዛባትን መቀነስና የፋይናንስ ዘርፉን ጤናማነት ማስጠበቅ ነው ብዬ አምናለሁ። ይህ በተቻለ መጠን የኢኮኖሚ ዕድገቱን ሳይጎዳ መፈፀም አለበት ብዬም አምናለሁ። ለዚህም በአጠቃላይ በግሉ ዘርፍ ወደሚመራና ምርትና ምርታማነት ላይ ያተኮረ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ማስተካከያ ያስፈልጋል።

## ሀ. የመንግስት ፋይናንስ መዋቅር ማሻሻያዎች

ከላይ እንደተጠቀሰው የመንግስት ኢንቨስትመንትና የእርሱን ወጪ ለመሸፈን መንግስት የወሰዳቸው እርምጃዎች የማትጊያ መዛባትን አምጥቷል። ከዚህ በተጨማሪ የመንግስት ኢንቨስትመንት ወጪ ላይ የነበረው አስተዳደር ለሙስናና ለብክነት የዳረገ ነበር። ይህንን ለማስተካከል የመንግስትን ዕዳና የበጀት ጉድለት ሊያስተካክሉ የሚችሉ እርምጃዎችን መውሰድ ያስፈልጋል። ይህንን ለማድረግ የሚያስችሉት ወጪን በሚገባ ለማስተዳደር ከሚያስችሉ የፕሮጀክቶች ቁጥር በላይ አለማቀድ አንዱ መፍትሔ ነው። ይህም ብዙ ፕሮጀክቶችን የማስተዳደር ጫና የሚያስፈልገውን የግምገማና የቁጥጥር አቅም ስለሚሻማና በጥራት ማስፈፀም ስለሚያዳግት ለሙስናና ለብክነት ያጋልጣል። በመሆኑም መንግስት ሊያስፈፅም የሚችለውን የፕሮጀክት ቁጥር ለይቶ እነዚያን በተገቢ ቁጥጥርና ክትትል ማስፈጸም ይኖርበታል። ከዚህ በተጨማሪም የወጪ አስተዳደሩ ጥራትን ማሳደግና ቅልጥፍናን መጨመር ይጠበቅበታል። አንዳንድ የተጓተቱ ፕሮጀክቶችንም ማጠፍ ሊያስፈልግ ይችላል። የታክስ ማሻሻያዎችንም አጠናክሮ መቀጠልም አስፈላጊ ነው።

ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ጉዳይ መንግስት ወጪውን በሚቀንስበት ጊዜ የኢኮኖሚ መቀዛቀዝ አያመጣም ወይ የሚል ነው። ከላይ እንደጠቀስኩት ምንም ወጪ የሌለው ማሻሻያ ስለሌለ የሚደርሰውን ጉዳት ሊቀንሱ የሚችሉ መንገዶችን መከተል ያስፈልጋል። ከላይ እንደተጠቀሰው የመንግስት ኢንቨስትመንት ሲደገፍ የቆየው በአብዛኛው በብድር፣ በተዛባ የፋይናንስ ስርዓትና በገንዘብ ልቀት ነው። አሁን ባለው ሁኔታ እነዚህ ምንጮች እየተሟጠጡ መሆናቸውን ኢኮኖሚው በራሱ ወቅት እያሳየ ነው። የውጪ ብድር ወሰኑ ላይ እየደረስን ነው። የገንዘቡ ልቀት የዋጋ ንረት ስለሚያመጣ የታሰበላቸውን ውጤት እንዳያመጡ እንቅፋት ይሆናል። የፋይናንስ ዘርፉን ማዛባት ደግሞ የግሉን ዘርፍ በማፈንና ምርታማ ዘርፎችና የወጪ ንግዱ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ በመፍጠር የበለጠ ቀውስ ውስጥ ሊከሰት ይችላል። ስለዚህ ድንገተኛ ዕጥረት ተፈጥሮ በድንገት የኢኮኖሚ ውድቀት ከመምጣቱ በፊት ጊዜያዊ መቀዛቀዝ ሊያመጡ የሚችሉ ማሻሻያዎች ይሻላሉ።

### ለ. የገንዘብ ልቀት ላይ ገደብ ማድረግ

ከላይ እንደተጠቀሰው የገንዘብ ፖሊሲው የማክሮ ኢኮኖሚውን የማረጋጋት ስራ ከመስራት ይልቅ የመንግስትን የገንዘብ ፍላጎት ማሟላት ላይ ያተኮረ ነበር። ይህም በሀገሪቱ የታየውን የዋጋ ንረት እንዲፈጠር አስተዋፅዖ አድርጓል። ይህንን ለማስተካከል መንግስት የገንዘብ ልቀት ላይ ሊታይ የሚችል ገደብ ማድረግ ይኖርበታል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከተቋቋመባቸው ዓላማዎች መካከል ዋነኛው የዋጋና የውጭ ምንዛሬ ተመን ማረጋጋት በመሆኑ ይህንን ስራውን በሚገባ መወጣት ይኖርበታል። ይህንን ለማድረግ ለመንግስት የሚሰጠውን ቀጥተኛ ብድር ከዋጋ ንረት ግብ ጋር አጣጥሞ መሄድ ይኖርበታል። ከመረጃ ዕጥረት የሚከሰት ውዥምብርን ለማስቀረት ለህዝቡ ዋጋ ለማረጋጋት የሚወስዳቸውን እርምጃዎች ማሳወቅ ይኖርበታል።

### ሐ. የፋይናንስ ስርዓት ማሻሻያዎች

የፋይናንስ ዘርፉ ከላይ እንደተጠቀሰው ለመንግስት በርካሽ የፋይናንስ ሀብት ማሰባሰቢያ አንዱ ምንጭ ነበር። ይህንን ለማድረግ መንግስት የተጠቀመበት የወለድ ተመንና የመንግስት ባንኮችን ተጠቅሟል። የነበረው የብድር ስርዓት የመንግስትን የመመለስ ዓቅም ያገናዘበ ሳይሆን በዋስትና ላይ የተመረኮዘ ነበር። ይህ ደግሞ የፋይናንስ ስርዓቱን አደጋ ላይ የጣለ ነበር። ይህንን ለማስተካከል መንግስት ከንግድ ባንኮች የሚወስደውን ብድር በመክፈል አቅም ላይ የተመረኮዘ እንዲሆንና ከምርታማ ዘርፎች ጋር በገበያ የተመጣጠነ አሰራር መከተል ያስፈልገዋል። ባጠቃላይ ያለውን ስልጣን ተጠቅሞ ከውድድር ውጭ የሚወስደውን የፋይናንስ ሀብት መገደብ ይኖርበታል።

### መ. የውጭ ምንዛሬ ስርዓት ማሻሻዎች

አሁን የውጭ ምንዛሬ ተመኑ በብሔራዊ ባንክ የሚተመን ሲሆን በዓመት ስድስት በመቶ እንዲያድግ ተወስኗል። ባንፃሩ የትይዩ ገበያው ተመን ከኦፊሴላዊ የ 34 በመቶ ብልጫ ያሳያል። ይህ ልዩነት ከሁለት በመቶ መብለጥ የለበትም። ለዚህ ልዩነት መነሻው የውጭ ምንዛሬ ተመኑ ያለውን ትክክለኛ ፍላጎት ያገናዘበ አለመሆኑን ነው። ከላይ ከጠቀስናቸው ማሻሻያዎች ጋር የሚሄደው የውጭ ምንዛሬ ስርዓት ማሻሻያ መንግስት የሚጠቀመውን የውጭ ምንዛሬ መጠን መቀነስ ነው። ይህንን በማድረግ በቂ የውጭ ምንዛር ክምችት ከያዘ የትይዩ ገበያውን ያረጋጋዋል። ገበያው በግመታ ላይም የተመሠረተ ስለሆነ የውጭ ምንዛሬ ክምችቱ ሲጨመር የትይዩ ገበያው የመረጋጋት ዕድሉ ይጨምራል። የውጭ ኢንቨስትመንትንና የሀዋላ አገልግሎትን በማሻሻል የውጭ

ምንዛሬ ፍሰቱን ማስተካከል ይቻላል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የውጭ ምንዛሬ ተመን ማሻሻያ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ባለፈው አንድ ዓመት መንግስት የዚህን ለውጥ አስፈላጊነት የተገነዘበ ይመስላል፡፡ በመሆኑም በነዚህ ጉዳዮች ረገድ የሚታዩ እርምጃዎች ሲወስድ ቆይቷል፡፡ ለምሳሌ ከብሔራዊ ባንክ መንግስት የሚያገኘው ቀጥተኛ ብድር እንዲቀንስ ተደርጓል፡፡ የመንግስት ወጪ ስርዓትን ለማስተካከል ፕሮጀክቶች አዋጭነታቸው የሚገመገምበት ስርዓትን አሻሽሏል፡፡ ብድር የመክፈሉን ጫና ለመቀነስ ከአበዳሪዎች ጋር በድርድር የክፍያ ጊዜን የማራዘም ስራ ተሰርቷል፡፡ ለተለያዩ የውጭ ኢንቨትመንት ለመሳብ የሚያስችሉ የቢዝነስ ከባቢ ማሻሻያዎች ተደርገዋል፡፡ ይህንን ለማስተካከል ከተለያዩ ድርጅቶች ድጋፍ ተገኝቷል፡፡ ይህ አበረታች ጅምር ሲሆን በተቋማት ግንባታ፣ በገንዘብና የውጭ ምንዛሬ ስርዓቶች ማሻሻል ገና የሚሰሩ ነገሮች ይኖራሉ፡፡

## 7 ማጠቃለያ

ባለፉት 15 ዓመታት የኢትዮጵያ መንግስት የልማታዊ መንግስት መርህን የፖሊሲ አቅጣጫ ተከትሏል፡፡ መንግስት ለዕድገት የተጠቀመው መንገድ ብዙ ጥሩ ውጤቶችን ቢያስመዘግብም ኢንቨስት ያደረገበት መንገድ የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባት አምጥቷል፡፡ ይህንን ለማስተካከል የዕድገት መርህ ለውጥ ከማምጣት በፊት ሊደረጉ የሚችሉ ማሻሻያዎች አሉ፡፡ እነዚህም የመንግስት ወጪ ስርዓትን እና የገንዘብ ፖሊሲ ስርዓትን ማስተካከል፣ የፋይናንስ ስርዓት ማሻሻያዎችና የውጭ ምንዛሬ ስርዓት ማሻሻዎችን ያካትታል፡፡ ባለፈው ዓመት እነዚህን ለውጦች በማምጣት ረገድ ጥሩ ጅምሮች ቢኖሩም ሊስተካከሉ የሚገባቸው ተቋማትና ስርዓቶች ገና ይቀራሉ፡፡

# ፕራይቬታይዜሽን እና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ማሻሻያ

# የመንግስት የልማት ድርጅቶች ማሻሻያ

ብሩክ ታዬ

## መግቢያ

የኢትዮጵያ መንግስት የልማታዊ መንግስትን የኢኮኖሚ ሞዴል ተከትሎ በአገሪቱ ውስጥ የሚገኙትን የልማት ድርጅቶች ለበርካታ ዓመታት ሲያለማ፣ ሲቆጣጠርና ሲያስተዳድር ቆይቷል። የልማታዊ መንግሥት ሞዴል በርካታ ውጤቶች በኢኮኖሚው ላይ አስመዝግቧል። ሆኖም ግን በልማታዊ መንግስት ቅርጽ በተነደፈው የኢኮኖሚ ልማት ሳቢያ የመጡትን ተግዳሮቶች ከግንዛቤ በማስገባት በእ.ኤ.አ 2018 ወደ ስልጣን የመጣው አስተዳደር የቀደሙትን የትኩረት አቅጣጫዎች በመፈተሽ መንግስት የልማት አጀንዳው ላይ የትኩረት ችግር ሳይኖረው እንዳልቀረም ተገንዝቧል። በዚህም መሠረት አማራጭ እይታዎች እየተስተናገዱ ቆይተው እነሆ የልማታዊ መንግሥት በግል ዘርፍ ጉልህ ድጋፍ የሚደረገው ሽግግር በስራ ላይ መዋል ከጀመረ ሰነባብቷል። መንግስታዊ ውሳኔዎችን እና የኢኮኖሚ ፖሊሲዎችን ከዚህ ለውጥ ጋር መሳ ለመሳ ማስኬድ ስለሚገባና በተለይም የመንግስት የልማት ድርጅቶች በተለያዩ ችግሮች የተተበተቡ ከመሆናቸው አንጻር ኢኮኖሚያዊ ጥቅማቸው እንዳይደበዝዝ በመንግስት ድጎማ የሚንቀሳቀሱ መሆናቸውን ተገንዝቦ የመፍትሔ አቅጣጫ ለማስቀመጥ ተንቀሳቅሷል።

በዚህም መሠረት መንግስት በኢኮኖሚው ዘርፍ የግሉን ክፍለ-ኢኮኖሚ ድርሻ በማስፋት የአገሪቱን የኢኮኖሚ ልማት ማፋጠን አስፈላጊ በመሆኑ፤ የልማት ድርጅቶች በመንግስት ይዞታ ሥር እስካሉ ድረስ ተወዳዳሪ እና አትራፊ ሆነው በመቀጠል የሀገሪቱን የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ በማስፈጸምና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት በማምጣት ረገድ ተገቢውን ሚና እንዲጫወቱ ለማድረግ የሚያስችል አመራር እና ድጋፍ መስጠት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። በመሆኑም አገሪቱ በጀመረችው የኢኮኖሚ ሪፎርምና ዲሞክራሲያዊ የለውጥ ጉዞን ተከትሎ ትላልቅ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ወደ ግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ እንዲዛወሩ በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት ይህን ማስፈፀም እንዲቻል መንግስት የአሰራር ስርዓትን ቀርጾ በመስራት ላይ ይገኛል። በዚህም መሠረት የመንግስት ልማት ድርጅቶች ማሻሻያ ፕሮግራም ተነድፎ በአሁኑ ሠዓት የቅድመ ትግበራና የትግበራ ስራዎች በመሰራት ላይ ይገኛሉ።

ይህ ጽሁፍ ስለማሻሻያ መርሀ-ግብሩ አስፈላጊነት፣ ስለሚያስገኘው ጥቅም፣ ስለአተገባበሩ ሁኔታና አሁን ያለበትን ደረጃ በተመለከተ መረጃ ይዟል። ጽሁፉ በአራት ዋና ዋና ክፍሎች የተከፈለ ሲሆን፤ የመጀመርያው ክፍል የልማት ድርጅቶቹ አሁን ያሉበትን አቋም፣ የማሻሻያውን አስፈላጊነት እና በትግበራው በሚገኙት ኢኮኖሚያዊ ትሩፋቶች ላይ ያተኩራል። ሁለተኛው ክፍል በማሻሻያው ትግበራ ላይ ማብራርያ ይሰጣል። የሦስተኛው ክፍል በማሻሻያው ትግበራ ሂደት እስከአሁን የተሰሩ ስራዎች ላይ መረጃ የሚሰጥ ሲሆን የመጨረሻውና የማጠቃያው ክፍል በጽሁፉ የተነሱትን ሀሳቦችና ዝርዝር ጉዳዮችን በአጭሩ ለማስቀመጥ ይሞክራል።

# 1 የማሻሻያው አስፈላጊነት

የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ወደ ግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ የማዛወሩ ጉዳይ ሲነሳ አንድ ልብ ሊባል የሚገባው ጉዳይ ቢኖር ማዛወሩን መንግስት ስለፈለገ ብቻ የሚያደርገው ሳይሆን የድርጅቶቹ ነባራዊ ሁኔታ ብዙ ችግሮችን የሚያስተናግዱ በመሆኑ እነዚህ ችግሮቻቸው ተቀርፈውላቸው ለአገር ኢኮኖሚ ከፍተኛ ሚና እንዲያበረክቱ በማሰብ የተደረገ መሆኑን ነው። ይህም ድርጅቶቹ ያሉበትን ሁኔታ ለማየት በተካሄደው ጠለቅ ያለ ጥናትና ዳሰሳ ውጤት ላይ ተመስርቶ ነው። በተደርገው የዳሰሳ ጥናት ከፍተኛ ችግር ያለባቸው እና ጥሩ እየሰሩ ያሉትን ድርጅቶች የመለየት ስራ የተሰራ ሲሆን አብዛኞቹ ድርጅቶች በተለያዩ ምክንያቶች ሳብያ ከአቅም በታች የሚሰሩ እና የተቋቋሙበትን ዓላማ፣ ተልዕኮና ራዕይ ለማሳካት በችግር ላይ እንዳሉ ለመገንዘብ ተችሏል።


ጠለቅ ተብሎ ሲታይ፤ ከማሻሻያው በስተጀርባ ሦስት አንኳር ምክንያቶች ያሉ ሲሆን አንደኛው እና ዋነኛው ምክንያት አብዛኞቹ የልማት ድርጅቶች ከፍተኛ የዕዳ ጫና ያለባቸው ከመሆናቸውም በላይ በበቂ ሁኔታ አትራፊ ያልሆኑና በመንግስት ድጎማ የሚንቀሳቀሱ መሆናቸው ነው። ስለሆነም ማሻሻያው መንግስትን ከገባበት ጫና ለማውጣት የታሰበ እርምጃ ነው ማለት ይቻላል። እዚህ ላይ መጠቀስ የሚገባው ጉዳይ የአንድ መንግስት ልማት ድርጅት ብቻውን ተነጥሎ ድርጅቱን አደጋ ላይ ወይንም የብድር መብዛት ሀገርን አደጋ ላይ ይጥላል ማለት አዳጋች ነው። ይልቁንም የልማት ድርጅቶችን ወይንም ሀገርን አጣብቂኝ ውስጥ የሚከተው ብድርን የመክፈል አቅም አናሳ መሆን ነው። መንግስት ባካሄደው ጥናትም የተስተዋለው ይኸው ብድርን የመክፈል ድክመትና አቅም ማነስ ነው።

ሁለተኛው ምክንያት የልማት ድርጅቶቹ በወሳኝ የልማት ዘርፎች አገልግሎት አሰጣጥ ዙርያ የጥራትና የተደራሽነት ችግር ያለባቸው በመሆኑ ለክፍለ-ኢኮኖሚው ተወዳዳሪነት ማነስ ምክንያት ሆነው መገኘታቸው ነው። ይህም ተወዳዳሪነትን በመገደብ በኢኮኖሚው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሲፈጥር ቆይቷል።

ሦስተኛው ምክንያት ከካፒታል አቅም ጋር የተያያዘ ነው። ድርጅቶቹ በካፒታል ዕጥረት ምክንያት የመሠረተ-ልማት ዝርጋታና ማስፋፊያ ስራዎች ወጪን ለመሸፈን በጀት ስለሚያንሳቸው የገበያ ድርሻን ለመውሰድ እና ገበያውን መጠቀም አልቻሉም። እንዲሁም የልማት ድርጅቶቹ የወጠኑትን የማስፋፍያ ፕሮጀክት በወቅቱ ለመተግበር አለመቻላቸውም ይጠቀሳል። ይህም ስራዎች በወቅቱ ተጠናቅቀው መንግስት እዕዳውን ለመክፈል እንዳይችልና ይልቁንም የሚከማቸው ዕዳ መጠን በከፍተኛ ሁኔታ እንዲጨምር ምክንያት ሆኗል።

የማሻሻያ ስራው የተሰራው በእነዚህ ሦስት አንኳር ነጥቦች ላይ ተመስርቶ ነው። ሆኖም የብድር ጉዳይ ብዙ ጊዜ ውስብስብ ከመሆኑ የተነሳና በተጨማሪም ስለ ብድር የሚደረጉ ገለጻዎችና ውይይቶችም በቂ ባለመሆናቸው ምክንያት የአረዳድ ውስንነት ይታያል። ቁጥሮች ሲቀመጡ ገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መረጃ ላይ ብቻ የተመሠረተ ይመስላል። ይህን የግንዛቤ ጉድለት ለመቅረፍ አገሪቱ ላይ ያለውን የብድር ጫና የበለጠ ግልፅ አድርጎ ማሳየት አስፈላጊ ይሆናል።

የሚከተለውን መረጃ ብንመለከት ሁኔታው ይበልጥ ግልፅ ይሆናል።




ምንጭ፡- የገንዘብ ሚኒስቴር (እ.ኤ.አ በነሀሴ 2019)

እ.አ.አ በኦገስት 2019 በገንዘብ ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ ከታተመ ሪፖርት ላይ የተወሰደው ቻርት እንደሚያሳየው የመንግስት የልማት ድርጅቶች እስካሁን ያሉባቸው የአገር ውስጥና የውጭ የብድር መጠን አገሪቱ በተለመደው ወይም በሌላም መንገድ ከተበደረችው 25 ቢሊዮን ብር የሚሆን ገንዘብ ውስጥ 25% የሚሆነው ድርሻ

ይይዛሉ። በምስሉ ላይ ማየት እንደሚቻለው እ.ኤ.አ ከ2014-2019 በአጠቃላይ በማዕከላዊው መንግስት ከተወሰደው ብድር ውስጥ 48% የሚሆነው በመንግስት የልማት ድርጅቶች የተወሰደ ነው። ከላይ እንደተጠቀሰው የብድር መብዛት ብቻውን አደጋ አይሆንም። የችግሩ መገለጫ እና በፍጥነት መፈታት ያለበት ዋናው ጉዳይ በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ የተከሰተው ብድርን የመክፈል አቅም አናሳ መሆን ነው።

በማሻሻያው አስፈላጊነት ላይ በቂ ግንዛቤ ይኖር ዘንድ የልማት ድርጅቶቹ አሁን ያሉበትን ሁኔታና የተጋረጡባቸውን ችግሮች በምሳሌ እንመልከት።የኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ ሀይል ባለስልጣን እና የስኳር ኮረፖሬሽንን በአንድነት ብንወስወድ፤ ሁለቱ ድርጅቶች በድምሩ ከአራት መቶ ቢሊዮን ብር በላይ የሚሆን ብድር አለባቸው። የስኳር ኮርፖሬሽን በስሩ ባሉት ፕሮጀክቶች አማካኝነት ከፍተኛ የብድር ጫና አለበት። በአጠቃላይ ሲታይ የማሻሻያ ፕሮግራሙ የመንግስት የልማት ድርጅቶች በአሁኑ ሰዓት ያሉባቸውን ከፍተኛ ዕዳን በመክፈል አትራፊ ሆነው በኢኮኖሚው ከፍተኛ ሚና እንዲጫወቱ ለማድረግ ተስቦ የተወሰደ አቅጣጫ ነው።

እንደሚታወቀው አንዳንዶቹ የልማት ድርጅቶች ልማቱን የበልጥ ለማጠናከር አጋዥ ከመሆናቸው አንፃር ታስበው የተወጠኑ ናቸው። ለምሳሌ ያህል የህዝብ ትራንስፖርትን ችግር በመቅረፍ እና የውጭ ንግድን በማሳለጥ ረገድ የባቡር አገልግሎት አጠያያቂ አይደለም። የኢትዮጵያ ምድር ባቡር ኮርፖሬሽንን ለመመስረት እና አስፈላጊ አውታሮችን ለመዘርጋት የወጣውን ወጪ ጨምሮ ድርጅቱ ስራ ላይ ቢሆንም ከሦስት ቢሊዮን ዶላር በላይ የውጭ ብድር አለበት። ሆኖም እዚህ ላይ መጠየቅ ያለበት ጥያቄ አገልግሎቱን ለማስቀጠል ይቻል ዘንድ በምን አይነት መንገድ ነው አገራዊ ጫናው ባነሰ መልኩ ብድሩን መክፈል የሚቻለው? የሚለው ነው። ማሻሻያው ይህን ጥያቄ በሚገባ ይመልሳል ተብሎ ይታመናል።

ስለሁሉም የመንግስት ልማት ድርጅቶች የስራ ቅልጥፍና (efficiency) ጉዳይ በተመለከተ በተመሳሳይ ሁኔታ ያለው ግንዛቤ ውስብስብና ግልፅነት የጎደለው ሆኖ ስለሚታይ ይህን ጉዳይ ትንሽ ጠለቅ ብሎ መመልከት ጠቃሚ ነው። በዳሰሳው እንደታየው የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለው ገበያ ብቁ ሆነው ያለውን ፍላጎት ማሟላት እንዳይችሉ የሚያደርጋቸው የቅልጥፍና፣ የጥራትና የብቃት ችግሮች አሉባቸው። ለምሳሌ ኢትዮጵያ ከ100 ሚሊዮን በላይ ህዝብ ቢኖራትም የመንግስት የልማት ድርጅቶቹ ይህን ሠፊ የገበያ ዕድል ተጠቅመው አትራፊ ለመሆን ካለመቻላቸው በተጨማሪ ምርታቸውን ወደ ውጭ መላክም አልቻሉም። በመሆኑም አንዳንዶቹ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ለምንድን ነው ለስራው ብቁ ሆነው አትራፊ ያልሆኑት የሚለው ጥያቄ ሊሰመርበት የሚገባ ጉዳይ ነው።

እነዚህ ድርጅቶች ያላቸው ማኅበራዊ ዓላማ በጣም አስፈላጊ ስለሆነ ድርጅቶቹ የሚሰጧቸው አገልግሎቶች ላለማቋረጥ ሲባል መንግስት በከፍተኛ ወጪ ድጎማ ያደርግላቸዋል፡፡ የከፋ ችግር አንኳን ቢገጥማቸው ድጎማው አይቀርም (ለምሳሌ ድርጅቱ ብድሩን አልከፈለም ተብሎ መብራት አይቋረጥም)፡፡ ታድያ እንዴት ተደርጎ ነው በዚህ ዘላቂ ባልሆነ ሁኔታ የሚቀጥለው? እንዴትስ ነው እያንዳንዱ ድርጅት እንደ አንድ አትራፊ ኩባንያ በቂ አገልግሎት በመስጠት አትራፊ ሆኖ ለህዝብና ለሀገር ኢኮኖሚ ጥቅም ላይ የሚውለው? የሚለውን ጥያቄ በተገቢው መንገድ ለመመለስ ታስቦ ነው ማሻሻያው ያስፈለገው፡፡ ድርጅቶቹ አትራፊ አይሆኑም ነገር ግን የሚሰጡት አገልግሎት መቀጠል አለበት ከተባለም የመንግስት ድጎማ ስርዓት ተበጅቶለት መካሄድ ይኖርበታል፡፡

ሎጂስቲክስ እና የወደብ የአገልግሎትን በተመለከተ ውስብስብ ችግሮች አሉ፡፡ ለአንድ ዕቃ letter of credit ተከፍቶለት፣ ዕቃው መርከብ ላይ ተጭኖ፣ ጅቡቲ ላይ ተከማችቶ፣ ደረቅ ወደብ ላይ ደርሶ፣ ቀረጥ ተከፍሎበትና፣ የመሳሰሉ ሂደቶችን አልፎ መጋዘን እስኪገባ ድረስ በአማካኝ እስከ 123 ቀን ይወስዳል፡፡ ይህ ማለት ዕቃዎችን ከውጭ የሚያስመጣ አንድ አስመጪ ድርጅት ወይም ግለሰብ በዓመት መስራት የሚችለው 3 (ሦስት) ጊዜ ብቻ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለድርጅቶችና ለግለሰቦች ብቻ ሳይሆን በኢኮኖሚው ላይ የሚያስከትለው ጫና ቀላል እንደማይሆን ግልጽ ነው፡፡ ይህ እንግዲህ መሠረታዊ ለምንላቸው እንደ ማዳበሪያ፣ ስንዴና ስኳርን ጨምሮ ሌሎችም መሠረተ-ልማት ግንባታ ላይ የሚውሉ አስፈላጊ ቁሳቁሶች አቅርቦት ላይ ማነቆ ስለሚሆን በኢኮኖሚው ላይ የሚያሳድረው ጫና ቀላል አይሆንም፡፡ ፕሮጀክቶችን ቶሎ ካለመጨረስ ጋር ተያይዞ የሚመጣው የዕዳ ጫናም ከዚህ ጋር በቀጥታ ይያያዛል፡፡

የውጭ ንግድን በተመለከተ በሌሎች አገሮች ያለውን ሁኔታ ስንመለከት ሂደቱ ከ20-43 ቀን ድረስ እንደሚፈጅባቸው አይተናል፡፡ ከዚህ የምንረዳው ይህ የአገልግሎት ዘርፍ መፋጠን እና ማደግ ያለበት እንደሆነ ነው፡፡ ስለ አቅርቦት ማሻሻያ ፕሮግራም ስንነጋገር እነዚህ እንደ ማሳያ ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡


በዳሰሳው መሠረት ዘርፈ-ብዙ ችግሮች ያሉበትና ማሻሻያው ከሚያስፈልጋቸው የአገልግሎት ዘርፎች ሌላው የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ዘርፍ ነው፡፡ በአገራችን ያለውን የቴሌኮም አገልግሎት ብቃትና ጥራት ከጎረቤት አገሮች አንጻር ስናይ ከአገራችን ኢትዮጵያ ጋር ቅርርብ ካላት እና በህዝብ ብዛት ከኛ ከምታንሰው ጎረቤት አገር ኬንያ እንኳን እጅጉን ያነሰ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

የሚከተለው ቻርት የሁለቱን አገራት የቴሌኮም አገልግሎት ጥራትና ብቃት በንጽጽር ያሳያል፡፡

**የአቅርቦት ተወዳዳሪነት**

| አመላካች | የኢትዮጵያ አፈጻጸም | የሌሎች አገሮች መነሻ |
|---|---|---|
| ወደ ውጭ ለመላክ የሚወስደው ጊዜ | 123 ቀናት | 20-43 ቀናት |
| ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት የሚወስደው ጊዜ | 36 ቀናት | 20-28 ቀናት |
| ወደብ ላይ የሚቆይበት ጊዜ | 37 days | 3-11 ቀናት |
| ምዘና (በሎጀስቲክስ አፈጻጸም መረጃ ጠቋሚ መሠረት) | 126 | 1-40 |

አቻ አገራት፡- ቬትናም፣ ህንድ፣ ኢዶኔ፣ ባንግላዴሽ፣ ፊሊፒንስ




ምንጭ: የሎጀስቲክስ ሴክተር ስትራቴጂ፤ የትራንስፖርት ሚኒስቴር (2008)

ቻርቱ እንደሚያሳየው አገራችን ኢትዮጵያ በቴሌፎን አገልግሎት እና አቅርቦት መስፋፋትና ፍጥነት እንዲሁም በኢንተርኔት አጠቃቀም ረገድ ከጎረቤት አገር ኬንያ በጣም ወደ ኋላ ቀርታለች፡፡ ይህም እንደሌሎቹ የልማት ድርጅቶች ሁሉ በዚህ ዘርፍም ላይ ብዙ መሰራት እንዳለበት ትክክለኛ ማሳያ ነው፡፡

ወደ ማሻሻያው ስንመጣ በአጠቃላይ የኢትዮ ቴሌኮምንና ሌሎች በመንግስት ስር ያሉት የልማት ድርጅቶችን በአቅምና በተደራሽነት ረገድ ለማጎልበት ከፍተኛ የካፒታል መጠን ያስፈልጋል፡፡ ሆኖም መንግስት በእነዚህ ድርጅቶችና በሌሎች ምክንያቶች ሳቢያ ባለበት የበጀት ጫና ምክንያት የሚፈለገው ካፒታል ከየት ይመጣል የሚለው ጥያቄ ምላሽ ይፈልጋል፡፡ የመንግስት ገቢ ውስን ከመሆኑ በላይ በታክስ፣ በድጋፍና በብድር

ብቻ ላይ የተመሰረተ ከመሆኑ አንጻር አገልግሎቶችን ለማስፋፋት አዳዲስ እና አስፈላጊ ሀሳቦችን ማጤን ግድ ይላል።

በተመሳሳይ ሁኔታ የኤሌክትሪክ አቅርቦትን ብንመለከት አገሪቱ ዝቅተኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ ለመመደብ ለ86.2% ያህል ህዝቦቿ የኤሌክትሪክ ሀይል ተደራሽነትን ማረጋገጥ ይኖርባታል። ሆኖም አሁን ያለው የአቅርቦት መጠን ከ44.3% ያልበለጠ ነው። ይህንን ግብ ለማሳካት ከባድ ስራ ለመስራት ከፍተኛ ካፒታል ያስፈልጋል። አገሪቷ ተጨማሪ ብድር የመውሰድ አቅሟ በጣም እየጠበበ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ የኤሌክትሪክን ተደራሽነት በማሳደግ ተጨማሪ ፍላጎትን ማርካት የማይቻልበት ሁኔታ ተፈጥሯል። በመሆኑም ህብረተሰባችን የኤሌክትሪክ ሀይልን ጨምሮ ውሀ እና ስልክ መጠቀም የሚችልበትን ሌላ መንገድ ማፈላለግ ግድ ይላል። እንደ መንግስት አረዳድና አቋም ይህን መብት ያለማረጋገጥ የዜጎችን አገልግሎት የማግኘት ፍትሀዊነት ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባው ይሆናል። ስለዚህ በአጠቃላይ የካፒታል አስፈላጊነት ጉዳይ በመንግስት ተይዘው በጥሩ ሁኔታ እየሰሩ ያሉትን የልማት ድርጅቶች ብቻ ሳይሆን በራሳቸው ማኅበራዊ ግብ እና መንግስት ባስቀመጠላቸው አቅጣጫ መሠረት የሚንቀሳቀሱትም ቢሆኑ በኢኮኖሚው ምህዳር ለመሳተፍ ከባድ የካፒታል ዕጥረት ያሉባቸው በመሆኑ ማሻሻያው አስፈልጓል። ስለሆነም የእነዚህ ድርጅቶች የካፒታል ጥያቄ ይሟላ ዘንድ የመንግስት የልማት ድርጅቶችን በከፊልና በሙሉ ወደ ግሉ ማዛወርና የግሉ ዘርፍ ሚና ተጨምሮበት አገልግሎቶችን በበቂ ሁኔታ ማዳረስ ሀገራዊ ግዴታ ነው።

የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ወደ ግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ በከፊል ወይንም በሙሉ ማዛወር መወሰኑ ብዙ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም እንዳለው ቢታወቅም የሪፎርሙን ዓላማ ካለመረዳት የተነሳ በብዙ ሰዎች ዘንድ የተሳሳቱ አመለካከቶች ሲንፀባረቁ ይስተዋላል። ከእነዚህ የተሳሳቱ አመለካከቶች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል፤

- የህዝብ ሀብት የሆኑት ልማት ድርጅቶችን ወደ ግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ ማዛወር ወይም በከፊል መሸጥ መንግስት ያገኝ የነበረውን ጥቅም አሳልፎ መስጠት ነው።
- የመንግስት የልማት ድርጅቶች የማይነኩ ብርቅዬ የህዝብ ጌጦች ናቸው።
- ፕራይቬታይዜሽን ለከፍተኛ የታሪፍ ጭማሪ ስለሚዳርግ የህብረተሰቡን ጥቅም ይጎዳል። በመሆኑም ማሻሻያው ተገቢ አይደለም የሚሉ ናቸው።

እነዚህ አመለካከቶች የተወሰኑ እውነታዎች ቢኖራቸውም በቂ የማስተካከያ እርምጃ እስከተወሰደ ድረስ የሪፎርሙን ትሩፋቶች በተግዳሮት ብቻ ማመላከት አግባብ አይሆንም። ነገር ግን ከዚህ በፊት በሌሎች ሀገሮች ተሞክሮ እንደሚታየው ወደ ግል

የሚዞሩ የመንግስት ድርጅቶች ላይ የተካሄደው ማሻሻያ ከፍተኛ እንደመሆኑ መጠን ስራው በከፍተኛ ጥንቃቄ መሰራት እንዳለበት አጠያያቂ አይደለም።

## 2 የማሻሻያ ፕሮግራሙ የሚሰጣቸው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎች

የማሻሻያ ፕሮግራሙ አያሌ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎች እንደሚኖሩት ይታመናል። ከብዙ በጥቂቱ ለመጥቀስ ያህል፦

i. በሂደቱ የሚገኘው ገንዘብ ልማትን ለማስቀጠል አስፈላጊ የሆነውን የፋይናስ ፍሰት በማጠናከር ኢኮኖሚውን ያበረታል። ከሽያጭም የሚገኘው ገንዘብ ዕዳን ለመክፈል እና በሌሎች አስፈላጊ ኢንቨስትመንቶች ላይ ለማዋል ከማስቻሉም በላይ የሚገኘው ገንዘብ ድርጅቶችን እየገነቡ እና እያሻሻሉ ለማስቀጠል ያስችላል። ይህም ሲሆን የመንግስትን ገቢ እንደ ታክስ ባሉ በተለያዩ የገቢ ማስገኛ መንገዶች ማሳደግ ይቻላል። በከፊል ወደ ግል የተዛወሩትም ድርጅቶችም ቢሆኑ ታክስ ስለሚከፍሉ የሚገኘው የኢኮኖሚ ጥቅም ከፍተኛ እንደሚሆን ይታሰባል።

ii. የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት (Foreign Direct Investment) እንዲጨምር ያደርጋል። ከዚህ በተጨማሪ ደካማዎቹን የልማት ድርጅቶች ለመደጎም የመንግስት ፋይናንስ ጫናን ይቀንሳል። ይህም የብርን ትክክለኛ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ያረጋግጣል። መንግስት በስሩ ከሚያቆያቸው ከጠንካሮቹና ተፎካካሪ/ተወዳዳሪ የልማት ድርጅቶች የሚያገኘው ትርፍ እና ግብር እንዲሁም ሌሎች ገቢዎች ይጨምራሉ።

iii. ማሻሻያው የግል ክፍለ-ኢኮኖሚውን ተሳትፎ የመጨመር ሀይልም አለው፤ የስራ ፈጠራንም ያሳልጣል። ተጨማሪ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ወደ ግል ዘርፍ በሚዛወሩበት ጊዜ የግል ክፍለ-ኢኮኖሚውን ተሳትፎ ስለሚጠይቅ ወይም ስለሚጋብዝ እርሱ በራሱ ተጨማሪ ሀብት ይፈጥራል። ተጨማሪ የስራ ዕድልም ለዜጎች የሚፈጠርበት ሁኔታ ይኖራል። በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ ንቁና ትርጉም ያለው የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ ተሳትፎን ያጎለብታል፤ ያፋጥናል። አገልግሎት መስጠትን በተመለከተ በቴሌኮም እና በሎጂስቲክስ ላይ ቀደም ብሎ በምሳሌነት የተነሳው ችግር የግሉ ዘርፍ ተቀላቅሎ በእነኝህ ሴክተሮች ላይ ሲሳተፍ ተወዳዳሪነት ስለሚኖር አገልግሎቱን በብቃት መስጠት ይችላሉ ማለት ነው።

iv. የመንግስት የልማት ድርጅቶችን በሙሉ፣ በከፊል፣ በሽርክና ወይም በትብብር መድረክ አልያም በተዘዋዋሪ፣ ድርጅቶቹን አንድ አካባቢ በማድረግ እና

በትስስር ወደ ግሉ ክፍል ኢኮኖሚ ከማዛወር በሚገኘው ካፒታል፣ የካበተ ልምድና ዕውቀት እንዲሁም ቴክኖሎጂ አማካኝነት ቴሌኮም፣ አሌክትሪክ ሀይልና የመሳሰሉት አገልግሎቶችን በብቃት እና በጥራት ለተጠቃሚዎች የማቅረብ ሰፊ ዕድል ይፈጠራል።

በዳሰሳው መሠረት እያንዳንዱ የልማት ድርጅት አሁን ያለበት ሁኔታና የሚያስፈልገውን የማሻሻያ ፕሮግራም በሴክተር እንመልከት።

## *ሀ. ኢትዮ ቴሌኮም*

ኢትዮ ቴሌኮምን በተመለከተ በርካታ ውይይት ሲደረግ ቆይቷል። ዘርፉ የአቅም ችግር ቢኖርበትም እስከ አሁንም የኮሙኒኬሽን ህጉን አርቅቆ በመጨረስ በኩል ጥሩ ውጤት የታየበት፤ ብዙ ስራም የተሰራበት የአገልግሎት ዘርፍ ነው። ከ100 ሚሊዮን በላይ ለሆነ ህዝብ አንድ የቴሌኮም ኦፕሬተር ብቻ ባለበት ሁኔታ አገልግሎቱ በቂ ተደራሽነት አለው ለማለት ያስቸግራል። በመሆኑም የአገልግሎት ዘርፉ ብቁ ሆኖ እንዲቀጥል ወደ ግል መዛወር የሚያስፈልገው መሆኑ በጥናቱ ታይቷል። ስለዚህ ኢትዮ ቴሌኮምን በከፊል (እስከ 49% ድረስ) ወደ ግሉ ክፍል-ኢኮኖሚ ለማዛወር አቅጣጫ ተይዞ እየተሰራበት ይገኛል። በቅርቡ በወጣው የኢትዮጵያ ኮሚኒኬሽን አዋጅ 1140/2011 መሠረት መንግስት ራሱን የቻለ የሚቆጣጠር እና የሚያስተዳድር አካል (regulatory authority) አቋቁሟል። መንግስት ባስቀመጠው አቅጣጫ መሠረትም በሴክተሩ መሳተፍ ለሚፈልጉ ሁለት ተጨማሪ የቴሌኮም አገልግሎት ሰጭዎች ፍቃድ በመስጠት ዘርፉን እንዲቀላቀሉ ያደርጋል።

## *ለ. ስኳር ኮርፖሬሽን*

እንደሚታወቀው የስኳር ኮርፖሬሽን በስሩ 13 የስኳር ፕሮጀክቶች አሉት። ፊንጫ፤ ወንጂና መተሀራን ሳይጨምር የተቀሩት አዲስ ሲሆኑ በጠቅላላው ከፍተኛ ዕዳ ያሉባቸው ናቸው። የአገር ውስጥ ዕዳቸው ብቻ ከ75 ቢሊዮን ብር በላይ ደርሷል። እነዚህ አዳዲስ ፕሮጀክቶች በሁለት እና በሦስት ዓመታት ውስጥ ተጠናቀው ስራ ሲጀምሩ፤ ምርታቸውን ለውጭና ለሀገር ውስጥ ገበያ እያቀረቡ በሚያገኙት ገቢ ዕዳቸውን ይከፍላሉ የሚል ዕሳቤ ነበር። ሆኖም በተለያዩ ምክንያቶች ይህ ሊሆን አልቻለም። አዲስ ከተቋቋሙት ፋብሪካዎች መካከል ኩራዝ 2 እና 3 ፕሮጀክቶች የተጠናቀቁ ሲሆን ኩራዝ 5፣ በለስ 1፣ በለስ 2፣ ወልቃይት እና ኩራዝ 1 ገና አልተጠናቀቁም። የተጠናቀቁትም ቢሆኑ ገና በሙሉ አቅማቸው መስራት አልጀመሩም። የተንዳሆ ፕሮጀክት አልቆ ጥሩ ውጤት የታየበት ቢሆንም በአገዳ ዕጥረት የተነሳ ስራ አቁሟል። የቀሰም እና የአርጆ ደዴሳ ፕሮጀክቶችም እንደዚሁ ተመሳሳይ ችግሮች አሉባቸው። እንግዲህ በአጠቃላይ እነዚህን ችግሮች ለማስተካከል

በርካታ ተጨማሪ፣ ምናልባት እስካሁን ለአስሩ የስኳር ድርጅቶች ለልማት የወጣውን ወጪ የሚስተካከል ገንዘብ የሚያስፈልግ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ቀደም ብሎ እንደተገለፀው በማሻሻያው ትግበራ ሂደት መጀመሪያ የተሰራው ስራ ያተኮረው እንዴት ዕዳቸውን እንቀርፋለን በሚለው ላይ ነበር፡፡ ሆኖም በውስጣቸው ያሉባቸውን ችግሮች ግምት ውስጥ በማስገባትና እነዚህን አንድ በአንድ ለመቅረፍ ይቻል ዘንድ የስኳር ፕሮጀክቶቹን ሙሉ በሙሉ ወደ ግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ እንዲተላለፉ በተወሰነው መሠረት ከስኳር ድርጅት ጋር በመተባበር ይህ እየተሰራ ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ የዋጋ ግመታ ተጠናቅቆ በውድድር ላይ የተመሠረተ ወደ ግል የማዞር ቅድመ-ስራ እየተከናወነ ይገኛል፡፡

### *ሐ. የኤሌክትሪክ ሀይል*

የኤሌክትሪክ ሀይል አመንጭቶ ማከፋፈል አጅግ አስፈላጊ የሆነ የአገልግሎት ዘርፍ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ እዚህ ላይ የተካሄደው ጥናት በሁለት ዘርፍ ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሀይል የዕዳ ችግር አፈታት ዙርያ ያተኮረ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ የኤሌክትሪክ ሀይል አገልግሎት ተደራሽ ያልሆነውን የህብረተሰብ ክፍል ተጠቃሚነቱን ለማረጋገጥ በሚያስችሉ ስራዎች ላይ ነበር፡፡

የድርጅቱ ዕዳ ከድርጅቱ አልፎ የአገር ስጋት እንዳይሆን በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ የዕዳ ክፍያ ግዴታው እንዲሻሻል ተደርጓል፡፡ ይህም ሲባል የመክፈያ ጊዜን ከማራዘም ጋር የተያያዙ ስራዎችን ያጠቃልላል፡፡ ከዚህ ጋር በተገናኘ በቅርብም እንደታየው "የመንግስትና የግል ዘርፍ አጋርነት" (public private partnership) የተሰኘው አንደኛው የፋይናንሲንግ ሞዴል ጋር ተያይዞ በቅርቡ በገንዘብ ሚኒስቴር ይፋ የተደረገው በአፍሪካ ውስጥ የመጀመሪያ የሆነ ከፀሀይ ብርሀን በሚገኝ ሀይል አንድ ኪሎዋት በ0.25 ሳንቲም ብቻ የሚሸጥ የግል ኩባንያ ወደ ስራ እንዲገባ ለማስቻል ጨረታው ተጠናቅቋል፡፡ እንደዚህ ዓይነት አሰራር ድርጅቶቹን የሚገዛው የግል ዘርፍ ገንዘቡን ይዞ መጥቶ ስጋቱን ራሱ የሚወስድበት ሁኔታ መፈጠሩ፣ መንግስትም በአጋርነት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ በመሆን የሁለቱም ወገኖች ፍላጎት እንዲሟላ የሚያደርጉ የማጣመር ስራዎች እንዲቀጥሉ ያደርጋል፡፡

### *መ. ሎጂስቲክስ*

ሎጂስቲክስን በተመለከተ ያለው ዋና ችግር የብቃት እና የቅልጥፍና ማነስ ነው፡፡ ከደረቅ ጭነት ወደብ ጀምሮ ተያያዥ የሆኑ በርካታ ውጥንቅጦች መፍትሔ ሊገኝላቸው ይገባል፡፡ ጠቅለል ባለ መልኩ የኢትዮጵያ መርከብ ድርጅት አሰራርና የግሉ ዘርፍ በስራው ላይ ያለው ሚናን ማጠናከር የሪፎርሙ ዓላማ ነው፡፡ አንድን ኮንቴይነር ከሌላ አገር ወደብ ላይ አንስቶ አንድ አዲስ አበባ ውስጥ ያለ መጋዘን ለማድረስ

የኢትዮጵያ መርከቦች ድርጅት አሰራርን እንዴት ማዘመን ይቻላል? የአሰራር ዘይቤውን በምን ዓይን ሁኔታ በማሳደግ ብቃትና ቅልጥፍናን ማምጣት ይቻላል የሚለው እየታየ ያለ ጉዳይ ነው፡፡ እስካሁን በዚህ ጉዳይ ላይ ስምምነት ላይ የተደረሰ ሲሆን ትራንስፖርት ሚኒስቴር እና ከኢትዮጵያ መርከቦች ድርጅት እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የተሰራው ስራ አልቆ የውሳኔ ሀሳብ እየተጠበቀ ይገኛል፡፡

### *ሠ. ኢንዱስትሪ ፓርክ*

ኢንዱስትሪ ፓርኮቻችን በተመለከተ በውስጣቸው አስፈላጊ የሆኑት አገልግሎቶች ተሟልተውላቸው አልሚዎች ሲመጡ በቀጥታ ወደ ምርት እንዲገቡ የሚያስችሉ ስራዎች እየተሰሩ ነው፡፡ የእነዚህ ድርጅቶች ወጪ ከፍተኛ ስለሆነ ከስራው በሚገኘው ትርፍ የድርጅቶቹን ወጪ ለመሸፈን ስለሚከብድ ይህ ዘርፍ ሙሉ በሙሉ ወደ ግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ እንዲዛወር አቅጣጫ ተሰጥቷል፡፡ ለዚህም እንዲረዳ አስፈላጊው ጥናት በመዘጋጀት ላይ ይገኛል፡፡

### *ረ. የኢትዮጵያ የምድር ባቡር ኮርፖሬሽን*

ይህ የአገልግሎት ዘርፍ ከተደራሽነት ጋር በተያያዘ ውስንነቶች ያሉበት ሲሆን አገልግሎቱን ለማሳደግ ተጨማሪ ፉርጎዎች እና የኤሌክትሪክ ሀይል ማስተላለፊያ መስመሮች የመሳሰሉ ግብዓቶች ያስፈልጉታል፡፡ ያልተጠናቀቁ መስመሮችም አሉ፡፡ ይህ ሁሉ እንዳለ ሆኖ ከዚህ ቀደም ተሰርተው ለተጠናቀቁት ስራዎች የተገኘው ብድርም መከፈል አለበት፡፡ ስለሆነም ይህ ዘርፍ ወደ ግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ በማዘዋወር በብቃት ስራውን እንዲያከናውንና ያለበትን ዕዳ እንዲከፍል ማድረግ የተሻለው አማራጭ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ይሁን እንጂ ከላይ የተዘረዘሩት ሥራዎች የሚኖራቸው ውጤታማነት በቀጣይ የሚረጋገጠው ጠንካራ የመንግስት ልማት አስተዳደርና ህግ ሲኖር ነው፡፡ ለዚህም እንዲረዳ ከ1992 ዓ.ም ጀምሮ በስራ ላይ የሚገኘውን የመንግስት የልማት ድርጅት አስተዳደር አዋጅን የማሻሻል ስራ እየተከናወነ ይገኛል፡፡ የማሻሻያው ዋና ዓላማ የመንግስት ልማት ድርጅቶችን አስተዳደርና አመራር እንዲሁም ከፋይናንስ እና ከፕሮጀክት ማስፈጸም አቅም ጋር የተገናኙ ስርዓቶችን በህግ ማዕቀፍ አጠናክሮ ማስቀመጥ ነው፡፡ በተለይ የብድር አወሳሰድና አከፋፈል አሰራር እና የቦርድ እና የተቆጣጣሪ ባለስልጣን ሀላፊነትን በተመለከተ ረቂቅ አዋጁ በርካታ ማሻሻያዎችን ይዟል፡፡ በተጨማሪም የመንግስት ልማት ድርጅቶች የተሰጣቸውን ኃላፊነት በበቂ ሁኔታ ለመወጣት እንዲችሉ የንግድ ድርጅቶች አስተዳደራዊ ቅርጽ በረቂቁ ላይ ተካትቷል፡፡

***ሠንጠረዥ 1፡*** *የመንግስት የልማት ድርጅች ያሉባቸውን ችግሮች (ምክንያቶች) እና የተወሰዱ የማሻሻያ እርምጃዎች*

| ተ.ቁ | ዘርፍ | የማሻሻያው ምክንያት | የተወሰዱ የማሻሻያ እርምጃዎች |
|---|---|---|---|
| 1 | ኢትዮ ቴሌኮም | ቅልጥፍናን ለማሳደግ ተጨማሪ ኢንቨስትመንት አስፈላጊነት | በከፊል ወደ ግሉ ኢኮኖሚ እንዲዛወር በማድረግ የአገልግሎቱን በብቃትና ጥራት ማሳደግ ገበያውን ክፍት በማድረግ ሁለት ተጨማሪ ኦፕሬተሮችን ማስገባት የሚፈልገውን ተጨማሪ ኢንቨስትመንት ማሳካት ለሀገር ተጨማሪ ገቢ በማግኘት ሌላ ኢንቨስትመንት ላይ ማዋል። |
| 2 | የኢትዮጵያ ስኳር ኮርፖሬሽን | ብድር ጫና<br>የፕሮጀክቶች አለመጠናቀቅ | ብድር በአግባቡ ለመክፈል የዕዳ ጫናን መቀነስ<br><br>ፕሮጀክቶች ተጠናቀው በቂ ምርት ለሀገር ውስጥና ለውጭ ሽያጭ ማቅረብ |
| 3 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል | የብድር ጫና<br><br>የአገልግሎት ብቃት፣ ቅልጥፍናና ተደራሽነት | በዳሰሳው ውጤት መሠረት የግል ዘርፉን ተሳትፎ ማሳደግ<br><br>የብድር አከፋፈል ችግርን መቅረፍ |
| 4 | የሎጂስቲክስ የአገልግሎት ዘርፍ | የአገልግሎት ቅልጥፍናና ድክመት | የአገልግሎት ገበያውን ነፃ/ክፍት ማድረግ ፤ የአገልግሎት አሰጣጥ ሰንሰለቱን (ደረቅ ወደብ፣ ትራንስፖርት፣ ወዘተ) በማሳጠር ኢኮኖሚው ላይ በተለይ የውጭ ንግድ ላይ አወንታዊ ተፅዕኖ ማምጣት |
| 5 | ኢንዱስትሪ ፓርክ | በአገልግሎት ቅልጥፍና ድክመት<br><br>የብድር ጫና | በዳሰሳው ውጤት መሠረት ጎልቶ የሚታየውን ችግር መፍታት |
| 6 | የኢትዮጵያ የምድር ባቡር ኮርፖሬሽን | የብድር ጫና<br><br>የአገልግሎት ቅልጥፍና ድክመት | የአስተዳደር ስርዓት ማዘመን<br><br>ብድር የመክፈል አቅምን ማጎልበት<br><br>ኢኮኖሚው ላይ ጉልህ ሚና እንዲኖረው ማስቻል፡ |

## 3 የማሻሻያ ፕሮግራሙ አተገባበር

የእነዚህ የመንግስት ከፍተኛ የልማት ድርጅቶች ወደ ግል ማዛወር አካሄድ በምን ዓይነት ሁኔታ ነው እየተሰራ ያለው የሚለው ግልፅ ያልሆነ ነገር አለ። ይህንን ሒደት በባለቤትነት እየተገበረ የሚገኘው፤ ወደ ግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ የማዛወሩን ስራ ጥናቱንና አካሄዱን እየሰራ የሚገኘው የገንዘብ ሚኒስቴር ነው። በተግባር ማዛወር ደረጃ ላይ ሲደርስ ደግሞ ስራውን የመንግስት ልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ

ይረከበዋል፡፡ በመረጃ ደረጃ ጥናት እና ግምገማውን የሰራን ድርጅት፤ ድርጅቶችን ወደ ግል የማዛወር ተግባርን ከሚሰራው ድርጅት ጋር መቀላቀል ራሱን የቻለ ችግር ስለሚያመጣ የዝግጅት ስራውን እና ተግባራዊ ስራው በተናጠል ይሰራል፡፡

ከተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች፣ ከፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ከባለሙያዎች እንዲሁም ከያንዳንዱ ሪፎርሙ ከሚመለከተው አካል የተውጣጣ ድርጅቶቹ ራሳቸው የሚገኙበት (ምክንያቱም ያሉባቸውን ችግሮች ከነሱ በላይ የሚያውቅ የለም ተብሎ ስለሚታመን) የመንግስት ልማት ድርጅቶች ቴክኒካል ኮሚቴ አባል የሆኑበት የአማካሪዎች ቡድን ተዋቅሯል፡፡

የመንግስት የልማት ድርጅቶች ማሻሻያ መርሀ-ግብር ዓላማ የመንግስትን አገራዊ የልማት ፖሊሲዎችና ግቦችን ለማሳካት ቁልፍ ሚና የሚጫወቱትን ልማታዊ ተቋማት በመንግስት ስር እንዲቆዩ በማድረግ፤ የተቀሩትን በከፊል ወደ ግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ በማዛወር ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ አፈጻጸሙም የሀገርን ጥቅም በሚያረጋግጥ መልኩና ሂደቱም ፍጹም ግልጽነትና ተጠያቂነት በሞላበት መንፈስ የሚከናወን እና የዜጎችን መብትና ጥቅምን የሚያስከብር ነው፡፡ አተገባበሩም በጥናት ላይ ተመስርቶ እና እንደ የልማት ድርጅቶቹ ሁኔታ የተለያየ የማሻሻያ ስራዎችን በመስራት የሚካሄድ ነው፡፡

በሌላ አነጋገር የማሻሻያ እርምጃው እንደየድርጅቶቹ ባህሪና ሁኔታ ታይቶ የሚከናወን እንጂ ለሁሉም ሴክተር አንድ አይነት የማሻሻያ ስትራቴጂ አልተቀመጠም፤ ሁሉም ድርጅቶች ሙሉ በሙሉ ወደ ግሉ ዘርፍ ይዙሩ የሚል አጀንዳም የለም፡፡ በመጀመሪያ የተሰራው ሪፎረሙ ሲሆን፤ በመቀጠል በጥናት ላይ ተመስርቶ ሴክተሩ ሙሉ በሙሉ በመንግስት የተያዘ ከሆነና ወደ ግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ ማዛወር አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ከመንግስት ልማት ድርጅቶች ኤጀንሲ ጋር በመመካከር እና በመተባበር የሚሰሩበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

የመንግስት የልማት ድርጅት ማሻሻያ መርሀ-ግብሩን የሚያስፈጽሙ ተቀዳሚ መንግስታዊ አካላት የተሰየሙ ሲሆን ግዴታ እና ሀላፊነታቸውም እንደሚከተለው ነው፡፡

- ***ገንዘብ ሚኒስቴር-*** የማሻሻያ ፕሮግራሙን አፈጻጸም ሂደት ይመራል፤ በጥናትና በመረጃ የተደገፈ መሆኑንም ያረጋገጣል፤
- **የመንግስት የልማት ድርጅቶች አስተዳደርና ቁጥጥር ኤጀንሲ፡-** ወደ ግል ክፍለ-ኢኮኖሚው የማዛወር ሥራን ያከናውናል፤

- ***የመንግስት የልማት ድርጅቶች ማሻሻያ ፕሮግራም አማካሪ ቡድን፡-*** ስለ ማሻሻያ አፈጻጸም ሂደት እየተከታተለ ለህዝቡ የማሳወቅና የማስተማር ስራ ይሰራል፤ የአፈጻጸም ሂደቱንም እየተከታተለ የህዝብ ጥቅምና ፍላጎት የሚረጋገጥበትን ሁኔታ ላይ ለአስፈጻሚዎቹ ምክረ-ሀሳብ ይሰጣል

- ***የሴክትር ሚኒስቴር መ/ቤቶች፡-*** በቁልፍ ሴክተሮች አፈጻጸም ሂደት ላይ ምክረ-ሀሳብ ይሰጣሉ፤

- ***ኢንተርፕራይዞች፡-*** የማሻሻያ ፕሮግራሙን ስኬት በሚያረጋግጡ ቁልፍ የትግበራ አቅጣጫዎች ላይ ግብዓት ይሰጣሉ።

## 4 ማሻሻያውን ለመተግበር ያለው ተቋማዊ ዝግጅት

የሪፎርም መርሀ-ግብሩን ተግባራዊ በማድረግ ሂደት የህግ ማዕቀፎች ላይ ዳሰሳ የሚደረግ ሲሆን በተጨማሪም በሴክተር፣ በልማት ድርጅቶቹ ደረጃና የገበያ ቁጥጥር ስርዓቱ ላይ ዳሰሳ ተካሂዷል። ከላይ እንደተጠቀሰው በመንግስት ልማት ድርጅቶች የህግና የቁጥጥር ማዕቀፎችን በተመለከተ የመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅና ቁጥር 25/1992 የማሻሻያ ሥራ እየተካሄደ ይገኛል።

በተቋማት ደረጃም እንዲሁ በመልካም አስተዳደር፣ በፋይናንስ አቅምና በኦፐሬሽን ዙርያ ያሉት ተግዳሮቶችና መልካም አጋጣሚዎች ተዳስሰዋል። በኢንተርፕራይዝ ደረጃ ደግሞ እያንዳንዱ ድርጅት ምን ደረጃ ላይ እንዳለ ማወቁ አስፈላጊ በመሆኑ በዚሁ ላይ ሰፊ የዳሰሳ ጥናት በመካሄድ ላይ ይገኛል። ለሽያጭ የሚቀርቡት ድርጅቶች ዋጋቸው እንዲጨምር በማሰብ የተጀመሩና በእንጥልጥል ያሉ ስራዎች እንዲያልቁ የማድረግ ስራዎችም በመሰራት ላይ ይገኛሉ።

በተጨማሪም ድርጅቶቹ በሚሳተፉበት ገበያ ደረጃም የገበያ ቁጥጥር ስርዓቱ ተዳስሷል። በዚህም መሠረት የግል ክፍለ-ኢኮኖሚውን ለመደገፍና ተሳትፏቸውን ማሳደግ ብቻ ሳይሆን ማህበረሰቡን የማገልገል ግዴታቸውንም እንዲወጡ የሚያደርግ ህጋዊ ማዕቀፍ ተዘጋጅቷል። የመንግስት የልማት ድርጅቶች ማሻሻያ መርሀ-ግብሩን የሚያስፈጽሙ ተቀዳሚ መንግስታዊ አካላት የተሰየሙ ሲሆን ግዴታ እና ሀላፊነታቸውም በመዋቅር ተቀምጧል።

*ሠንጠረዥ 2፡ የማሻሻያ ስራውን በተመለከተ እስካሁን የተከናወኑ ስራዎች*

| ተ.ቁ | ሴክተር | የተጠናቀቁ ፣ በሒደት ላይ ያሉ እና ቀጣይ ስራዎች |
|---|---|---|
| 1. | ኢትዮ ቴሌኮም | • የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ቅልጥፍናን ለማረጋገጥ በአዋጅ ቁጥር 1148/2019 መሠረት የኢትዮጵያ የቴሌኮሙኒኬሽን ኤጀንሲ ተቋቁሟል። <br>• በከፊል ወደ ግሉ ሴክተር የሚዛወረው ኢትዮ ቴሌኮምን ዋጋ የማውጣት ስራ እየተካሄደ ይገኛል። <br>• የሂሳብ አያያዙን ጨምሮ መሠርተ-ልማቱን ከአገልግሎቱ የመለየት ስራዎች ይካሄዳሉ። <br>• የተለያዩ አዳዲስ መመሪያዎችና ደንቦች በመዘጋጀት ላይ ይገኛሉ። <br>• ሁለት ቴሌኮም አገልግሎት አቅራቢ ኩባንያዎች ገበያውን እንዲቀላቀሉ በቂ ቅድመ-ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል። |
| 2. | የኢትዮጵያ ስኳር ኮርፖሬሽን | • በ13ቱም የስኳር ፕሮጀክቶች ላይ ቴክኒካል ግምገማ ተካሂዶ ተጠናቋል። <br>• በ13ቱ ላይ የዋጋ ትመና ስራ ተጠናቋል። <br>• የማህበረሰብና ከባቢ አየር ተፅዕኖ ዳሰሳ በመከናወን ላይ ይገኛል። <br>• ዋጋቸውን ከፍ ለማድርግ ሲባል የተወሰኑት ፕሮጅክቶች የማጠናቀቅ ስራ እየተሰራ ይገኛል። |
| 3. | ሎጂስቲክስ | • የሴክተሩ ማሻሻያ ዳሰሳ ተጠናቋል። <br>• በዳሰሳው ላይ ተመስርቶ ቀጣይ ስራዎችን የመለየት ሥራ እየተከናወነ ይገኛል። |
| 4. | የኢንዱስትሪ ፓርክ ልማት ኮርፖሬሽን | • ኢንዱስትሪ ፓርኮች የዳሰሳ ጥናት የሚካሄድ ይሆናል። |
| 5. | የኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ ሀይል ባለስልጣን | • ብድሩ በሚከፈልበት ሁኔታ የማስተካከያ ስራዎች እየተሰሩ ይገኛል። <br>• የሴክተሩ ማሻሻያ ዳሰሳ ተጀምሯል። |
| 6. | የኢትዮጵያ ምድር ባቡር ኮርፖሬሽን | • የሴክተሩ ማሻሻያ ዳሰሳ ተጠናቅቋል። <br>• የቴክኒካል ኮሚቴው የዳሰሳው ሪፖርትን ተመልክቶ በቀጣይ ስራዎች ላይ የሚወስን ይሆናል። |

## 5 ማጠቃለያ

ብዙ ተመክሮበትና ብዙ ሂደቶችን አልፎ በአሁኑ ጊዜ በመተግበር ላይ ያለው የመንግስት የልማት ድርጅቶች ማሻሻያ ሪፎርም በጥናት ላይ የተመሠረተ እንደመሆኑ

የልማት ድርጅቶቹን ባህርይ፣ አቋም፣ ብቃት እና አጠቃላይ ድርጅታዊ ሁኔታዎች በመገምገም የሚፈጸም እንጂ ሁሉንም የመንግስት የልማት ድርጅቶችን አውጥቶ የመሸጥ ጉዳይ አይደለም፡፡

ማሻሻያው እነዚህን የልማት ድርጅቶች በሴክተር ለይቶና ያሉበትን ሁኔታ፣ ድካምና ጥንካሬያቸውን፣ ኢኮኖሚያዊ እና የፋይናንስ አቋማቸውን፣ የብድር መጠን እና ሌሎችም ድርጅታዊ ሁኔታዎችን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት አስፈላጊ የሆነውን ስራ የመስራት ሂደት ነው፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ በተደረገው ዳሰሳ ከእነዚህ የልማት ድርጅቶች ውስጥ ጠንካራ ሊባሉ የሚችሉ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ያሉባቸው ቢሆንም አብዛኞቹ በከፍተኛ ዕዳ የተዘፈቁና ኪሳራ ውስጥ ያሉ በመሆናቸው በዚህ ሁኔታ ቢቀጥሉ መንግስትን ለባሰ የዕዳ ጫና ከመዳረግ በስተቀር ለህብረተሰቡ የሚጠበቅባቸውን አገልግሎቶች ለመስጠት በበቂ ሁኔታ ለመቀጠል የማይችሉ ናቸው፡፡

ስለሆነም ከእነዚህ ድርጅቶች ገሚሶቹ የተቋቋሙበትን ዓላማ ለማሳካትና ሌሎቹም ጊዜው የሚጠይቀውን ድርጅታዊ ቁመና ተላብሰው በገበያ ተወዳዳሪ በመሆን በኢኮኖሚው ትርጉም ያለው እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ እንደ የሁኔታቸው በከፊልና በሙሉ ወደ ግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ እንዲዛወሩ ማድረግ በርካታ ጠቀሜታዎች ያሉት ሲሆን በጥንቃቄ መስራት ስኬታማነቱን ይወስናል፡፡

ለዚህም በአደረጃጀትም ሆነ በባለሙያተኞች በመታገዝ አስፈላጊው ስራ እየተሰራ ሲሆን፤ በዚህም ከዜጎች በሚነሱ ሀሳቦችና ሀገራዊ ጥቅምን በማስጠበቅ መንገድ ተፈጻሚ ለማድረግ እየተከናወነ ይገኛል፡፡

# ፕራይቬታይዜሽን በኢትዮጵያ
# ኢትዮ ቴሌኮም ለምን ይሸጣል?

***ክቡር ገና***

## 1 መግቢያ

የመንግስትን ንብረት ወደ ግል ማዞር እ.ኤ.አ ከ1980 ዓ.ም ጀምሮ የዘለቀና መንግስታትም ትኩረት ሰጥተውት ሲያካሂዱት የቆዩት ጉዳይ ነው። በርካታ ታዳጊ ሀገሮችም ከዓለም ባንክ ድጋፍ ለማግኘት ሲሉ ተገድደው የተቀበሉት ፕሮግራምም ነበር። ሌሎች ሀገሮችም የዕዳ ጫናን ለማቃለል እና ለኢኮኖሚያዊ ቀውስ መፍትሔ ለመስጠት በሚል አስተሳሰብ የመንግስትን ሀብት ወደ ግል የማዞሩን አጀንዳ ገፍተውበታል።

በኢትዮጵያ የመንግስትን ድርጅቶች ወደ ግል ማዞር የተጀመረው በ1986 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 87 (Proclamation No.87/1994) በወጣው የፕራቬታይዜሽን አዋጅ ነው። በዚህ አዋጅ መሠረት እስካሁን 381 ድርጅቶች ከመንግስት ወደ ግል ተዛውረዋል። ወደ ግል የተዛወሩት የማዕድን፣ የእርሻ፣ የትራንስፖርት፣ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች፣ የንግድተቋማት፣ የሆቴሎች እና ቱሪዝም ድርጅቶች ሲሆኑ፤ በእኔ ዕይታ አብዛኞቹ ድርጅቶች ከዚህ በፊት በግል ባለሀብቶች ተመሥርተው በደርግ ዘመን የተወረሱ ሲሆኑ፤ ሌሎቹ ከብሔራዊ ደህንነትና ተያያዥ የህዝብ ጥቅም ፖሊሲዎችና ከገዥዎች ማንነት አንጻር ሲታዩ ያንን ያህል የመንግስት እና የህዝብ ስትራቴጂያዊ ሀብቶች የሚባሉ አይደሉም። እነዚህን ወደ ግል ማዛወር እምብዛም ጉዳት የለውም። ሆኖም ግን ዓላማው ግልጽ ሆኖ ባለመቀመጡ ኢትዮጵያውያን ከፕራቬታይዜሽኑ ሂደት ልዩ ጥቅም አግኝተው ወይም አጥተው እንደሆነ አይታወቅም።

ወርቁ ገበየሁ ባጠናው እና የኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር ባሳተመው ጥናት መሠረትም ከ1986 ዓ.ም ጀምሮ ወደሰግል የተዛወሩት ድርጅቶች ውጤታማ እንዳልሆኑ ያመለክታል። በዚህ ጥናት መሠረት ከ1986 እስከ 2004 ዓ.ም 3.5 ቢሊዮን ብር ገደማ ዋጋ ያላቸው 223 የመንግስት ድርጅቶች ወደ ግል ይዞታነት የተዛወሩ ሲሆን፤ እነዚህ ድርጅቶች ውስጥ ውጤታማነታቸው በመንግስት ሥር ካሉና ከሌሎች በግል ባለቤትነት ስር ካሉ ድርጅቶች ጋር ተወዳደረው ወደ ግል የተዛወሩት

69 በመቶ፣ በመንግስት ስር ያሉት 75 በመቶ፣ በግል ይዞታ ሥር ያሉ ሌሎች ድርጅቶች ደግሞ 71 በመቶ ሆኖ ተገኝቷል (Worku, 2000)፡፡ እናም አጥኚው የኢትዮጵያ መንግስት በይዞታው ስር ያሉ ድርጅቶችን በጥድፊያ እንዳይሸጥ ምክረ-ሀሳብ ለግሰዋል፡፡

እስካሁን ወደ ግል የተዛወሩ የ381 የመንግስት ድርጅቶችን ውጤታማነት ለመለካት መስከረም 6 ቀን 2012 ዓ.ም በአዲስ አበባ በተካሄደ አውደ-ጥናትም ላይ እነዚህ ተሸጠው 45 ቢሊዮን ብር ለመንግስት ያስገቡ ድርጅቶች በአሁኑ ጊዜ በጥሩ ሁኔታ ላይ እንደማይገኙ እና ውጤታማም እንዳልሆኑ ተመልክቷል፡፡

ወደ ራሴ ነጥብ ስመለስ በግሌ ፕራይቬታይዜሽንን በጭፍን የምቃወም ሰው አይደለሁም፡፡ የተወሰኑ የመንግስት ድርጅቶች ወደ ግል ሲዛወሩ ምርትን በማሳደግ፣ ሀብትን በአግባቡ በመጠቀም፣ በተሻለ የስራ አመራር ድርጅቱን በማስፋፋት እና የሥራ ዕድል በመፍጠር የኢኮኖሚ ዕድገት ሊያመጡ ይችላሉ የሚል ግምት አለኝ፡፡

የኔ የትኩረት አቅጣጫ ግን የኢትዮጵያ ህዝብ እና መንግስት ስትራቴጂያዊ ሀብቶች በሆኑት እና ለሀገሪቱም ከፍተኛ ገቢ በሚያመነጩት የኢትዮጵያ ቴሌኮም፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ እና የኢትዮጵያ መብራት ሀይል ላይ ነው፡፡ ስትራቴጂክ ንብረት የምላቸው ለወደፊት የሀገሪቷ ዕድገት አስተዋፅዖ ሊያደርጉ የሚችሉ ስለሆነ ነው፡፡ የእነዚህ የሕዝብ እና የመንግስት ሀብቶች ሽያጭ ጉዳይ የዜጎች የውይይት አጀንዳዎች እየሆኑም አይደሉም፡፡ ጉዳዩ ግን ውይይት ይጠይቃል፡፡ ምክንያቱም ድርጅቶቹ ተራ የንግድ ድርጅቶች ብቻ ሳይሆኑ የሀገር እና የህዝብ ሀብት እና ኩራት በመሆናቸውም ጭምር ነው፡፡ ኢትዮ-ቴሌኮምን ብቻ እንኳን ወስደን ብንመለከት፡-

- ኢትዮ-ቴሌኮም እ.ኤ.አ በ1894 በዳግማዊ አጼ ሚኒሊክ የተመሠረተ የ125 ዓመት የዕድሜ ባለጸጋ ሲሆን አገልግሎቱም የተጀመረው ከሀረር ከተማ እስከ አዲስ አበባ በተዘረጋው የስልክ መስመር ነበር፡፡

- የኢትዮጵያ ቴሌኮም እንደ አየር መንገድ ሁሉ በሌሎች ሀገሮች የሚገኙ የቴሌኮም ድርጅቶችን መግዛት የማይችልበት ምክንያት አይኖርም፡፡

- መስሪያ ቤቱ የመጀመሪያውን 16 ዓመታት ብቻ በውጭ ዜጎች የተመራ ሲሆን እ.ኤ.አ ከ1910 ጀምሮ ግን በኢትየጵያውያን ስራ አስኪያጆችና ቴክኒሽያኖች መመራት የጀመረው ቴሌኮም ስትራቴጂክ የኢንዱስትሪ ሴክተር ነው፡፡ ቻይና በተለይ ይህን በመረዳት በአጭር ዓመታት የዓለምን ገበያ ለመቆጣጠር የቻለችው ቴሌኮምን በእጇ አድርጋ በመቆየቷ ነው፡፡ ዛሬ

የደህንነት (Security) ስጋት የላትም። በእጅ ያለ የቴሌኮም ኩባንያ ለሌሎች ድርጅቶች መፈጠር መነልበት መሣሪያ ይሆናል።

- የኢትዮጵያ ቴሌኮም ከኢትዮጵያ አየር መንገድ በተለየ የተዛባ የማኔጅመንት አስተዳደር ቢኖረውም በየዓመቱ ከ1.4 ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ ለመንግስት የሚያስገባ ድርጅት ነው።

## 2 ፕራይቬታይዜሽን እንደ የኢኮኖሚ አጀንዳ

በብዙ ታዳጊ አገራት ውስጥ ያሉ መንግስታት የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ሊያቀርባቸው ያልቻላቸውን ወይም ያልፈለጋቸውን ሸቀጦች ለማምረት ወይም አገልግሎቶችን ለመስጠት በመንግስት ባለቤትነት የተያዙ ድርጅቶችን ፈጥረዋል። በብዙ አጋጣሚዎች የመንግስት ኢንተርፕራይዞች ችግር መፈልፈያ፣ ውጤታማ ያልሆኑ እና የተቋቋሙባቸውን ዓላማ ማሟላት ያልቻሉ አሉ።

ስለዚህም በመንግስት ባለቤትነት ለተያዙ ኢንተርፕራይዞች ችግር የመጀመሪያው መፍትሔ እንዲሆን የሚቀርበው ምክረ-ሀሳብ ድርጅቶቹን ወደ ግል ይዞታ ማዛወር ነው። ይህ አካሄድ ውጤት የሚያመጣበት ጊዜ እና ቦታ ቢኖርም የመንግስት ልማት ድርጅቶች ችግር ሁሌም የባለቤትነት ጉዳይ እንዳልሆነ ብዙ ማስረጃዎች አሉ። ዋናው ችግር ግልፅ ግቦች እና ዓላማዎች አለመኖር፣ እንዲሁም የእነዚያን ግቦች እና ዓላማዎች አፈፃፀም የሚደግፉ እና የሚያበረታቱ የድርጅት ባህሎች እና ስርዓቶች አለመኖር ነው። በቀላሉ ከህዝብ ወደ የግል ይዞታ የሚደረግ የባለቤትነት ሽግግር የግድ ዋጋውን አይቀንሰውም ወይም የአገልግሎቶችን ጥራት አያሻሽልም።

የፕራይቬታየዜሽን ውሳኔዎች በዋናነት በተጠየቃዊ ትንታኔዎችና ተግባራዊ እውነታ ላይ በመመስረት የምንስማማበት አገልግሎት በተሻለ መሰጠት ያለበት በሕዝብ ወይስ በግል አቅራቢዎች ዘንድ መቻሉን ነው። አገልግሎቶቹ በብቃት ላይ ብቻ የተገደቡ መሆን የለባቸውም። እነሱ በግልጽ ሊገለፁ የሚችሉት በቅድሚያ ብቻ ነው።

### 2.1 ፕራይቬታይዜሽን እንደ የኢኮኖሚ ሥርዓት ለውጥ ሽግግር

የፕራይቬታይዜሽን እና የቁጥጥር ሥርዓት መላላት ኢኮኖሚያዊ መርሆዎች ኢትዮ-ቴሌኮምን በመሸጥ በሀገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ በጠቅላይ ሚኒስትር ዓብይ አስተዳደር ወቅት እውን ይደረጋል። ፕራይቬታይዜሽን ከመንግስት ባለቤትነት ወደ ግል ባለቤትነት የሚደረግ የሀብት ሽግግርን የሚመለከት ነው። በሀገራችንም ፕራይቬታይዜሽን ስንል በፌዴራል መንግስት ወይም የመንግስት አካላት ስር የነበሩ ድርጅቶችን በከፊል ወይም በሙሉ ወደግል የማዞር ሂደት ማለታችን ነው። ፕራይቬታይዜሽን የአመራር እና የባለቤትነት ሽግግርንም ያካትታል። ከዚሁ ጋር

ተያይዞ የማኅበራዊ አገልግሎቶችና የማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ አደረጃጀቶች ለውጦችም ይከሰታሉ።

ብዙ ጥናቶች ፕራይቬታይዜሽን እና የቁጥጥር ሥርዓት መላላት (liberalization) ከፍተኛ ጠቀሜታዎችን ሊያስገኙ እንደሚችሉ ይጠቁማሉ። ይሁን እንጂ የሚያስከትሉት ውጤት ግን አሁንም በጥርጣሬ የሚታይ ነው (Borcherding, 1982; Domberger and Piggott, 1986)።

በቅድሚያ ግን አንዳንድ ነጥቦችን በተለይም ስለ ልል ህግ (deregulation) እና ፕራይቬታይዜሽን ጥቂት ልበል። ልል ህግ የኢኮኖሚ ተዋንያን ተወዳዳሪነትን ለማጎልበት ወደ ገበያ ለመግባት እና ለመውጣት የሚያስችሉ ህጎችና ደንቦችን የሚያላላ ወይም ከነአካቴው የሚያስወግድ የገንዘብ (fiscal) እና የገንዘብ ፖሊሲ እርምጃ ተብሎ ሊጠቀስ የሚችል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ነው (Adegbemile, 2007)። ይህ በገበያ ሀይሎች መካከል በተለይም ከዋጋ ትመና ጋር በተገናኘ የህግን እና የመንግስትን ክልከላዎች የሚያለዝብ ወይም የሚያስወግድ ነው (Ajayi and Ekundayo, 2008; Ojo, 2010)። ለልል ህግ ተግባራዊነት በገበያ ውስጥ የንግድ እንቅስቃሴ እንዴት እንደሚካሄድ የሚደነግግ ነባር ህግ መኖር አለበት። ልል ህግ በቀላሉ እንደ ህግ-አልባነት ወይም ጸረ-ህግ ተደርጎም ሊተረጎም ይችላል። ይህ ማለት ለግል ቢዝነሶች እንደፈለጋቸው እንዲሆኑ በህግ ተፈቅዶላቸዋል እንደ ማለት ነው።

ስለዚህም በልል ህግ የሚመራ ኢኮኖሚ ግለሰቦች ምርት እና አገልግሎታቸውን በፈለጉት ዋጋ እንዲተምኑ ህጉ ይፈቅድላቸዋል ማለት ነው። ነገር ግን ልል ህግ በአንጻራዊነት መጤን አለበት። ከላይ የተገለጸው ልቅነት በተግባር እምብዛም የማይታይ ክስተት ቢሆንም አብዛኛውን ጊዜ ከቦታ ቦታና ከአንድ የንግድ ስራ ሌላ የንግድ ስራ የሚለያይ የመንግስት ቁጥጥር ልልነት ነው የሚኖረው።

ከዚህ በታች የቀረቡት አራት የፖሊሲ ሂደቶች ፕራይቬታይዜሽን የሚያስከትሉ ናቸው።

- መንግስታዊ ፕሮግራሞች ሲቆሙና መንግስት ከተወሰነ የሀላፊነት ተግባሮች ራሱን ሊያገል (በመንግስት ሲመረት የነበረ ምርት ወይም አገልግት በመጠን ሲቀንስ፣ የአንድ ነገር በቀላሉ ተደራሽ መሆን ወይም የምርት ጥራት ደንበኞችን በግል ወደተመረቱ ምርቶች የሚስብ ሲሆን)፤

- የመንግስት መሬት፣ መሠረተ-ልማትና ተቋማት ሲሸጡ ወይም ሲከራዩ (በዚህ ወቅት ግልጽ በሆነ መልኩ የመንግስት ድርጅት ወደ ግል ሀብት ይሸጋገራል)፤

- መንግስት በቀጥታ አንድን አገልግሎት ከመስጠት ይልቅ የግል አገልግሎትን ፋይናንስ ሲያደርግ (ለምሳሌ በኮንትራት መልክ ለግሉ ዘርፍ አገልግሎቱን ሲሰጠው)፤
- ከዚህ ቀደም በመንግስት ተጠቅልሎ የተያዘ የስራ እንቅስቃሴ ልል ህግ ተግባራዊ በመደረጉ ለግሉ ዘርፍ ክፍት ሲደረግ ናቸው።

የግል ባለቤትነት እና ተወዳዳሪ ገበያ (liberalization) አብዛኛውን ጊዜ እጅ ለእጅ ተያይዘው የሚሄዱ ናቸው ተብሎ ቢታሰብም የተለያዩ ጉዳዮች ሆነው እናገናኛቸዋለን። ለሁለቱም ትኩረት በሚሰጡ ኢኮኖሚስቶች ዘንድ ከሁለቱ ጉዳዮች ማለትም የግል ባለቤትነት ወይስ የውድድር መድረኩን መክፈት ይቀድማል የሚል ጥያቄም ይነሳል።

እዚህ ላይ የተለያዩ ሀሳቦች በኢኮኖሚስቶቹ ዘንድ ይቀርባል። ውጤታማነት በግል ባለቤትነት ይወሰናል የሚሉት ፕራይቬታይዜሽንን ሲደግፉ በተቃራኒው ውድድር የውጤማነት መሠረት ነው የሚሉት ደግሞ ፕራይቬታይዜሽንን በጥርጣሬ ያዩታል። እነዚህ ከፕራይቬታይዜሽን ይልቅ ለልል ህግ ትኩረት ይሰጣሉ።

ለምሳሌ መንግስት በቴሌ-ኮም ላይ ያለውን ጠቅላይነት (monopoly) በተመለከተ የግል ባለቤትነትን የሚደግፉ የቴሌን ወደ ግሉ ሴክተር መተላለፍን ይቀበላሉ። ውድድርን የሚመርጡ ደግሞ ቴሌ ከመሸጡ በፊት በመንግስት ይዞታ ስር ሆኖ ካሁን በተሻለ አወቃቀር ወይም አደረጃጀት እንዲሞከር እና በዕኩል ደረጃ የግል ድርጅቶች ከቴሌ ጋር እንዲወዳደሩ እንዲፈቀድላቸው ሀሳብ ያቀርባሉ።

## 2.2 ሁሉም የመንግስት ድርጅቶች መጥፎዎች ሁሉም የግል ድርጅቶች ደግሞ ጥሩዎች አይደሉም

ለፕራይቬታይዜሽን ደጋፊዎች የመንግስት የልማት ድርጅቶች ደካማ አፈጻጸምና የተለጠጠ አደረጃጀታቸው ድርጅቶቹን ወደግል ለማዛወር በቂ ምክንያትና ቅቡል ሀሳብ ነው። የገሀዱ ዓለም ልምድ ግን ይህን በግልጽ አያሳይም። የመንግስት ድርጅቶች በአጠቃላይ ሲታዩ ውጤታማነታቸው እና ቅልጥፍናቸው ላይ ችግር መኖሩ ባይካድም ወደግል ይዞታነት ማዛወሩ ግን ለነዚህ ችግሮች የግድ መፍትሔ ይሆናል ተብሎ አይታሰብም። በአንዳንድ ሀገሮች ለምሳሌ በፈረንሳይ እና በማሌዢያ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ውጤታማ ሆነው ተገኝተዋል። ስለዚህም የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባደጉ ቁጥር የኢኮኖሚ ዕድገት ይቀንሳል የሚለው አስተሳሰብ ትክክል አይደለም። ከተሞክሮ እንደምንረዳው በመንግስት ቁጥጥር ስር ያሉ የልማት ድርጅቶች፤ በተለይም የአስተዳደር እና የአመራር ነጻነት ያላቸው ድርጅቶች፤ ውጤታማነታቸውን አስመስክረዋል።

የመንግስት ድርጅቶችን በተመለከተ ከንብረት ባለቤትነት ጋር ተያይዞ የሚፈጠረው የፖለቲካ ተፅዕኖ በውጤታማነት ላይ አሉታዊ ሚና ይኖረዋል። ዓለም አቀፍ ተሞክሮ እንደሚያሳየው ግን የመንግስት ተቋማት ውጤታማነት በፖለቲካ ባህሉ፣ በመንግስቱ አወቃቀርና መንግስት በተቋማቱ ላይ በሚያራምደው ፖሊሲ ይወሰናል። በበርካታ ሀገሮች የመንግስት ድርጅቶች አስተዳደር የተጠናከረ፣ በባለሙያ የሚመራ እና የተከበረ ሲሆን በሌሎች ሀገሮች ደግሞ በስልጣን ላይ ያለው ፓርቲ ለዜጎቹ ሁሉ ስራ እንዲሰጥ ይጠበቃል። በመንግስት ድርጅቶች ላይ የሚካሄደውም ቁጥጥር እንደ ፖለቲካ አስተዳደሩ መዋቅርና ግንኙነት የተለያየ መልክ ይኖረዋል። ከመንግስት ጋር ያላቸው ቁርኝት እንደ አሜሪካ ባሉ ሀገሮች ላላ ያለመሆኑን ልብ ይሏል።

ነጻ የሆኑ የቦርድ አባላትና በዕቅዳቸው መሠረት ስራ ላይ የሚያውሉትን በጀት የሚያስተዳደሩ የአመራር አባላት ያሏቸው የመንግስት ተቋማት ከፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ራሳቸውን መከላከል ይችላሉ። የህግ ሰውነታቸውን በተመለከተ የመንግስት ድርጅቶች በስራቸው ሌሎች ተቋማትን ሊያቅፉና ፖለቲካዊ አመራር ሊሰጡ ይችላሉ። ነጻ የሆኑ ባለሥልጣናት ወይም ተቋማት በመንግስት ህግ የሚተዳደሩበት የመንግስት ድርጅቶችም በግል ድርጅቶች ህግ የሚተዳደሩበት እና መንግስትም በነዚህ ካምፓኒዎች ድርሻ የሚይዝበትም አሰራር አለ። በርግጥ የህጉ ልዩነት ለውጥ ሊያስከትልም ላያስከትልም ይችላል። ዋናው ጉዳይ ነጻ ሆኖ ያለ ተፅዕኖ መስራት ላይ ነው።

ሲጠቃለል መንግስት እንደ ፖሊሲ መመሪያ አድርጎ የመንግስት ድርጅቶችን በንግድ ሥራ መልክ መምራት ሊያስፈልገውም ላያስፈልገውም ይችላል። በንግድ ስራ መርህ የሚመሩ የመንግስት ድርጅቶችን ወደግል ማዛወር ደግሞ በውጤታማነታቸው ላይ ኢምንት ተፅዕኖ ብቻ የሚያስከትል ይሆናል።

## 3 የፕራይቬታይዜሽን አተገባበር እና ፖለቲካዊ ትርጉሙ

በተግባር የፕራይቬታይዜሽን ትርጉም አንድ ሀገር በአለም ኢኮኖሚ ውስጥ ባለው ስፍራ ይወሰናል። በበለጸጉት ሀገራት ፕራይቬታይዜሽን በቀላሉ እንደ ውስጥ ጉዳይ ፖሊሲ የሚስተናገድ ሲሆን በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት ግን ገዢው የውጭ ባለሀብት በሚሆንበት ጊዜ ብሔራዊ ሀብትን ለባዕድ የመሸጥ ጉዳይ ይሆንና የድርጅቱን አስተዳደር እና ቁጥጥር ጭምር ለውጭ ሰው የማሸጋር ሁኔታ ይፈጠራል። ይህ ድርጊት በግልጽ አነጋገር ብሔራዊ ሀብትን ለባእድ ማውረስ ወይም አሳልፎ መስጠት (denationalization) ይሆናል። የመንግስት ባለቤትነት ማለት ከህዝብ ባለቤትነት መብት ጋር ተያይዞ የመጣ ነው። ፕራይቬታይዜሽን ደግሞ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በዓለም አቀፍ ተቋማት ግፊት የመጣ ጉዳይ ነው።

የመንግስትን እና የህዝብን ሀብት ወደ ግል የማዞር ጉዳይ እንደ አሜሪካ ባሉ ሀገራት እንኳ አረዳዱ እና አተገባበሩ የተለየ ነው። በአሜሪካ የመንግስት ድርጅት ለሽያጭ ወይም ለኪራይ ሲቀርብ ገንዘብ አለኝ ብሎ በጨረታው ለተወዳደረ ለምሳሌ ለአንድ ራሺያዊ አይሸጥም። ሌላው ቀርቶ የአሜሪካ ወዳጅ ለሆነችው ለጃፓን ዜጋ እንኳ አይሸጥም። እንዲህ ያለ የመንግስት ወይም ህዝብ ሀብት እንደ ብሔራዊ ሀብት ስለሚቆጠር በአሜሪካዊ እጅ እንዲቀር ይደረጋል።

አንዲት ሀገር በውጭ መዋዕለ-ንዋይ ላይ ጥገኛ መሆኗ በጨመረ ቁጥር የፕራይቬታይዜሽን ጉዳይ የሀገሪቱን ሉዓላዊነት እና ብሔራዊ ስሜት እየተፈታተነ መሄዱ አይቀርም። ፕራይቬታይዜሽን ይህን መሰል ፈተና ሲደቅን በበርካታ ሀገራት የመንግስትን እና የህዝብን ሀብት ለውጭ ባለሀብት መሸጡ ታግዶ ለዜጎች እና ሀገር በቀል የግል ድርጅቶች በአክሲዮን ወይም በኮንትራት እንዲተላለፉ ይደረጋል። በበርካታ የምዕራብ አውሮፓ ሀገራትም የመንግስት ድርጅቶችን በባለቤትነት የሚይዙት ዜጎች ብሔራዊ ስሜት ያላቸው እንጂ ዓለም አቀፋዊ ስሜት ያላቸው ሶሺያሊስቶቹ አይደሉም። ለዚህ ምነው ፕራይቬታይዜሽንን ተግባራዊ በማድረግ ሂደት ብሔርተኝነት ወሳኝ ሚና የሚኖረው።

## 3.1 ፕራይቬታይዜሽን በኢትዮጵያ - ኢትዮ ቴሌኮም እንደማሳያ

የኢትዮ ቴሌኮም ግማሽ ያህል (49 በመቶ) ድርሻ ለሽያጭ እንደሚቀርብ በመንግስት ይፋ ተደርጓል። አንዳንዶች ኢትዮ-ቴሌኮም በጠቅላይነት (monopoly) ስለተያዘ ውጤታማ አልሆነም ይላሉ። በድርጅቱ ላይ የቀረቡ አሉታዊ መረጃዎች መካከል በዋናነት የሚከተሉት ይጠቀሳሉ።

- ድርጅቱ ከአቻ ተቋማት ውድድር ስለሌለበት ለአዳዲስ ፈጠራ አይተጋም፣ በኔትወርክ ዝርጋታና ማስፋፋት ላይ ውሱንነት አለበት። በአጠቃላይ የዘርፉ ዕድገት ቀጭጯል፤

- እ.ኤ.አ በ2016 በኔትወርክ ዝግጁነት መለኪያ (network readiness index) ኢትዮጵያ ከ139 ሀገሮች 120ኛ ስትሆን በዚህ መለኪያ የምትበልጠው ትንንሾቹን እና ድሀ የሆኑትን ዩጋንዳ (121ኛ)፣ ዙምባብዌ (122ኛ)፣ ሞዛምቢክ (123ኛ)፣ ካሜሩን (124ኛ)፣ ታንዛኒያ (126ኛ)፣ ስዋዚላንድ (129ኛ) እና ማዳጋስካርን (135ኛ) ብቻ ነው።

- በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ልማት መለኪያ (ICT Development Index) ኢትዮጵያ በባሰ ሁኔታ ከ176 ሀገሮች 170ኛ ነች። በተመሳሳይ ሁኔታም በሞባይል ትስስር መለኪያ (Mobile Connectivity Index) ሀገሪቱ

37.7 ነጥብ ብቻ ሰታስመዘግብ ይህም ከመጨረሻ ዝቅተኛው ነጥብ በ17.7 ብቻ ከፍ ያለ ነው።

- በቴሌኮም ረገድ ኢትዮጵያ የልማት ዱካዋን ከምትከተለው ቻይና በእጅጉ ኋላ የቀረች ነች። በአፍሪካ በህዝብ ቁጥራቸው ከኢትዮጵያ ጋር ተቀራራቢ ከሆኑት ከግብጽና ከናጄሪያ ጋር ደግሞ ጭራሽ ልትቀራረብ አልቻለችም። ጎረቤቶቿ የሆኑት ኬኒያና ሱዳን በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ስርጸት በአፍሪካ ከፍተኛ ደረጃ ደርሰዋል። ይበልጥ የሚገርመው ኢትዮጵያ በዓመታዊ ምርታቸው እና የነፍስ ወከፍ ገቢያቸው ከኢትዮጵያ በእጅጉ ያነሱና ወደብ አልባ ከሆኑት ትንንሽ ሀገሮች ከነማሊና ሩዋንዳ በቴሌኮም ስርጸት ያነሰች ነች።

- ኢትዮጵያ ውድድርን ከፈቀዱት ከግብጽና ናይጄሪያ በእጅጉ ኋላ የቀረች ነች። ሁለቱም ሀገሮች አራት አራት ዓለም አቀፍ የቴሌኮም አቅራቢዎችን ጋብዘው የውድድሩ ተጠቃሚ ሆነዋል።

ይህ ከላይ የሰፈረው አሉታዊ መረጃ ሁሉ ቢቀርብም እኔ ግን አሁንም ኢትዮ ቴሌኮም የተሻለ ስራ ሊሰራ ይችላል የሚል እምነት አለኝ። ደግሞ ስለዚህ ሁሉ ድክመቱ ኢትዮ ቴሌኮምን ወደ ግል ማዛወር ብቸኛው መፍትሔ አይደለም እላለሁ።

የዓለም ባንክ፣ ዓለም አቀፉ የገንዘብ ተቋም፣ ምዕራባዊያን የልማት ተቋማት እና ጠቅላይ ሚኒስትር ዓብይ አህመድ የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ችግሮች ለመፍታት ፕራይቬታይዜሽን ተገቢ ነው ብለው ይከራከራሉ። የእነርሱ አቀራረብ መጀመሪያ ፕራይቬታይዝ ይደረግ ከዚያ ነገሮች ሁሉ መልካም ይሆናሉ የሚል ነው። ይህ የራሺያ እና የምስራቅ አውሮፓ አካሄድ ነው። በዚህ አካሄዳቸውም ተጠቃሚ አልሆኑም።

የመንግስት የልማት ድርጅቶች ችግር በመንግስት ባለቤትነት መያዛቸው አይደለም። ከዚያ ይልቅ ግልጽ የሆነ ግብና ዓላማ ያለመኖር እንዲሁም ግቦቹንና ዓላማዎቹን ለማሳካት የሚያግዝ ተቋማዊ የአሰራር ባህልና ስልት ያለመኖር ነው ባይ ነኝ። በአንዳንድ ሁኔታ ፕራይቬታይዜሽን የድርጅቶችን የአሰራር ባህልና ስልት በማስፈን የድርጅቶችን ግቦች እና ዓላማዎች ለማሳካት ሊረዳ ይችላል። በሌላ አጋጣሚዎች ደግሞ ፕራይቬታይዜሽን ይህን ማሳካት ሲሳነው ተስተውሏል።

ስለዚህም እንደ ኢትዮ ቴሌኮም፣ አየር መንገድ እና መብራት ሀይል ያሉ የኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት ንብረት የሆኑ ብሔራዊ ሀብቶችን ፕራይቬታይዝ ማድረግ በማደግ ላይ ላለችው ኢትዮጵያ ትክክለኛ መፍትሔ አይደለም ስል እከራከራለሁ። ደግሞም

እነዚህ ሁሉ ተሸጠው ኢትዮጵያ ምን የጋራ ሀብት ሊቀራት ነው? አብሮ መኖሩ ከተናጋ የሀገር ባህልና ታሪክ ከጠፋ ምን ይቀረናል?

ከፕራይቬታይዜሽን ይልቅ ሌሎች አማራጮች አሉ። እነርሱም፦

- በመንግስት የልማት ድርጅቶች ዘንድ ነጻነት ያለው የልማት ድርጅቶች ስራ አመራር ተግባራዊ ማድረግ፤
- ውድድርን እና ልል ህግን ስራ ላይ ማዋል፤
- የልማት ድርጅቶችን ለስራ አመቺ በሆነ መልኩ ማወቀር እና ሌሎች የግል ድርጅቶች በዕኩልነት መንፈስ እንዲወዳደሩ በሩን መክፈት። (ይህ የቻይና ሞዴል ሲሆን ከ20 ዓመት ባነሰ ጊዜ ውስጥ እንደ ህዋዌ (Huawei) ያለ የግል እና እንደ ዜድቲኢ (ZTE) ያለ የመንግስት የቴሌኮም ድርጅቶችን መመስረት ችለዋል።)
- በከፍተኛ ደረጃ ውጤታማ የሆነ እና ቁርጠኝነት ያለው ባለሙያ መመልመል፤
- ጠባብ፣ የአጭር ጊዜ ጥገናዎችን አለመከተል፤
- ጠንክሮ ሀገርን መገንባትና እጅ አለመስጠት።

## 3.2 የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን መነሻና መድረሻ

መንግስት ለምን ፕራይቬታይዝ ያደርጋል?

- ክንውኑ በዋነኛነት ገቢ የማግኘት እንቅስቃሴ ነው?
- የአወቃቀር እንቅስቃሴ ነው?
- ገበያን ብርግድ አድርጎ ከመክፈት በፊት ያለ ቅድመ ሁኔታ ነው?
- የልማት ድርጅቶቹን ለማዳን ነው?

መንግስት ድርጅቶቹን ፕራይቬታይዝ ለማድረግ የሚሰጣቸው ምክንያቶች

- የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ለመሳብ፤
- የሀገሪቱን የስራአፈጻጸም በማቀላጠፍ የኢኮኖሚ ማሻሻያ አጀንዳውን ለማገዝ፤
- ለአጠቃላይ የኢኮኖሚ መዋቅሩ አስተዋጽኦ የሚያበረክት ሀብትን ከንግድ ስራ ፈቃድ፣ ከግብር እና ከትርፍ ገቢ ለማግኘት፤

- የሀገሪቱን የብድር ዕዳ ለመቀነስ (ይህ ሀሳብ በቅርቡ በታተመው ኢትዮጵያን ሔራልድ ዕለታዊ የእንግሊዝኛ ጋዜጣ ርዕሰ አንቀጽ ላይ እንዲህ የሚል ጽሁፉ ቀርቧል። *‹‹የሀገሪቱ የዕዳ ጫና የምር ስጋት የደቀነ ስለሆነ ችግሩን ለመቅረፍ የአጭርና የረጅም ጊዜ መፍትሔ ያስፈልጋል።አንዱ ተግባራዊ ሊደረግ የሚችል መፍትሔ የመንግስት ልማት ድርጅቶችን ፕራይቬታይዝ ለማድረግ የተጀመረውን ጥረት ማፋጠን ነው››።*)

ከላይ በተለያዩ የመንግስት ቃል አቀባዮች የተሰጡ ምክንያቶች ድርጅቶቹን ወደግል የሚዛወሩበትን ምክንያትና ፕራይቬታይዜሽን ሀገሪቱ ላቀደቻቸው ግቦች የሚያስገኘውን ውጤት በተመለከተ በቂ አይሆኑም።

መልሰን ጥያቄዎችን እንመልከት፤

- የብድር ጫናን ለመቀነስ ነው? - አይደለም! ቅነሳው ምን ያህል ቢሆን ነው? ምን ያህል ገቢ ተገኝቶ ነው ብድሩ የሚቀንሰው?
- ድርጅቶቹን ከኪሳራ ለመታደግ ነው? አይደለም! ቴሌኮምም ሆነ አየር መንገድ ገዥዎች የቋመጡባቸው ድርጅቶች ሲሆኑ የተፈለጉትም አትራፊ በመሆናቸው ነው።
- ብዙ ገቢ ለማመንጨት ነው? አይደለም! ከዚህ በተሻለ ገቢ ለማስገባት አስተዳደሩን መለወጥ በቂ ነው። የግል ድርጅት አይከስርም ያለው ማነው?
- የንግድ ስራን ለማቀላጠፍ ነው? አይደለም! ፕራይቬታይዜሽን ሳይሆን ነጻ ማድረግ (Liberalization) የተሻለ ውጤት ያመጣል።

መንግስት ድርጅቶቹን ፕራይቬታይዝ ለማድረግ የሚሰጣቸው ምክንያቶች አንድ በአንድ ሲቃኙ፡-

### i. የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ

በውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ላይ የተጻፉ ድርሳናትን ያየን እንደሆነ ፕራይቬታይዜሽን የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ለመሳብ ቁልፍ ስትራቴጂ እንዳልሆነ እንረዳለን፡፡ ከፕራይቬታይዜሽን ይልቅ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ለመሳብ የሚከተሉት ምክረ ሀሳቦች ይጠቀሳሉ፡-

- ገበያን ክፍት ማድረግና የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰትን ማሳለጥ። በውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ላይ የተጣሉ ገደቦችን ማላላት። የውጪና የሀገር ውስጥ ድርጅቶችን ባለየ ሁኔታ ክፍት፣ ግልጽነት ያለውና አስተማማኝ የስራ ከባቢያዊ ሁኔታ መፍጠር። ምቹ ሁኔታው ስራን

በቀላሉ የመስራት፣ ለገቢ እቃዎች ተደራሽ መሆን፣ እንደ ሁኔታው ሊቀያየር የሚችል የጉልበት ገበያ እንዲሁም የእዕምሯዊ ንብረት መብት ጥበቃን ያካትታል።

- ሀገሪቱን ከሙስና ማላቀቅ፤
- መልካም አስተዳደር ማስፈን
- ብቃት ላላቸው ባለሀብቶች የሚሆን መሠረተ-ልማቶችን ማሟላት። መሠረተ-ልማቶቹም እንደ አውሮፕላን ማረፊያና ወደብ፣ በቂና አስተማማኝ የሀይል ምንጭ፣ ለልዩ የቴክኒክ ባለሙያዎች ማሰልጠኛ የሚሆን ተቋም እና በበቂ ሁኔታ የሰለጠነ የሰው ሀይል የመሳሰሉት ናቸው።
- በሀገር ውስጥ የፋይናንስ ገበያ ላይ ማሻሻያ በማድረግ የብድር አገልግሎትን ተደራሽ ማድረግ። ለንግድ ስራ ምቹ የሆነ የፋይናንስ ስርዓት መዘርጋት ሀገር በቀል ድርጅቶች ከውጭ ተፎካካሪ ተቋማት የሚደርስባቸውን ጫና ለመቋቋም ያስችላቸዋል። የሀገር ውስጥ ድርጅቶቹ ግብዓት አቅራቢ በመሆን እንዲያድጉ እና እንዲበለጽጉም ይረዳቸዋል (Alfaro et al., 2009)
- ሲጠቃለል የጉልበት ዋጋ፣ የሙያ ክህሎት፣ የግብር ምጣኔ፣ የኢኮኖሚው መጠን (የማደግ አቅም)፣ የፖለቲካ መረጋጋት፣ የግብዓት አቅርቦት፣ ላላ ያለ የውጭ ምንዛሬ ምጣኔ፣ ነጻ የንግድ ቀጠናዎች ተደራሽነት ለውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰት አስፈላጊ ናቸው።

ii. ***የሀገሪቱን የሥራ አፈጻጸም በማቀላጠፍ የኢኮኖሚ ማሻሻያ አጀንዳውን ለማገዝ***

ፕራይቬታይዜሽን እንዴት አድርጎ የኢትዮጵያን ንግድ፣ የምርት እና የአገልግሎት አሰጣጥን እንደሚያቀላጥፍ አይገባኝም። ስራ አፈጻጸምን ለማቅለል እና ቀልጣፋ ለማድረግ የኢትዮ ቴሌኮምንም ሆነ የኢትዮጵያ አየር መንገድን መሸጥ አያስፈልግም። ይልቅ ስራን ለማቀላጠፍ የዘርፉ ሊቃውንት የሚከተለውን ምክረ-ሀሳብ ይለግሳሉ፡-

- የግንባታ ፈቃድ አሰጣጥን ማቅልል፤
- በድንበር አካባቢ ንግድን ለማቀላጠፍ ምቹ ሁኔታ መፍጠር፤
- በቀላሉ ንግድን ለመጀመር የሚያስችል አሰራርን መዘርጋት፤
- ብድር በቀላሉ ሁኔታ የሚገኝ እንዲሆን ማስቻል፤

- የሀይል አቅርቦትን ተደራሽ ማድረግ፤
- የሀብት ምዝገባን ቀልጣፋ ማድረግ እንዲሁም፤
- ግብርን በቀላሉ እና በፍጥነት መሰብሰብ ናቸው።

### iii. ለአጠቃላይ የኢኮኖሚ መዋቅሩ አስተዋጽኦ የሚያበረክት ሀብትን ከንግድ ስራ ፈቃድ፣ ከግብርና ከትርፍ ገቢ ለማግኘት

እዚህ ላይ ነው እንግዲህ በኢትዮጵያን ፕራይቬታዜሽንን የሚያቀነቅኑ ፖለቲከኞችም ሆኑ የመንግስት ስራ ኃላፊዎች ልምድ ማነስ ጎልቶ የሚታየው። ድንበር ዘለል ኩባንያዎች ተገቢውን ታክስ በመክፈል ረገድ እጅግ ዳተኞች ናቸው። እስቲ ባለፉት አስር ዓመታት የተለያዩ ሀገራትን ቴሌኮምን ገዝተው ታክስ ባለመክፈላቸው በየሀገሩ ፍርድ ቤቶች የሚታየውን የድንበር ዘለል ድርጅቶች ክስንና ክርክር እንመልከት! ይህን ሀቅ ለመረዳት ዓለም አቀፍ ጋዜጦችንና የቴሌቪዥን ዜናዎችን መከታተል ብቻ ይበቃል።

### iv. የሀገሪቱን የብድር ዕዳ ለመቀነስ

የብድር ጫናን ለመቀነስ የኢትዮ-ቴሌኮምን ፕራይቬታይዝ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑ በምክንያትነት ተጠቅሷል። እዚህ ላይ አንድ ጥያቄ እንድንጠይቅ ይፈቀድልን። ከፕራይቬታይዜሽኑ ምን ያህል ገቢ (ያውም የአንድ ጊዜ) እንደሚገኝ ሳይታወቅ እንዴት ስለዕዳ ጫና ቅነሳ ማውራት እንችላለን? ኢትዮ ቴሌኮም ለምሳሌ በራሱ ዕዳውን የመክፈል አቅም እያለው እንደሌለው ለምን ይነገራል?

## 4 የኢትዮ-ቴሌኮምን ፕራይቬታይዝ መደረግን ለምን እቃወማለሁ?

የኢትዮ-ቴሌኮምን ፕራይቬታዝ መደረግ በሚከተሉት ምክንያቶች እቃወማለሁ።

1. ፕራይቬታይዜሽኑ ምንን እንደሚያሳካ ወይም ምን ችግር እንደሚፈታ የሚያመለክት ግልጽ ዓላማ አልተቀመጠም (የመንግስትን የበጀት ጉድለት ለማሟላት ይሁን ወይም የዕዳ ጫናን ለማቃለል የተባለ ነገር የለም)።
2. ባለፉት ሦስት አስርተ ዓመታት ኢትዮጵያ የቴሌኮም ፖሊሲም ሆነ የመቆጣጠር አቅም አልገነባችም። ቴክኒካዊም ሆነ የፖሊሲ ቀረጻ አቅም የሚገነባው በዓመታት ትምህርትና የስራ ልምድ በመሆኑ በዚህ ዘርፍ ያለውን እንቅፋት በፍጥነት እና በቀላሉ ማለፍ አይቻልም። መመሪያዎችን በማስፈጸም ብዙ ልምድ ያላቸው ያደጉ ሀገራት እንኳ ዓለም አቀፋዊ ኩባንያዎችን መቆጣጠር አልቻሉም ።

3. ድርጅቶችን ወደ ግል በማዛወር ሒደት ውስጥ የባለድርሻዎችን (ህዝብ) ጥቅም የሚያስጠብቅ ማን ነው? የትኛው አስተዳደር? የኢህአዴግ?

4. ሁሉም ነገር አስፈላጊ ነው! ሁሉም ነገር በአንድ ጊዜ መከናወን አለበት! በሚል የጥድፊያና ጥሞና-አልባ መንፈስ የሚካሄድ በመሆኑ:: በማንኛውም መንግስት ዘንድ ያሉ የጊዜ፣ የትኩረትና የሀብት እጥረቶችን ግምት ያስገባ ትክለኛ ውሳኔ ማድረግ ሁሌም አስፈላጊ ነው:: ያለንን ውስን ገንዘብ ፕራይቬታይዜሽኑን ተግባራዊ ለማድረግ ጨረታ በማዘጋጀት፣ ሠነዶችን በማዘጋጀትና ሽያጩን ለማከናወን የሚያስፈልጉ ጉዳዮች ላይ ማዋል ይሻላል ወይስ አዳዲስ ካምፓኒዎች እንዲጎለብቱ ለንግድና ምርት ስራ እንቅፋት የሆኑ ደንቃራዎችን ለማስወገድ፣ የቢዝነስ ሕጉን ለማዘመን፣ የታክስ አሰባሰቡን ቀልጣፋ ለማድረግ ብናውለው ይሻላል?

5. ፕራይቬታይዜሽን በዘመናዊ የኢኮኖሚ ዕሳቤ ከስትራቴጂያዊ የሀብት ማካበቺያ ስልትነት ይልቅ የተወሰነ ባለሀብት እንዲከብር የማድረግ ዘዴ ስለሆነ፤

6. መላው የፕራይቬታይዜሽን ሂደቱ ግልጽነት የጎደለው መሆኑ:: ለዚህ ማሳያ የሚሆነው ደግሞ በሐምሌ 27 ቀን 2010 ዓ.ም በጠቅላይ ሚኒስቴር ዐብይ አህመድ የተሾሙት 21 የፕራይቬታይዜሽን አማካሪ ምክር ቤት አባላት ስላከናወኑት ተግባር እስካሁን ምንም ዓይነት መግለጫ ያለመስጠቱ ነው::

7. አሁን ያለው መንግስት እነዚህን የልማት ድርጅቶች እንዲሸጥ የህዝብ ውክልና ስለሌለው::

8. እንዲህ አይነት ወሳኝ ተግባር ለማከናወን አሁን ሀገሪቱ ያለችበት ሁኔታ አመቺ ባለመሆኑ::

9. ፕራይቬታይዜሽን መንግስት ትኩረት የሰጣቸውን እንደ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ያሉትን ለሀገሪቱ ወሳኝ የሆኑ ዘርፎችን ለድርድር የሚያቀርብ በመሆኑ::

10. የቴሌኮም አገልግሎት ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ ስለሚጨምር (ይህን ለማረጋገጥ የቴሌኮም አገልግሎታቸውን ፕራይቬታይዝ ያደረጉትን ሀገሮች መመልከት ነው)::

**ኢትዮ ቴሌኮም ስለራሱ ምን ይላል?**

የ125 አመት የዕድሜ ባለጸጋ የሆነውና በታሪካዊነቱ የኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት ሀብትና ኩራት የሆነው የኢትዮ ቴሌኮም ሽያጭን የምቃወምበትን ምክንያት ከላይ ጠቅሻለሁ:: እስቲ አሁን ደግሞ ድርጅቱ ስለራሱ የሚናገረውን ከዓመታዊ የስራ አፈጻጸሙና ከዕቅዱ በጥቂቱ እንመልከት::

**ኢትዮ ቴሌኮም በ2011 በጀት ዓመት**

የ2011 በጀት ዓመት የድርጅቱ ሪፖርት እንደሚያመለክተው ተቋሙ የሚከተለውን ይመስላል::

- ከ15 ሺህ በላይ ሠራተኞች አሉት::
- በበጀት ዓመቱ 36.3 ቢሊዮን ብር አጠቃላይ ገቢ ያገኘ ሲሆን ይህም የዕቅዱን 85 በመቶ ነው:: ካለፈው በጀት ዓመት አንፃር የ7 በመቶ ዕድገት አሳይቷል::
- በበጀት ዓመቱ የተቋሙ ያልተጣራ ትርፍ 24.5 ቢሊዮን ብር ሲሆን ካለፈው በጀት ዓመት የ5.6 በመቶ ዕድገት አሳይቷል::
- ኢትዮ ቴሌኮም በበጀት ዓመቱ 16.2 ቢሊዮን ብር ግብር ከፍሏል:: ይህ የግብር መጠን በሀገራችን ከከፍተኛ ግብር ከፋዮች በዘንድሮ ዓመት ከተሰበሰበው 85.9 ቢሊዮን ብር የ18.8 በመቶ ድርሻ ይይዛል::
- ኢትዮ ቴሌኮም በበጀት ዓመቱ 7 ቢሊዮን ብር ዲቪደንድ ለመንግስት ከፍሏል::
- የበጀት ዓመቱ አንዱ ስኬት የሆነው ባለፉት ሦስት ዓመታት ሳይከፈል የቆየ ብድር መክፈል መቻሉ ሲሆን፤ በዚህ በጀት ዓመት 9.9 ቢሊዮን ብር ወይም 362 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ብድር ክፍያ ተፈጽሟል::
- የኢትዮ ቴሌኮም ደንበኞች ብዛት 43.6 ሚሊዮን የደረሰ ሲሆን ከዕቅዱ አንፃር የ95 በመቶ አፈፃፀም እና ከባለፈው የበጀት ዓመት የ15 በመቶ ዕድገት አለው:: አጠቃላይ የቴሌኮም ስርጸት (teledensity) መጠኑ 44.5 በመቶ ደርሷል::
- የቴሌኮም አገልግሎትን አጠቃቀም ለማሻሻል እንዲሁም የደንበኞችን እርካታን ለመጨመር ያለመ ከ40 እስከ 50 በመቶ የሚደርስ ከፍተኛ የታሪፍ ቅናሽ በሁሉም ምርትና አገልግሎቶች ላይ ተደርጓል::
- በበጀት ዓመቱ ተቋሙ በተቀናጀ መልኩ ማኅበራዊ ኃላፊነትን ከመወጣት አንፃር በትምህርት፣ በጤና፣ በግብርና፣ በማኅበራዊ አገልግሎቶች፣ ህጻናትን፣ ሴቶችን፣ ወጣቶችን፣ አረጋዊያንን በማገዝ እና በአካባቢ ጥበቃ ዘርፎች ላይ በመሳተፍ በድምሩ ከ300 ሚሊዮን ብር በላይ በዓይነትና በገንዘብ አስተዋጽኦ አድርጓል::

### ኢትዮ ቴሌኮም በ2012 በጀት ዓመት

ድርጅቱ ከ2012 እስከ 2014 ዓ.ም የሚቆይ የሦስት ዓመት የስትራቴጂክ ዕቅድ ይፋ ያደረገ ሲሆን ለማሳያ ያህል የ2012 በጀት ዓመትን ዕቅድ ስንመለከት፡፤

- ኢትዮ ቴሌኮም በ2012 የበጀት ዓመት የደንበኞቹን ቁጥር ከ43.6 ሚሊዮን ወደ 50.4 ሚሊዮን ለማሳደግ አቅዷል።
- ገቢውን ከ36.3 ቢሊዮን ብር ወደ 45.4 ቢሊዮን ብር ለማሳደግ አቅዷል።
- የቴሌ ስርፀትን (teledensity) ከ44.5 በመቶ ወደ 50.5 በመቶ ለማሳደግ አቅዷል።

## 5 መደምደሚያ - ምን መደረግ አለበት?

በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውስጥ ከሁሉም የኢኮኖሚ ዘርፎች በላይ ወደፊት አስፈላጊ የሚሆነው ቴሌኮሙኒኬሽን ነው። ምክንያቱም መጪው ዘመን የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዘመን ነውና። ደግሞ ከላይ ባየነውና መስሪያ ቤቱ ይፋ ባደረገው የ2011 በጀት ዓመት የስራ አፈጻጸም ሪፖርትና በ2012 በጀት ዓመት ዕቅዱ መሠረት ኢትዮ ቴሌኮምን ለመሸጥ የሚያስገድድ ምን ምድራዊ ምክንያት ይኖራል? ስለዚህ በመንግስት ይዞታ ሥር ያለውን ኢትዮ ቴሌኮምን እንዳለ በመተው ይልቅ ችግሮቹን በማስወገድ ላይ ብናተኩር ይሻላል። አዳዲስ ድርጅቶች እንዲመሰረቱ መትጋት፣ የስራ ፈጠራ እንዲጎለብት ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣ የንግድ፣ የምርትና አገልግሎት ተቋማት በተረጋጋና ዘላቂነቱን በጠበቀ መልኩ እንዲያድጉ በገበያ የሚመራ ኢኮኖሚ መገንባት ይጠበቅብናል።

አሁን በመንግስት ይዞታ ስር ያሉ የመንግስትና የህዝብ ድርጅቶች ወደ ፊት ለሚመጡት አዳዲስ የግል ድርጅቶች እንደ ማነጻጸሪያና ዕድገታቸውንም ለማነሳሳት ጠቃሚ ናቸው። አዳዲሶቹ የግል ተቋማት በበኩላቸው ኢኮኖሚያዊና ማኀበራዊ ጥቅም በማስገኘት ሚዛን ያስጠብቃሉ። እያደጉ ሲሄዱም በመንግስት ድርጅቶች ውስጥ ይሰሩ የነበሩ ሰራተኞችን በመቅጠር ልምድ ያለውን የሰው ሀይል ተጠቃሚ ያደርጋሉ።

የኢትዮ ቴሌኮም ራዕይ ‹‹*በዓለም አቀፍ ደረጃ ግንባር ቀደም የቴሌኮም አገልግሎት ሰጪ መሆን ነው*›› ይላል። ኢትዮ ቴሌኮም በዓለም አቀፍ ደረጃ ተዋናይ መሆን ከፈለገ ለውድድር ራሱን ማዘጋጀት ይኖርበታል። ኢትዮ ቴሌኮምም ሆነ ሌላ ማንኛውም አካል ውድድርን ሊማር የሚችለው በውድድር ውስጥ ብቻ መሆኑን ልብ ሊል ይገባል።

## ዋቢ ጽሑፎች

Worku Gebeyehu 2000 Has Privatization Promoted Efficiency in Ethiopia? - Ethiopian Journal of Economics, Volume IX, No. 2, October 2000.

Orcherding,1982; Proletarische Frauenbewegung: Literatur-und Forschungs dokumentation 1982-1986.

Domberger and Piggott, 1986 Domberger, Simon & Piggott, John, 1986. "Privatization Policies and Public Enterprise: A Survey

Adegbemile, 2007. Developments in Telecommunications in Nigeria and its Impact on National Development: Experiences from Around the World.

Ojo, 2010. The Relationship Between Service Quality and Customer Satisfaction in the Telecommunication Industry: Evidence From Nigeria.

Alfaro et al., 2009 FDI, Productivity and Financial Development.

# የመወያያ ፅሁፎቹን ያቀረቡ ምሁራን



**ፕሮፌሰር ዓለማየሁ ገዳ**
በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ (ማክሮ-ኢኮኖሚክስ) እና የዓለም-አቀፍ ንግድና ፋይናንስ ፕሮፌሰር ሲሆኑ፤ በለንደን ዩኒቨርስቲ የአፍሪካና እስያ ትምህርት ክፍል፣ በኬንያ-ናይሮቢ የአፍሪካ የኢኮኖሚ ምርምር ማዕከልና በዑጋንዳ-ካምፓላ ማካራሬ ዩኒቨርስቲ ስር የሚገኘው የኢኮኖሚ ምርምር ተቋም መምህርና ተባባሪ የምርምር ፕሮፌሰር ናቸው። ከ60 በላይ የምርምር ፅሁፎችንና 6 መፅሀፍትን በኢትዮጵያና በአፍሪካ አገሮች ምርምራቸው ላይ ተመስርተው ዓለም-አቀፍ በሆኑ የምርምር መፅሔቶችና ታዋቂ አሳታሚዎች አሳትመዋል።



**ዶ/ር ብሩክ ታዬ**
የኢኮኖሚክስ እና ህግ የዶክትሬት ዲግሪ ያላቸው ሲሆን በአሁኑ ወቅት የገንዘብ ሚኒስቴር አማካሪ ሆነው በማገልገል ላይ ይገኛሉ። በተለይም የመንግስት ልማት ተቋማትን ወደ ግል ማዛወር፣ ኢኮኖሚ ማሻሻያ፣ ብድር እና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ይሰራሉ። ቀደም ብሎ በአሜሪካን ሀገር ኒዮርክ በሚገኝ የባንኮች ህግ ተቋም ውስጥ በፈንድ ማኔጀርነት አገልግለዋል።



**አቶ ክቡር ገና**
በተባበሩት መንግስታት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን በአዲስ አበባ እንዲሁም በተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም ኒውዮርክ በተለያዩ የስራ መስኮች ያገለገሉ ሲሆን፤ በምርምርና በልማት ጉዳይ ፕሮጀክቶች በተመራማሪነትና በአማካሪነት የካበተ ልምድ አላቸው። የአዲስ አበባ እና የኢትዮጵያ ንግድ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት እንዲሁም የፓን አፍሪካ ንግድና ኢንዱስትሪ ምክር ቤት አመራር ሆነው አገልግለዋል። በአሁኑ ጊዜ በልማትና ሰብዓዊ መብት ላይ ትኩረት የሚያደርገው የኢኒሽቲቭ አፍሪካ ድርጅት ኤክስኪዩቲቭ ዳይሬክተር ናቸው።



**ዶ/ር ቴዎድሮስ መኮንን**
በኢኮኖሚ ምርምር ከሌስተር ዩኒቨርስቲ የፒኤችዲ ዲግሪ፣ በኢኮኖሚ ፖሊሲ ትንተና ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የማስተርስ ዲግሪ ያገኙ ሲሆን፤ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ አሶሲዬሽን የኢኮኖሚ ፖሊሲ ምርምር ተቋም በማክሮ ኢኮኖሚ ክፍል በጁንየር ሪሰርች ፌሎውነት ለ5 ዓመታት አገልግለዋል። በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የጥናትና ምርምር ክፍልም ለ5 ዓመታት በጁኒየር ሪሰርች ኦፊሰርነት አገልግለዋል። በአሁኑ ወቅት በኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ እና በለንደን ስኩል ኦፍ ኢኮኖሚክስ (LSE) በጋራ በሚካሄደው አለም ዓቀፍ የዕድገት ማዕከል ካንትሪ ኢኮኖሚስት ሆነው በማገልገል ላይ ይገኛሉ።